# የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች

# ስልጠና ማዕከል

**ለቅድመ ስራ ሰልጣኞች የተዘጋጀ**

**የስልጠና ሞጁል**

# የማስረጃ ሕግ

በፌደራል የፍትህ አካላት በለሙያወች ማሰልጠኛ ማእከል የተዘጋጀ

## Contents


መግቢያ ........ 2
አጠቃላይ የትምህርቱ ዓላማ ........ 4
ክፍል አንድ ........ 5
ስለማስረጃ አጠቃላይ ግንዛቤ ........ 5
ምዕራፍ 1 ........ 5
የማስረጃ ጽንሰ ሐሳብ፣ አስፈላጊነትና ዓይነቶች ........ 5
1.1. የማስረጃ ጽንሰ -ሐሳብ ........ 6
1.2. የማስረጃ ዓይነቶች ........ 8
ምዕራፍ 2 ........ 14
ማስረጃ ስለማያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች ........ 14
ክፍል ሁለት ........ 22
ማስረጃን ለፍርድ ቤት ስለማቅረብ ........ 22
ምዕራፍ 3 ........ 22
ስለማስረጃ ተቀባይነት ........ 22
ምዕራፍ 4 ........ 37
ስለ ማስረጃ አቀራረብ ........ 37
ምዕራፍ 5 ........ 46
ምስክሮችን ስለመመርመር ........ 46
5.1. ጠቅላላ ........ 46
5.2. ምስክሮች በተከራካሪ ወገኖች ፊት ቀርበው መመስከር የሚገባቸው ስለመሆኑ ........ 47
ክፍል ሦስት ........ 53
ማስረጃን ስለመመዘን ........ 53
ምዕራፍ 6 ........ 53
የማስረጃ አስረጅነት መመዘኛ (ደረጃ) ........ 53
ምዕራፍ 7 ........ 67
የምስክሮችን ቃል አስረጅነት ስለመመዘን ........ 67
7.5. ሳይጠቀሱ የታለፉ ፍሬ ነገሮች (Omissions) የሚያስከትሉት ዉጤት ........ 82
7.6. ጥቅም ያላቸው ምስክሮች የምስክርነት ቃል ምዘና ........ 87
ምዕራፍ 8 ........ 92
የሰነዶችንና ኤግዚቢት ማስረጃዎችን አስረጂነት ስለመመዘን ........ 92
8.2. የጽሁፍ ሰነድ ማስረጃዎች ምዘና ........ 94
ምዕራፍ 9 ........ 102
የእምነት ቃል አስረጂነትን ስለመመዘን ........ 102

## መግቢያ

በፍርድ ቤት ክርክር የሚደረግባቸው ጉዳዮች ሁሉ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ማስረጃን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን የሚያስነሱ ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡ ውሳኔ ሊሰጥባቸው የተፈለጉት ጭብጦች ህግን የሚመለከቱ ቢሆኑ እንኳ ወደ ህግ ጭብጥነት ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት ፍሬ ነገሮችን የሚመለከቱ ጭብጦችን እንደሚያስተናግዱ የሚታወቅ ነው፡፡ ፍሬ ነገሮቹን የሚመለከቱት ጭብጦች የሚረጋገጡት ወይም የሚስተባበሉት ደግሞ በማስረጃ አማካኝነት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የፍሬ ነገሮችን መኖር ወይም የመደምደሚያን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል ያስችላል ተብሎ የቀረበ ማስረጃ ሁሉ እንደተባለው ያረጋግጣል ወይም ያስተባብላል ለማለት አይቻልም፡፡ በሥራ ሂደት ትልቅ ችግር ሆኖ የሚታየው ማስረጃን የመመዘን ጉዳይ ነዉ፡፡ የቀረበዉ ማስረጃ እውነተኛ ወይም ትክክለኛ ላይሆን ይችላል፤ ወይም እውነተኛ ወይም ትክክለኛ ቢሆን አንኳን ያስረዳዋል ወይም ያስተባብለዋል የተባለውን ፍሬ ነገር ወይም የተደረሰ መደምደሚያ በተፈለገው ደረጃ ላያስረዳ ይችላል፡፡ ስለዚህም ማስረጃውን የሚቀበለው ፍርድ ቤት የቀረበለትን ማስረጃ የመመዘን ኃላፊነት ይወድቅበታል፡፡ የሚመዝነው ደግሞ በአንድ በኩል በማስረጃነት የተገለፀው ፍሬ ነገር እውነተኛ ወይም ትክክለኛ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ነው፡፡ ማለትም ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ የሆነውን ፍሬ ነገር መኖር ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል በማስረጃነት የቀረበው ፍሬ ነገር "እውነት ነው ወይስ አይደለም" የሚለውን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ያጣራል፡፡ በሌላ በኩልም የተባለው ማስጃ እውነተኛ ወይም ትክክለኛ ነው ቢባል ውሳኔ ለመስጠት ተፈላጊ የሆነውን ፍሬ ነገር ወይም ጭብጥ በሚፈለገው ደረጃ ማስረዳቱን ወይም ማስተባበሉን ያጣራል፡፡ ስለዚህም "የቀረበው ማስረጃ በሚፈለገው ደረጃ አስረድቷል ወይስ አላስረዳም " ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ፍርድ ቤቱ የማስረጃ ምዘና ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡

የዚህ ፅሁፍ ዝግጅት ዋነኛ ትኩረትም ማስረጃዎችን በዓይነት ለይተዉ አዉቀዉ በሥራ ወቅት በወንጀልና በፍትሐብሔር ጉዳዮች የማስረጃ ምዘና ሲከናወን ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸውን መሠረታዊ ነጥቦችን በማንሳት የሰልጣኞችን ግንዛቤ በማስፋት ወደሥራ

በሚገቡበት ወቅት ሳይቸገሩ ኃላፊነታቸዉን እንዲወጡ ለማስቻል ነዉ፡፡ ሠልጣኞች ከቅርብ አሰልጣኞቻቸዉ ጋር በመሆን ብዙ ነጥቦችን በዉይይት እንደሚያዳብሩም ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሠረት ማስረጃ ሲመዘን ከቀረበው ማስረጃ፣ እና ከጉዳዩ ዓይነት አንፃር የማስረጃውን እውነተኛነት ወይም ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ምንምን ነገሮችን ግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚገባ፣ እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የአስረጅነት ደረጃ አንፃር የቀረበው ማስረጃ ተፈላጊውን ፍሬ ነገር አስረድቷል ለማለት የሚበቃው ምን ዓይነት መመዘኛዎችን ሲያሟላ እንደሆነ የፍርድ ቤት መዘግብትን እና ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ ይገለፃል፡፡

ዝግጅቱ በሦስት ክፍሎችና በዘጠኝ ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡ በክፍል አንድ ሥር የተካተቱት ሁለት ምዕራፎች (ምዕራፍ 1 እና 2) ማስረጃን በሚመለከት አጠቃላይ ግንዛቤ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ማስረጃ ምን ማለት አንደሆነ፣ ለምን እንደሚያስፈልግ፣ ዓይነቶቹን፣ በልዩ ሁኔታ ማስረጃ ማቅረብ የማያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች በአጭሩ ይገለፃሉ፡፡ በክፍል ሁለት ሥር የተካተቱት ሦስት ምዕራፎች( ከምዕራፍ 3-5 የማስረጃ አቀራረብን የሚመለከቱ ሲሆን ለፍርድ ቤት መቅረብ የሚችሉት ምን ዓይነት ማስረጃዎች እንደሆኑ፣ ማን እና እንዴት እንደሚያቀርባቸው፣ እንዲሁም ችሎት የቀረቡት ማስረጃዎች የገለፀት ፍሬ ነገር እንዴት እንደሚሰበሰብ መሠረታዊ ነጥቦች ይገለፀሉ፡፡ ሦስተኛውና የጽሁፉ አብይ ክፍል ማስረጃ መመዘንን የሚመለከት ሆኖ በዚህ ሥር ከተጠቃለሉ አራት ምዕራፎች በመጀመሪያው (ምዕራፍ 6 ሥር በወንጀልና በፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ያስረዳል ተብሎ የሚቀርብ ማስረጃ አስረድቷል ለማለት ማሟላት የሚጠበቅበት ተፈላጊው የአስረጅነት ደረጃ ምን እንደሆነ የሚገልፅ ሲሆን፤ በተከታዮቹ ሦስት ምዕራፎች ደግሞ በምዕራፍ 6 ላይ የተገለፀውን የአስረጅነት ደረጃ ማሟላት አለማሟላታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ዐይነት ማስረጆዎች እንዴት ሊመዘኑ እንደሚገባ እና ማስረጃዎቹ ሲመዘኑ ግምት ውስጥ መግባት የሚኖርባቸው ጉዳዮች ይገለፃሉ፡፡

በየክፍሉ ከተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች እና የፍርድ ጉዳዮች የተወሰዱ ጥያቄዎች የተካተቱ ሲሆን ዓላማቸውም የሥልጠናው ተካፋዮች እነዚህን ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ የቡድን ውይይት እንዲያደርጉና ልምድ እንዲለዋወጡ ማስቻል ነው፡፡

## አጠቃላይ የስልጠናው አላማ፣

የትምህርቱ ዓላማ የፍትህ ሥርዓቱን በዳኝነትን በዐቃቤ ህግነት ለሚያገለግሉ ባለሙያዎች በማስረጃ ህግ በቂ ግንዛቤና ተግባርን ያተኮረ ክህሎት ማዳበር በመሆኑ ስልጠናዉ ሲጠናቀቅ፡-

- ስለማስረጃ ሕግ ፅንሰ ሀሳብ በቂ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፤
- በወንጀልን በፍታብሔር ጉዳዮች የማስረጃን ተቀባይነት፣ አግባብነትና አቀራረብ በተመለከተ በቂ እዉቀት ያገኛሉ፤
- የተለያዩ ዓይነት ማሰረጃዎች በወንጀል እና በፍታብሔር ጉዳዮች እንዴት እንደሚመዘኑ ተገቢ ክህሎት ያዳብራሉ፣

## ዝርዝር ዓላማዎች

- የማስረጃ ዓይነቶችን፣ ልዩነቶችን እና አስፈላጊነትን ለይተዉ ይገልፃሉ፤
- ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ የሚሆንባቸዉን ጉዳዮች እና አስፈላጊ የማይሆንባቸዉን ጉዳዮች ለይተዉ ያዉቃሉ፣ ሥራ ላይ ያዉላሉ፤
- የተለያዩ የህግ ሥርዓቶች የሚከተሉ አገሮች ማስረጃ እንዴት እንደሚመዝኑ በቂ ግንዛቤ ይጨብጣሉ ከአገራችን አፈፃፀም ጋር ማዛመድ ይችላሉ፤
- በወንጀልም ሆነ በፍታብሔር ጉዳዮች ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ቢሆንም እንኳ መቅረብ የሚገባቸዉ አግባብነት እና ተቀባይነት ያላቸዉ ማስረጃዎች ብቻ መሆናቸዉን ምን ዓይነት ማስረጃዎች አግባብነት እንዳላቸዉ እና ለፍርድ ቤት እንዴት መቅረብ እንዳለባቸዉ ለይተዉ አዉቀዉ በተግባር ሥራ ላይ ማዋል ይችላሉ፤
- በወንጀልም ሆነ በፍታብሔር ጉዳዮች ማስረጃ ማን፣ መቼ እና እንዴት ማቅረብ እንደሚገባቸዉ ያዉቃሉ ተግባራዊ ልምምድ በማድረግ በዚሁ መሠረት መሥራት ይችላሉ፤

- የማስረጃ አስረጅነት መመዘኛዎችን እንዲሁም በፍታብሔርና በወንጀል ጉዳየች መካከላ ያለዉን የመመዘኛ ልዩነት ያዉቃሉ፤ ይህንን የሚመለከቱ መመዘኛ ጉዳዮችን በተግባር ሥራ ላይ ያዉላሉ፤
- በተለይ በወንጀልና በፍትብሔር ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ማስረጃዎች ሲመዘኑ ትኩረት ዉስጥ መግባት ስለሚያስፈልጋቸዉ መሠረታዊ መርሆዎች ያዉቃሉ፤
- በፍታብሔርም ሆነ በወንጀል ጉዳይ የቀረቡ ምስክሮችን የመመርመር ክህሎት ያዳብራሉ፤
- የተለያዩ ዓይነት ማስረጃዎችን በወንጀልም ሆነ በፍታብሄር ጉዳይ ሲቀርቡ መዝነዉ አሳማኝነታቸዉን በመለየት መጠቀም ይችላሉ፤

# ክፍል አንድ

# ስለማስረጃ አጠቃላይ ግንዛቤ

## ምዕራፍ 1

## የማስረጃ ጽንሰ ሐሳብ፣ አስፈላጊነትና ዓይነቶች

**ዝርዝር አላማዎች**

ሰልጣኞች ይህንን ምእራፍ ሲያጠናቅቁ ፣

- የማስረጃን ፅንሰ ሀሳብ ይረዳሉ፣
- የማስረጃ ዓይነቶችን የመለየት ጠቀሜታ ከህግ ሥርዓቶች ተሞክሮ አንፃር ጠንቅቀዉ ያዉቃሉ፤
- በአገራችን ያለዉን ተግባራዊ አፈፃፀም ፈትሸዉ አዉቀዉ በሥራ ላይ ተገቢዉን ጥንቃቄ ያደርጋሉ።

## *1.1. የማስረጃ ጽንሰ-ሐሳብ*

ዉድ ሰልጣኞች ማስረጃ ምንድነው? ማስረጃና መረጃ ልዩነት ይኖራቸዉ ይሁን? ለሚለው ጥያቄ የአገራችን ሕጐች ግልፅ መልስ አይሰጡም፡፡ በህጐቻችን ውስጥ የማስረጃ ጉዳይን የሚመለከቱ በርካታ ድንጋጌዎች ቢኖሩም፤ ማስረጃን ግን አይተረጉሙትም፡፡ ስለዚህም ማስረጃ ለሚለው ቃል ትርጉም ለመፈለግ ሌሎች ምንጮችን መመርመር ግዴታ ይሆናል፡፡

ከመዝገበ- ቃላት አንፃር ማስረጃ "ፍሬ ነገርን ወይም በጭብጥነት የተያዘን ጉዳይ መኖር ወይም አለመኖር አስመልክቶ ውሳኔ ሰጭውን ከፍል የማሳመን ውጤት ለመፍጠር ታቅዶ የሚቀርብ ማናቸውም ፍሬ ነገር ነው" የሚል ፍቺ ይሰጠዋል፡፡ በአገራችን ማስረጃን አስመልክቶ ከተፃፉ ጽሑፎች መካከል ዓላማየሁ ሐይሌ " የኤክስፐርት ማስረጃ በኢትዮጵያ ሕግ -በማነፃፀር የቀረበ" በሚል ጽሑፋቸው (ገፅ 56) ላይ ማስረጃን "ለፍርድ ቤት ግምት መሠረት በመሆን ውሳኔ ሊያሰጡ ከሚችሉት ከነዚህ ፍሬ ነገሮች በመነሳት ግምት የሚወሰድበት ነጥብ ላይ የሚደረስበት ሥርዓት ነው " ብለውታል፡፡ ከውጭ አገር ጸሐፊዎች ደግሞ (Richard May) " ማስረጃ ማንኛውም ፍሬ ነገርን ወይም መደምደሚያን ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል የሚጠቅም ነገር ነው፤ የክስ መሰማት ሒደትን በተመለከተም ማስረጃ ማለት በጭብጥ የተያዙትን ፍሬ ነገሮች ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል ተብሎ የሚቀርብ መረጃ ነው" ይሉታል፡፡

ስለዚህም ከነዚህ ለማስረጃ ከተሰጡ ፍቺዎች የምንረዳቸው ቁም ነገሮች፡-

- ✓ ማስረጃ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ መረጃ ሲሆን ይህ መረጃም ፍሬ ነገርን የሚመለከት ነው፡፡
- ✓ ይህንን ፍሬ ነገርን የሚመለከተው መረጃ ማስረጃ የሚያሰኘው በፍርድ ቤት በጭብጥ የተያዘን ፍሬ ነገር ወይም መደምደሚያ እውነተኛነት ወይም ትክክለኛነትነ ማረጋገጥ (Proving of fact in issue or conclusion) ወይም እውነተኛ ወይም ትክክለኛ አይደለም በሚል ለማስተባበል (Disproving any fact in issue or conclusion) የሚረዳ በመሆኑ ነው፡፡

በዚህም መሠረት ከማስረጃ ምንነት ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን ማስተዋል ተገቢ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍሬ ነገርን ወይም መደምደሚያን ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል የሚቀርብ ይሁን እንጂ ማስረጃ ራሱ ፍሬ ነገር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ማለት ማስረጃ  የፍሬ ነገርን መኖር ወይም መደምደሚያን ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል የሚቀርብ እንጂ የህግ ጉዳይን ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል የሚቀርብ አይደለም፡፡ ሕግን የሚመለከት ክርክር የተነሳ እንደሆነ ውሳኔ የሚያገኘው ሕጉን በመመርመር ነው እንጂ ማስረጃ በማቅረብ አይደለም፡፡ ማስረጃ የህግ ክርክርን ለማስረዳት የሚቀርብ አይደለም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ማስረጃን ለማስረዳት ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች መለየት ያስፈልጋል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ማስረጃ የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም የመደምደሚያን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ፍሬ ነገር ሲሆን በኋላ እንደሚገለፀው ይህንን ፍሬ ነገር ለፍርድ ቤት ለመግለፅ የምንጠቀምባቸው መንገዶች ወይም ዘዴዎች ምስክር አቅርቦ ማሰማት ወይም ሰነድ አቅርቦ ይዘቱን ማሳየት ወይም አንድ ዕቃ አቅርቦ ፍርድ ቤት ግንዛቤ እንዲወሰድበት ማድረግ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለፍርድ ቤቱ የተገለፀው ወይም ፍርድ ቤቱ አይቶ የተገነዘበው ፍሬ ነገር (ምስክሩ የተናገረው ቃል፣ ወይም የሰነዱ ይዘት ወይም መልዕክት፣ ወይም ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ዕቃ አይቶ የወሰደው ግንዛቤ) ማስረጃ (Evidence) ሲሆን ይህንን ማስረጃ ፍርድ ቤቱ እንዲያውቀው ለማድረግ የቀረቡት ምስክሮች፣ ሰነዶች ወይም ዕቃዎች... ወዘተ ደግሞ ዘዴዎች (Proof) ይባላሉ፡፡ በእንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ በህንድ  የማስረጃ ህጐችና ስለማስረጃ የተፃፉ ጽሑፎች ላይ ማስረጃን  (Evidence) ከዘዴው (Proof) ለይቶ መጠቀም የተለመደ ሲሆን የአገራችን ህጐችም ይህንን ልዩነት ግምት ውስጥ ያስገቡ የሚመስሉ ድንጋጌዎችን ይዘዋል፡፡ ለምሳሌ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት ቁጥር 147 ርዕስ " ማስረጃን በመዝገብ ስለመፃፍ "ይልና ዝርዝሩ ሲታይም ማስረጃ ተብሎ በመዝገቡ ውስጥ የሚፃፈው ምስክሮች የተናገሩት ቃል መሆኑን ይገልፃል፡፡ ሌሎችም በርካታ ልዩነቱን አመልካች የሆኑ ድንጋጌዎች ይኖራሉ፡፡ በፍርድ ቤቶችና በዐቃቤ ህግ መስሪያቤቶች ያለው ልማድ ሲታይ ግን "ማስረጃ" የሚለውን ቃል ፍሬ ነገሩንና የተጠቀምንበትን ዘዴ እንዲገልፅ በመለዋወጥ መጠቀም የተለመደ በመሆኑ

በዚህ ጽሑፍም በዚሁ በተለመደው መልክ በተለዋዋጭነት መጠቀሙ የሚቀጥል ሲሆን የትኛውን ሐሳብ ለማመልከት እንደተፈለገ ከቃሉ አገባብ በቀላሉ መለየት ይቻላል፡፡[1]

## 1.2. የማስረጃ ዓይነቶች

የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም የመደምደሚያን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል ከሚቻልባቸው ዘዴዎች እና ማስረዳት ከሚፈለገው ፍሬ ነገር ወይም መደምደሚያ ጋር ማስረጃው የሚኖረውን ግንኙነት መሠረት በማድረግ ማስረጃን በተለያዩ መንገዶች ክፋፍሎ መረዳት ይቻላል፡፡ ፍሬ ነገርን ለማስረዳት ከምንጠቀምበት ዘዴ አንፃር ማስረጃን የምስክርነት ማስረጃ (Testimonial Evidence) የሰነድ ማስረጃ (Document Evidence) እና ገላጭ ማስረጃ (Real or Demonstrative Evidence) በሚል ከፋፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡

እንዲሁም በማስረጃነት የሚገለፀው ፍሬ ነገር ሊያስረዳው ከተፈለገው ፍሬ ነገር ወይም መደምደሚያ ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር ማስረጃን ቀጥተኛ ማስረጃ (Direct Evidence) እና ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ (Indirect Evidence) በሚል ለያይቶ መመልከት ይቻላል፡፡

### 1.2.1. ማስረዳት ከሚቻልበቸው ዘዴዎች አንፃር የማስረጃ ዓይነቶች

#### ሀ. ምስክርነት

ምስክርነት ሰዎች በአካል ፍርድ ቤት ቀርበው ለችሎት መረጃ የሚሰጡበት መንገድ ሲሆን ፍሬ ነገሩን ለፍርድ ቤቱ የሚገልፁት በመሠረቱ በንግግር ነው፡፡ (እንደሁኔታው ግን ምስክሮች በምልክት ቋንቋ እየገለፁ በፍርድ ቤቱ በባለሙያ እየተተረጎመ ሊቀርብ ይችላል፡፡) እነዚህ ሰዎች የሚገልፁት ፍሬ ነገር በዚህ ፅሑፍ ውስጥ "የምስክር ቃል"

[1] አለማየሁ ኃይሌ ገፅ 56

በሚል የሚገለፅ ሲሆን ይህም ከንግግር በተጨማሪ በምልክት ወይም በድርጊት የተሰጠ የፍሬ ነገር መግለጫን ያጠቃለላል፡፡

ለ. <u>ሰነዶች</u>

የሰነድ ማስረጃ የሚባለው በላዩ ላይ የተፃፈበት፣ የተሳለበት ፣ ወይም ማናቸውም ዓይነት ምልክት የተደረገበት፣ ወይም ድምፅ የተቀዳበት ወይም ድምፅና ምስል የተቀረፀበት ሆኖ ይዘቱም ለአስረጅነት የሚቀርበው የተፃፈው ጽሑፍ፣ የተሳለው ስዕል፣ ወይም የተደረገው ምልክት ወይም  የተቀዳው  ወይም የቀረፀው ድምፅ ወይም ምሰል ወይም ማናቸውም ነገር ነው፡፡  በዚህም መሠረት በጽሑፍ የተገለፁ ነገሮች (ለምሳሌ ውሎች፣ ቼኮች፣  ለፖሊስ ወይም ለፍርድ ቤት የተሰጠ የዕምነት ቃል የተመዘገበበት፣ በጽሑፍ የተገለፀ የላቦራቶሪ ወይም የህክምና ምርመራ ውጤት የሰነድ ማስረጃ  ነው፡፡ እንዲሁም ስዕሎች፣ ቻርቶች፣ በድንጋይ ላይ የተቀረፁ ነገሮች፣ በቴፕና የቪዲዮ ካሴቶች፣  ዲስኮች፣ የተፈለገው ይዘታቸው እስከሆነ ድረስ  የሰነድ ማስረጃ ናቸው፡፡

ማስረጃውን የሰነድ ማስረጃ የሚያሰኘው ወረቀትነቱ፣ ወይም ካሴትነቱ ፎቶ ግራፍነቱ አለመሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ ሰነድ ያሰኘው ለማስረጃነት የተፈለገው ለፍርድ ቤት የሚቀርበውና ፍርድ ቤት የሚመለከተው ፍሬ ነገር በዚህ በወረቀት፣ ካሴት ወዘተ ላይ ሰፍሮ መገኘቱ ነው፡፡ ስለዚህ ለሰነድ ማስረጃነት ዋናው ነጥብ ማስረጃ የሚሆነው ፍሬ ነገር ( የተፃፈው ቃል፣ የተቀረፀው ምልክት፣ የተሳለው ስዕል፣  የተቀረፀው ድምፅ ወይምምስል) በወረቀቱ፣ በካሴቱ፣ በዕቃው....ወዘተ ሠፍሮ መገኘቱ ነው፡፡

ሐ. <u>ገላጭ ማስረጃዎች</u>

እነዚህ ፍርድ ቤት እንዲያያቸውና ግንዛቤ እንዲወሰድባቸው የሚቀርቡ ነገሮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረት፣ ወይም ወንጀል ለመፈፀም  አገልግሎት ላይ የዋለ መሳሪያ በማስረጃነት ሲቀርብ ገላጭ ማስረጃ ይባላል፡፡ አገልግሎቱም ፍርድ ቤቱ ተመልክቶት አንድ አይነት ግንዛቤ እንዲወስድ ማስቻል ነው፡፡ ተከሳሹ ግድያ ፈፀመበት የተባለው ቢላዋ በማስረጃነት ቢቀርብ ፍርድ ቤቱ ይህንን ተመልክቶ መሳሪያው የተባለውን ጉዳት ለማድረስ ብቃት እንዳለውና የተከሳሹን ቁርጠኝነት፡...ወዘተ

በሚመለከት ግምት ይወስድበታል፡፡ የተሰረቀ ዕቃ ፍርድ ቤቱ እንዲመለከተው ቢቀርብ የከሳሽ ዐቃቤ ሕግ ክስና ምስክሮች እንደሚገልፁት ዕቃው በአንድ ሰው ሸክም ከቦታ ቦታ ሊንቀሳቀስ መቻል አለመቻሉን በተመለከተ ግንዛቤ ለመውሰድ ይጠቅማል፡፡

***<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. አንድ ሰው ይዞታው በሆነው መሬት ላይ መተላለፊያ የመስጠት ግዴታ አለበት በሚል በሚቀርብ ክስ ላይ በእርግጥም ለከሳሹ በተከሳሹ ይዞታ ላይ የመተላለፊያ መንገድ አስፈላጊ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም በውሐ አጠቃቀም ምክንያት የሚቀርብ ክርክር በተመለከተ ልዩ ልዩ ጥቅሞችን በመጠበቅ ለመወሰን እንዲያስችል ዳኞች የክርክር መነሻ የሆኑትን መሬቶችና ውሐዎች ሁኔታ በአካል ተገኝተው ማየት ይችላሉ፡፡ በዚህ መንገድ የተገኘ ማስረጃ ከላይ ከተጠቀሱት የማስረጃ ዓይነቶች በየትኛው ውስጥ ይመደባል?
2. ከላይ በተገለፀው ዓይነት ማስረጃን ከፋፍሎ መረዳት ማስረጃን ከመመዘን አንፃር ምን ጥቅም ይሰጣል?

### 1.2.2. <u>ለማስረዳት ከተፈለገው ፍሬ ነገር ግንኙነት አንፃር የማስረጃ ዓይነቶች</u>

***ሀ. <u>ቀጥተኛ ማስረጃ</u>***

ማስረጃ ቀጥተኛ ነው የሚባለው አንድን በጭብጥ የተያዘ ፍሬ ነገር ወይም የተወሰደን መደምደሚያ ትክክለኛነት በቀጥታ ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል የሚቀርብ ሲሆን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ምስክር ቀርቦ በጭብጥ የተያዘው ፍሬ ነገር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ራሱ በስሜት ህዋሳቱ አማካኝነት በማየት፣ በማሽተት፣ በመቅመስ፣ በመስማት ወይም በመዳበስ ያወቀ መሆኑን የሚመሠክር ሲሆን ቀጥተኛ ማስረጃ ይባላል፡፡ ሰው ገድሏል በሚል ዐቃቤህግ ላቀረበው ክስ ምስክር ቀርቦ " ተኩሶ ሲገድል አይቻለሁ" በሚል የሚመሠክር ቢሆን፤ በንግግር ስም አጥፍተሃል በሚል በተከሳሽ ላይ ለቀረበ ክስ የቀረበ የከሳሽ ምስክር "ተከሳሹ የግል ተበዳይን ስም በማጥፋት ሲናገር ሰምቻለሁ" በሚል የሚመሠክር ቢሆን ቀጥተኛ ማስረጃ ይባላል፡፡

በሰነድ ማስረጃ በኩልም በማስረጃነት የቀረበው ሰነድ በጭብጥ የተያዘው ፍሬ ነገር መኖርን ወይም የተደረሰበት መደምደሚያ ትክክለኛ መሆኑን ሰነዱ ራሱ በቀጥታ ያረጋግጣል ወይም ያስተባብላል በሚል የቀረበ ከሆነ ቀጥተኛ ማስረጃ ይባላል፡፡ ለምሳሌ በቂ ስንቅ ሳይኖረው ቼክ ፈርሞ ሰጥቷል በሚል ገንዘብ እንዲከፍል በተከሳሽ ላይ ለቀረበ ክስ ከሳሽ ቼኩን በማስረጃነት ያቀረበ ቢሆን ተከሳሹ ስለመፈረም አለመፈረሙ እና ስለገንዘቡ ልክ ቼኩ በቀጥታ የሚናገር ስለሆነ ቀጥተኛ ማስረጃ ይባላል፡፡ ቼኩ ሳይሆን "ተከሳሹ ቼክ መፈረሙን እናረጋግጣለን" የሚል ሌላ ሰነድ ቢቀርብ ግን ቀጥተኛ ማስረጃ አይደለም፡፡

ለ. <u>ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ</u>

ማስረጃ ቀጥተኛ ያልሆነ ነው የሚባለው ከሁለት ሁኔታዎች አንፃር ነው፡፡ አንደኛው ማስረጃ ያስረዳል የተባለውን ፍሬ ነገር ምንጩ ማስረጃው ራሱ በቀጥታ ያወቀው ሳይሆን ከሌላ ያገኘው ወይም የተረዳው ሲሆን ነው፡፡ ምስክር ይመሠክረዋል የተባለውን ፍሬ ነገር ራሱ በቀጥታ በስሜት ህዋሳቱ የተረዳው ሳይሆን ሌላ ሰው የገለፀለት መሆኑን ጠቅሶ የሚመሠክር ሲሆን ቀጥተኛ ሳይሆን የሰሚ ሰሚ ማስረጃ (Hearsay Evidence) ይባላል፡፡ ከላይ በቂ ስንቅ ሳይኖረው ቼክ ሰጠ በሚል በቀረበው ምሳሌ ላይ እንደተመለከተው ተከሳሹ ቼክ መፈረሙን እና የገንዘቡን መጠን የሚናገረው ቼኩ ራሱ ሳይሆን ስለዚህ ይገልፃል በሚል የቀረበ ሌላ ጽሑፈ ቢሆን ሰነዱ ቀጥተኛ ሳይሆን በሰነድ የተገለፀ የሰሚ ሰሚ ማስረጃ (Documentary Hearsay Evidence) ነው የሚባለው፡፡ የሰሚ ሰሚ ማስረጃን ቀጥተኛ ያልሆነ የሚያሰኘው ማስረጃው ፍሬ ነገሩን የሚገልፀው ራሱ በቀጥታ እንዳወቀው ሳይሆን ከሌላ ሰው የሰማው ወይም ከሰነድ ያነበበው በመሆኑ ነው፡፡ በሰነድ ማስረጃም በኩል የሰሚ ሰሚ የሚያሰኘው ማስረጃ ሆኖ የቀረበው ሰነድ ላይ የተገለፀው ፍሬ ነገር ስለዚህ ፍሬ ነገር አውቃለሁ በሚል ሌላ ሰው የተዘጋጀ መሆኑ ነው፡፡

ሁለተኛው ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ ነው የሚባልበት ሁኔታ የሚያጋጥመው አከባቢያዊ ማስረጃ (Circumstantial Evidence) የቀረበ እንደሆነ ነው፡፡ አከባቢያዊ ማስረጃ በጭብጥ ስለተያዘው ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር በቀጥታ አይነግረንም፡፡

ይልቁንም የተወሰኑ ፍሬ ነገሮችን መኖር ወይም አለመኖር በማረጋገጥ ከዚህ ተነስተን በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር በተመለከተ አንድ አይነት መደምደሚያ ላይ እንድንደርስ የሚያደርግ ነው። ጠመንጃ ተኩሶ ሰው ገድሏል በሚል ዐቃቤ ህግ ላቀረበው ክስ የቀረቡት ማስረጃዎች የሚገልፁት ተከሳሹ ተኩሶ ስለመግደሉ ሳይሆን ተከሳሹ ከሟች ጋር ፀብ እንደነበረው፣ ሟች ከመሞቱ ጥቂት ጊዜ አስቀድሞ ተከሳሹ ከብት ሸጦ ጠመንጃ እንደገዛ፣ ሟች ተገደለ ከተባለ በኋላ ተከሳሹ ከአካባቢው ተሰውሮ ቆይቶ በፖሊስ ክትትል መያዙን ቢሆን ስለዋናው ክስ ጉዳይ በቀጥታ አይናገሩም ። ስለአከባቢያዊው ሁኔታ ይናገራሉ። እነዚህ ማስረጃዎች ከራሳቸው ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን ውሳኔ ስለሚሰጥባቸው ፍሬ ነገሮች መኖር ወይም አለመኖር አንድ ዓይነት ግምት ለመውሰድ ያስችላሉ። ለማጠቃለል አካባቢያዊ ማስረጃን ቀጥተኛ ያልሆነ የሚያሰኘው በማስረጃነት የተገለፀው ፍሬ ነገር በጭብጥ ስለተያዘው ፍሬ ነገር በቀጥታ የሚናገር ወይም የሚገልፅ ሳይሆን ሌሎች ፍሬ ነገሮችን በመግለፅ በጭብጥ ስለተያዘው ፍሬ ነገር ግምት እንዲወሰድ የሚያደርግ መሆኑ ነው።

ማስረጃን ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ በሚል ከፋፍሎ ማየት ለምን አስፈለገ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። የአንግሎ አሜሪካ የህግ ስርዓት ተከታይ በሆኑ አገሮች በልዩ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የሰሚ ሰሚ ማስረጃ (ምስክርም ይሁን ሰነድ) ተቀባይነት የለውም። ከኢትዮጵያ ህግ አንፃር ሲታይ ግን በማስረጃነት ሊቀርብ ይችላል። የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነሥርዓት ቁጥር 137(1) እና የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ. ቁጥር 263(1) እንደሚያመለክቱት የሰሚ ሰሚ ማስረጃ በማስረጀነት ሊቀርብ ይችላል።

> የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርአት ሕግ ቁጥር 137(1) ‹በዋናው ጥያቄ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ውሳኔ ስለሚሰጥበት ፍሬነገር ተገቢ የሆኑትንና በቀጥታም ሆኖ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ምስክሩ ስለሚያውቃቸው ፍሬነገሮች ብቻ ነው።›
>
> Questions put in examination-in-chief shall only relate to facts relevant to the issues to be decided and to such facts only of which the witness has direct or indirect knowledge.
>
> የፍትሀብሄር ስነስርአት ህግ ቁጥር 263(1) ‹ምስክሩ የመጀመሪያ ቃሉን ሲሰጥ የሚቀርብለት ጥያቄ ጭብጡን የሚመለከትና በቀጥታ ወይም በሌላ መንገድ

በሚያውቀው ወይም ሊያውቀው በሚችለው ነገር ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡›

Questions put in examiniation-in-chief shall only relate to facts relevant to the issues to be decided and only to such facts of which the witness has direct or indirect knowledge.

ነገር ግን የማስረጃ ምዘና በሚከናወንበት ጊዜ የማስረጃው ዓይነት ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ማስረጃ ሲመዘን በመስቀለኛ ጥያቄ “ትክክለኛነቱ፣ አጣራጣሪነቱ፣ እውነትነቱ”(የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 263(3)) የሚፈተሽ በመሆኑ ይህ የመመዘን ተግባር ሲከናወን የማስረጃው ቀጥተኛ ወይም የሰሚ ሰሚ መሆን ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡ እንዲሁም ማስረጃ ሲመዘን ትክክለኛነቱ፣ አጠራጣሪነቱ እና እውነተኛነቱ ብቻ ሳይሆን ማስረጃው እውነተኛ፣ ትክክለኛቱ፣ እርግጠኛ ቢሆን እንኳን በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር መኖር ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል ያለው ብቃት (ማለትም እውነት ቢሆንስ ለማስረዳት ይበቃልን የሚለው ) የሚመረመር በመሆኑ የማስረጃው ቀጥተኛ ወይም አከባቢያዊ መሆኑ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ማስረጃው ቀጥተኛ ወይም አከባቢያዊ መሆን አለመሆኑን መለየት በማስረጃ ምዘና ጊዜ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

***<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>***

ከዚህ በታች ከተገለፁት ውስጥ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑትን በመለየት ከነምክንያቱ ጭምር ግለፅ፡፡ ከህግ አንፃር የሚወሰደው መደምደሚያስ ምንድነው ?

ሀ. ልጅነትን ለማረጋገጥ ለቀረበ የፍትሐብሔር ክስ ከህፃኑ የተወሰደው የደም ናሙና DNA አባት ነህ በማለት ክስ ከቀረበበት ሰው ከተወሰደ የደም ናሙና DNA ጋር ተመሳሳይ መሆኑን የሚገልፅ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት መግለፅ /በፅሁፍ የቀረበ/

ለ. በስም ማጥፋት ወንጀል የተከሰሰው ተከሳሽ ስም አጠፋ ተብሎ ክስ ያቀረበበት ንግግር ተጠቅሶ በጋዜጣ የወጣ የዜና ዘገባ፡፡ ተከሳሹ ራሱ የጋዜጣው አዘጋጅ መሆኑ በማስረጀው ዓይነት ላይ ልዩነት ያመጣል?

# ምዕራፍ 2

# ማስረጃ ስለማያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች

**ዝርዝር አላማዎች**

ሰልጣኞች ይህንን ምእራፍ ሲያጠናቅቁ ፣

- በወንጀል ጉዳዮችም ሆነ በፍታብሔር ጉዳዮች ማስረጃ ስለማያስፈልጋቸዉ ነገሮች ለይተዉ አዉቀዉ በመተግበር ጊዜን፣ ገንዘብንና ጉልበትን እንዲቆጠብ ያደርጋሉ፡፡
- በፍርድ ቤት እና ከፍርድ ቤት ዉጭ ስለሚሰጡት የእምነት ቃሎች ተቀባይነት በቂ ግንዛቤ ያዳብራሉ ሥራ ላይ በሚያዉሉበት ወቅት ተገቢዉን ስልት ይጠቀማሉ፡፡

## 2.1 *ጠቅላላ*

ዉድ ሠልጣኞች ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ማንኛውም የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም የአንድን መደምደሚያ ትክክለኛነት በመግለፅ ወይም በማስተባበል የሚከራከር ሰው ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት እንደሚገባው ተመልክቷል፡፡ በክርክር ሂደት ማስረጃ የማያስፈልግ ጉዳይ ሊኖር ይችላል ብላችሁ ገምታችሁ ታዉቃላችሁ? እስቲ በምን በምን ሁኔታ ማስረጃ ሳያስፈልግ መወሰን ይቻላል ትላላችሁ? በመሠረታዊነት የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ማረጋገጥ የሚቻለዉ ማስረጃ በማቅረብ ነዉ፡፡ ነገር ግን ይህ መሠረታዊ መርህ የማይመለከታቸው ልዩ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ማለት ከፍሬ ነገሮቹ የተለየ ባህሪይ ወይም የሚያከራክር ነገር ባለመኖሩ ምክንያት ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ የማይሆንባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነዚህም

- ❖ ፍርድ ቤት ግንዛቤ ሊወሰድባቸው የሚችሉ ወይም የሚገቡ ፍሬ ነገሮች፤ እንዲሁም
- ❖ በፍርድ ቤት በሚደረግ የክርክር ሒደት በተከራካሪ ወገን የታመኑ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡

እነዚህን ሁኔታዎች በቅድሚያ መረዳት የተያዘውን ጉዳይ በአግባቡ ለመወሰን አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ማስረጃ መቀበል ሳያስፈልገው ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢ የሆነውን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ግንዛቤ ሊወስድበት የሚገባ ነው፤ ወይም የታመነ ነው የሚል አቋም መውሰድ እንዲችል ማድረግ ያስፈለገውም በተለያዩ ምክንያቶች

ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በታወቀ ፍሬ ነገር ወይም አከራካሪ ያልሆኑ ማረጋገጫዎች በመመልከት መወሰን በሚቻል ፍሬ ነገር ላይ ማስረጃ መቀበሉ ትርጉም ስለማይኖረው ነው፡፡ በይፋ የታወቀ ወይም አከራካሪ ያልሆነ ማረጋገጫን መሠረት በማድረግ በቀላሉ ሊረጋገጥ የሚችል ሆኖ እያለ ተከራካሪዎች ግን ሊካካዱበት ይችላሉ፡፡ ይህንን መከልከል አይቻልም፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ራሱ ግንዛቤ ሊወስድበት የሚችል ወይም የታመኑ ምንጮችን መሠረት በማድረግ መደምደሚያ ላይ መድረስ እየቻለ ተከራካሪ ወገኖችን ማስረጃ አቅርቡ ማለት ጊዜና ገንዘብ ከማባከን ሌላ የሚጨምረው ነገር የለም፡፡ እንዲሁም የፍሬ ነገሩ መኖር ወይም አለመኖር ወይም የመደምደሚያው ትክክለኛነት በችሎት በተደረገ ክርክር ወይም መግለጫ የታመነ በሆነበት ሁኔታ ማስረጃ መቀበል የሚሰጠው አገልግሎት የለም፡፡ ማስረጃ የሚቀርበው ተከራካሪ ወገኖች በተካካዱበት እና ጭብጥ ብለን የምንጠራው በተያዘበት ሁኔታ መሆኑ እየታወቀ ፍሬ ነገሩ ባልተካደበት፤ ጭብጥ ባለተያዘበት ማስረጃ ቢቀርብም የሚያስረዳው ነገር የለም፡፡ ከወጭና ጊዜን ከማባከን ውጭ የሚሰጠው ጥቅም የለም፡፡

በዚህ ምዕራፍ የሚገለፁትም እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን ወደዝርዝር ውስጥ ከመግባት አስቀድሞ በአብዛኛው የቀድሞ የማስረጃ ሕግ ጽሑፎች ላይ 3ኛው አይነት ማስረጃ ማቅረብ የማያስፈልገው ፍሬ ነገር ስለሚባለውና በሕግ ግምት (Presumption) ላይ መጠነኛ መግለጫ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ አንድ ፍሬ ነገር በህግ ግምት እንዲረጋገጥ ህግ በደነገገ ጊዜ ይህ ፍሬ ነገር ህግ በሚወስነው ግምት መሠረት እንደሚረጋገጥ ይታወቃል፡፡ በዚህም መሠረት፣

- ❖ ከአንድ ከተረጋገጠ ፍሬ ነገር (Basic Fact) በመነሳት ሌላ ፍሬ ነገርን ወይም መደምደሚያን (Presumed fact) ትክክለኛነት መገመት እንደሚገባ፤ነገር ግን ይህ ግምት መውሰዱ የሚጐዳው ሰው ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል እንደሚችል ህግ ሊደነግግ የችላል፡፡ ይህም ሊስተባበል የሚችል የህግ ግምት (Rebutable presumption) ይባላል፡፡
- ❖ እንዲሁም ከአንድ ከተረጋገጠ ፍሬ ነገር (basic fact) በመነሳቱ ሌላ ፍሬ ነገርን ወይም መደምደሚያን (presumed fact) ትክክለኛነት መገመት እንደሚገባና ይህንን ህግ የወሰደውን ግምት ግን ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል እንደማይቻል

ህግ ሊደነገግ ይችላል፡፡ ይህም ሊስተባብል የማይችል የህግ ግምት (irrebutable or conclusive presumption) ይባላል፡፡

ግምት የሚወስድበት ፍሬ ነገር በጥልቀት ከታየ ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ያልሆነበት ሁኔታ አለ ለማለት አይቻልም፡፡ በርግጥ ማስረጃው የሚቀርበው ግምት የሚወሰድበትን ፍሬ ነገር መኖር ወይም መደምደሚያ ትክክለኘነት ለማረጋገጥ አይደለም፡፡ ነገር ግን ለህግ ግምት መሠረት የሚሆነውን ፍሬ ነገር (Basic Fact) ለማስረዳት ማስረጃ ሊቀርብበት የሚገባ ነው፡፡ ለምሳሌ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3(1) "የልጅ መፀነስ ጊዜ የሚቆጠረው ልጁ ከተወለደበት  በፊት ካለው ከሦስት መቶኛው ቀን ወዲህ ነው፡፡" ይላል፡፡ በዚህም መሠረት ልጁ የተፀነሰበትን ቀን ለመወሰን የሚቻለው ልጁ የተወለደበትን ቀን ለማስረዳት ከሚቀርበው ማስረጃ በሚወሰድ ግምት ነው፡፡ ልጁ የተወለደበትን ቀን የሚያስረዳ ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ልጁ  የተፀነሰበትን ጊዜ ለመገመት መሠረት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ምንም  እንኳን ልጅ የተፀነሰበትን ቀን ለማስረዳት ማስረጃ ባይቀርብም የተወለደበትን ቀን ለማስረዳት ግን ማስረጃ መቅረቡ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ግምት የሚወሰድበት ፍሬ ነገር መኖርን ለመገመት መንደርደሪያ የሆነውን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ማስረጃ የሚቀርብ በመሆኑ፤ ይህ ግምት የሚወሰድበት ፍሬ ነገር በራሱ ብቻውን ሊቆም የማይችል በመሆኑ "ማስረጃ ሳያስፈልገው ስለሚረጋገጥ ፍሬ ነገር" በሚል በተጠቀሰው በዚህ ምዕራፍ ጉልህ ስፍራ የሚሰጠው አይደለም፡፡ በዚህም መሠረት ቀጥሎ በፍርድ ቤት ግንዛቤ ስለሚወሰድባቸው፤ እና ስለታመኑ ፍሬ ነገሮች ይገለፃል፡፡

<u>***መወያያ ጥያቄዎች***</u>

በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 184 ላይ የሚከተለው ተደንግጉአል፡፡

1. አንድ ሰው ደንበኛ የመኖሪያ ስፍራው አንድ በሆነ ጊዜ በዚሁ ስፍራ በነዋሪ አኳኋን ለመኖር አሳብ እንዳለው ይገመታል፡፡
2. ይህ የተባለው ሰው የገለፀው ተቃራኒ ሐሳብ ቢኖር አሳቡ በቂ በሆነ አነጋገር የተለየ ካልሆነና ውጤትም የሚኖረው እንደነገሩ ደንበኛ ሁኔታ ወደፊት ለመድረስ የሚችል አንድ ሁኔታ ከደረሰ በኋላ የሚሆን ካልሆነ በቀር በደንበኛው

የነገሮቹ መንገድ ወደ ፍፃሜ ደርሶ መታየት ያለበት ተቃራኒው አሳብ ከቁም ነገር አይቆጠርም፡፡

በዚህ መሠረት

ሀ. ማስረጃ ሊቀርብበት የሚገባው ፍሬ ነገር የትኛው ነው?

ለ. ግምት የሚወስድበት ፍሬ ነገር የትኛው ነው?

ሐ. ግምቱን ለማስተባበል ተገቢ የሆነው ፍሬ ነገር የትኛው ነው?

መ. ግምቱን ለማስተባበል የሚቀርበው ማስረጃ እስከምን ደረጃ ማስረዳት ይገባዋል?

ሠ. ግምቱን ለማስተባበል ተገቢነት የሌለው ፍሬ ነገር የትኛው ነው?

## 2.2 ግንዛቤ ስለሚወሰድባቸው ፍሬ ነገሮች

አንድ ፍሬ ነገር በፍርድ ቤት ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚችለውና ማስረጃ ማቅረብ አስፈለጊ አይደለም የሚባለው ፍሬ ነገሩ በስፋት የታወቀ (Common Knowledge) በመሆኑ ወይም ተቀባይነት ያላቸው ምንጮችን በማየት (Reference form authoritative sources) ሊረጋገጥ የሚችል ሲሆን ነው (May, p.25)፡፡ የአንዳንድ ፍሬ ነገሮች መኖር ወይም አለመኖር ክርክር የሚያስነሳ፣ በስፋት የሚታወቁ በመሆናቸውም የተነሳ ዳኞች ግንዛቤ የሚወስዱባቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ “አዲስ አበባ የኢትዮጲያ ዋና ከተማ ነው” ፤ “አንበሳ የዱር አራዊት ነው” … የሚሉት በኢትዮጵያ ውስጥ ክርክር የማያስነሱ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ፍሬ ነገሮች መረጋገጥ ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ፍርድ ቤቱ በራሱ ሊቀበላቸው ይገባል፡፡ ያም ሆኖ ግን ዳኞች ክርክር የማያስነሳ በሚገባ የሚታወቅ ነው በማለት የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልግም የሚል አቋም ሊወስዱ የሚችሉት የራሳቸውን ዕውቀት መሠረተ በማድረግ ሳይሆን በአካባቢው ህበረተሰብ ዘንድ በሚገባ መታወቅን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በተጨማሪም አንዳንድ ፍሬ ነገሮች በስፋት የሚታወቁ ባይሆኑም እንኳን የነዚህን ፍሬ ነገሮች መኖር ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ተቀባይነት ያላቸውን አስገዳጅ ምንጮች (Authoritative Sources) በመመልከት ውሳኔ ላይ መድረስ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በቂ ስንቅ ሳይኖር ቼክ ፈርሞ ስለሰጠ በቼኩ ላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል የሚል ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ለቀረበው ክስ ተከሳሹ " ክሱ የቀረበው ለክስ ማቅረቢያ በህግ የተወሰነው ጊዜ  አንድ ቀን ካለፈው በኋላ በመሆኑ በይርጋ የታገደ ነው" በሚል መቃወሚያ ቢያቀርብና ከሳሹ በበኩሉ ክሱ ፍርድ ቤት ከቀረበበት ቀን በፊት ያለው ቀን የህዝብ በዓል ቀን በመሆኑ ሊቆጠርበት እንደማይገባ ቢገልፅ " ክስ  ከቀረበበት ቀን በፊት ያለው ቀን የህዝብ በዓል ቀን ነው ወይስ አይደለም" የሚለው ጭብጥ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ሲሆን ይህንን ለማረጋገጥ ግን ፍርድ ቤቱ ከሳሹን ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊያስገድድው አይገባም፡፡ ይህንን

- ተቀባይነት ያለውን የቀን መቁጠሪያ በመመልከት፣ ወይም
- ስለህዝብ በዓላት ቀናት የወጡትን አዋጆች

በመመልከት መወሰን አለበት፡፡

ማስረጃ መቀበል ሳያስፈልግ  ግንዛቤ ሊወሰድባቸው ስለሚገቡ ፍሬ ነገሮች በህግ በግልፅ የተደነገገባቸው ሁኔታዎችም አሉ፡፡ ለምሳሌ በ1934 ዓ.ም በቁጥር 1 የወጣው የነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ማናቸውም  አዋጅ፣ ድንጋጌ፣ ህግ፣ ደንብ፣ ውሳኔ፣ ትዕዛዝ፣ ማስታወቂያ በማናቸውም  የመንግስት ሥራ ላይ የተሾመ ሹም ስም፣ ስራና ፊርማ  በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የወጣ እንደሆነ ማናቸውም ፍርድ ቤት ሊቀበለው እንደሚገባ ተደገግጓል፡፡ በ1987 ዓ.ም የወጣው የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 3/1987  እንደዚሁ በተመሳሳይ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ላይ የወጡ ነገሮችን ፍርድ ቤቶች ሊቀበሉዋቸው እንደሚገባ ተደንግጓአል፡፡ ስለዚህም የክርክር መነሻ የሆነው ፍሬ ነገር በነጋሪት ጋዜጣ  ላይ መውጣት አለመውጣቱን ነጋሪት ጋዜጣውን በመመልከት ማረጋገጥ እንደሚገባ ሁሉ፤ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ የተገለፀ ፍሬ ነገር ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ሌላ ማስረጃ መቀበል አያስፈልግም፡፡ ጋዜጣውን በመመልከት ብቻ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

<u>*መወያያ ጥያቄዎች*</u>

የመተጫጨት ውሉን ያለበቂ ምክንያት ስላፈረሰች በአገሩ ባህል መሠረት ለጥሎሽ በሽማግሌ በኩል የተቀበለችውን ብር 5000 ትክፈለኝ በሚል ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ለአቀረበው ክስ ተከሳሽዋ  በሰጠችው መልስ ከሳሽ ገንዘቡን ለሽማግሌዎች የሰጠ ቢሆንም የማታወቀውና ያልደረሳት በመሆኑ ልትከፍለው እንደማትችል ገልፃ ተከራክራለች፡፡ በዚህ ጉዳይ ተከሳሽ ሽማግሌዎችም መቀባላቸውን እስካልካደች ድረስ በአገር ልማድ በግልፅ እንደሚታወቀው ጥሎሽ የተቀበለው ሽማግሌ ገንዘቡን ጥሎሽ ለሚገባው ሰው የሚሰጥ በመሆኑ ሽማግሌዎቹ ጥሎሹን ለተከሳሽ መስጠታቸውን ለማስረዳት ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ትክፈል በሚል መወሰን ይቻላልን? (ከጠቅላይ ፍርድ ቤት የወ.ይ.መ.ቁጥር 274/79 በላይ በማስተካከል የተወሰደ፡፡)

## 2.3 *<u>በችሎት ስለታመኑ ፍሬ ነገሮች</u>*

### 2.3.1 <u>ጽንሰ ሐሳቡ</u>

አንድ ፍሬ ነገር መኖሩ ወይም አለመኖሩ ታምኗል የሚባለው በተከራካሪ ወገኖች በአንደኛው  ስለዚህ ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር የተገለፀውን ሌላኛው ወገን አምኖ ሲቀበለው ወይም ስምምነቱን ሲገልፅ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የታመነውን ፍሬ ነገር በተመለከተ የታመነለት ሰው ማስረጃው አድርጐ እንዲጠቀምበት፣  ወይም ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ተደርጐ እንዲወሰድ የማድረግ ውጤት አለው፡፡

የዕምነት ቃል አሰጣጡን በተመለከተም ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ማለትም ከፍ/ቤት ውጭ የተሰጠና የማስረጃነት ዋጋ ያለው (Evidentiary Admission) ወይም ከፍ/ቤት ከተጀመረ ክርክር ሒደት ማለትም በፍርድ ቤት  ውስጥ የተሰጠ የዕምነት ቃል (Judicial Admission)ሊሆን ይችላል፡፡

ከፍርድ ቤት ውጭ የተሰጡ የዕምነት ቃሎች ፍሬ ነገርን ለማስረዳት በማስረጃነት ሊቀርቡ የሚችሉ ናቸው ፡፡ (የማስረጃ ተቀባይነትን የሚመለከቱ ደንቦችን እስከ አሟሉ ድረስ ማለት ነው፡፡) ከነዚህም መካከል

- ❖ በወንጀል ጉዳይ የወንጀሉ ድርጊት መፈፀሙን በማመን በተከሳሹ ለመርማሪ ፖሊስ ወይም ለምርመራ ቃል ተቀባይ ፍርድ ቤት የሚሰጡ የዕምነት ቃሎች፣
- ❖ በፍትሐብሔር ጉዳይ ዕዳን በማመን ከፍርድ ቤት ውጭ የተሰጡ መተማመኛዎች ተጠቃሽ ሲሆኑ እነዚህም በማስረጃነት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን አምኖአል የተባለው ሰው ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል ይችላል፡፡

በፍርድ ቤት ውስጥ የተሰጡ የዕምነት ቃሎች የተለያዩ ዓይነት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ያህልም፡-

- ❖ በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ፍርድ ቤት የቀረበ ተከሳሽ ክሱ ተነብቦለት ከተረዳው በኃላ የዕምነት ክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወንጀሉን በማመን የሚሰጠው የዕምነት ቃል፤
- ❖ በፍትሐብሔር ጉዳይ የተከሰሰው ሰው ለፍርድ ቤት በሰጠው መልስ፣ ወይም በክርክሩ ሒደት በቃል፣ በጽሑፍ የሰጠው የዕምነት ቃል ፤ በጽሁፍ የሰጠው የዕምነት ቃል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በፍርድ ቤት ውስጥ የተደረገ የማመን ቃል እንደሁኔታው የማስረጃነት ወይንም ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ እንደተረጋገጠ ፍሬ ነገር የመወሰድ ውጤት ያስከትላል፡፡

ከላይ ከተመለከተው መረዳት የሚቻለው ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈለግ ፍሬ ነገሩ የተረጋገጠ ተደርጐ እንዲወሰድ የማስደረግ ውጤት ሊኖረው የሚችለው በፍርድ ቤት ውስጥ የተደረገ ማመን ነው፡፡ ከፍርድ ቤት ውጪ የተደረገ ዕምነት ግን በማስረጃነት የሚቀርብና ማስተባበያ ማስረጃም ሊቀርብበት የሚችል በመሆኑ "ማስረጃ የማያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች" በሚለው በዚህ ምዕራፍ ሥር የሚሸፈን አይደለም፡፡ በዚህ ምዕራፍ የሚታየው በፍርድ ቤት የተደረገ የእምነት ቃል ሲሆን በፍትሐብሔር እና በወንጀል ጉዳዮች የተለያየ አፈፃፀም ስለአለው ለያይቶ መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.3.2. <u>በወንጀል ጉደይ በችሎት የታመኑ ፍሬ ነገሮች</u>

በወንጀል ጉዳይ በፍርድ ቤት የታመኑ ፍሬ ነገሮች ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ የተረጋገጡ ተደርገው የሚወሰዱበት ዕድል በጣም ጠባብ ነው፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 134 ላይ እንደተመለከተው እንደተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ተደረገው

የሚወሰዱት "ተከሳሹ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ ያመነ" እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በወንጀል ጉዳይ

- ❖ የዕምነት ቃል ሰጠ የሚባለው ተከሳሹ ራሱ ነው፡፡ እንደፍትሐብሔር ጉዳይ ከሳሹ (ተከሳሹ በመልስ ላይ የገለፀውን ከሳሽ ሊያምን ይችላል) ወይም ጠበቃ ሞግዚቱ፣ እንደራሴው፣....ወዘተ ስለተከሳሽ ሆነው የዕምነት ቃል ሊሰጡ አይችሉም፡፡
- ❖ ተከሳሹም ቢሆን በመሠረቱ አመነ ለመባል " በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ ያመነ" መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ እንደፍትሐብሔር ጉዳይ በዝምታ፣ ወይም በግልፅ እና በዝርዝር ባለማስተባበል መነሻ አምኖአል አይባልም (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነሥርዓት ቁጥር 133-134 ድንጋጌን ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 73(1)፣ 83 ፣ 234፣ 235 ፣241 ጋር አገናዝብ)፡፡
- ❖ ተከሳሹ ራሱ "በክሱ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ ያመነ" ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ "አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ዐቃቤ ሕጉ ለክሱ የሚደግፈውን ማስረጃ እንዲያቀርብ ለማዝዝና ተከሳሹም የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያቀርብ ለመፍቀድ ይችላል፡፡ " (የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 134(2))

ሆኖም ቃሉ የዕምነት ቃል የሚለውን የአሟላ ሆኖ ከተገኘና ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ ህግንና የመከላከያ ማስረጃን መቀበል አስፈላጊ ሆኖ ባላገኘው ጊዜ የታመነው ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ ተቆጥሮ የጥፋተኛነት ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ይህም ማለት፡፡

- ❖ ፍሬ ነገሩን ለማስረዳት ማስረጃ ማቅረብን አላስፈላጊ ያደርገዋል፤ ስለዚህም ዐቃቤ ህጉም ሆነ ተከሳሹ ማስረጃ አያቀርቡም፤
- ❖ በቅጣቱ ላይ ካልሆነ በስተቀር ጥፋተኝነትን ባቋቋሙት ፍሬ ነገሮች ላይ ይግባኝ መጠየቅ አይፈቀድም (በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 185(1))፡፡

### 2.3.3. <u>በፍትሐብሔር ጉዳይ በችሎት የታመኑ ፍሬ ነገሮች፣</u>

በፍርድ ቤት ውስጥ በችሎት የታመኑ ፍሬ ነገሮች ማስረጃ ሳያስፈልጋቸው ውሳኔ ለማሰጠት የሚችሉት በዋነኛነት በፍትሐብሔር ጉዳዮች ነው፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳይ በችሎት የተሰጡ ናቸው የሚባሉት የዕምነት ቃሎች፡-ተከራካሪ ወገኖች

የሚያቀርቡአቸው የአቤቱታ ጽሑፎች፣ እንዲሁም እነዚህ ወገኖች በፍርድ ቤት ለሚደረግ የቃል ክርክር በሚሰጡዋቸው መልሶች ሊገለፁ ይችላሉ፡፡ በዚህ መንገድ የተሰጡትን ቃሎች የዕምነት ቃል የሚያደርጋቸው፡፡

- ❖ ተከራካሪ ወገኖች ወይም ወኪሎቻቸው በግልፅ ማመናቸው፣
- ❖ በዝምታ ማለፋቸው ፣ ወይም
- ❖ በአነጋገር ወይም በአገላለፅ ዘይቤ ማመናቸው ተደርጐ እንዲወሰድ ማድረጋቸው ሊሆን ይችላል (የፍትሐብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 73(1)፣ 83፣234፣235፣241….)፡፡

በተጨማሪም የፍትሐብሔር ጉዳይ እንደወንጀል ጉዳይ በሙሉ ማመንን በግዴታ የሚጠይቅ አይደለም፡፡ በዚህም መሠረት የዕምነት ቃሉ፣

- ❖ በግልፅም፣ በዝምታ፣ ወይም በአነጋገር ዘይቤ በሙሉ የታመነ በመሆኑ የታመነውፍሬ ነገር በሙሉ ማስረጃ ማቅረብ የማያስፈልገው፤ ወይም
- ❖ በግልፅም በዝምታ ወይም በአነጋገር ዘይቤ በከፊል የታመነ ሆኖ የታመነው ክፍል ብቻ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ውሳኔ ሊያሰጥ የሚያስችል ሊሆን ይችላል፡፡

***<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>***

በወንጀል ጉዳይ ተከሳሹ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተረዘረዘውን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ አምኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ማስረጃ እንዲቀርብ ትዕዛዝ የሚሰጠው ምን ምን ነገሮችን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው?

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# <u>ማስረጃን ለፍርድ ቤት ስለማቅረብ</u>

## <u>ምዕራፍ 3</u>

## <u>ስለማስረጃ ተቀባይነት</u>

***<u>ዝርዝር አላማዎች</u>***

ሰልጣኞች ይህንን ምእራፍ ሲያጠናቅቁ ፣

- በወንጀል ጉዳይም ሆነ በፍታብሔር ስለማስረጃ ተቀባይነት እና አግባብነት በቂ ግንዛቤ በመጨበጥ በተግባር ላይ ማዋል ይችላሉ፤
- ተቀባይነት ያላቸዉን ማስረጃዎች ተቀባይነት ከሌላቸዉ የመለየት ብቃት ያዳብራሉ፡፡

## 3.1 ጠቅላላ

ዉድ ሠልጣኞች ባለፉት ምዕራፎች ውስጥ እንደተገለፀው በተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር የአንድን ፍሬ ነገር መኖር በመጥቀስ በፍ/ቤት የሚከራከር ሰው ወይም አንድ ዓይነት መደምደሚያ ላይ ሊደርስ ይገባል በሚል የሚከራከር ሰው ማስረጃ በማቅረብ የፍሬነገሩን መኖር ወይም የመደምደሚያውን ትክክለኛነት ማስረዳት ይገባዋል፡፡ የተባለው ፍሬ ነገር አለመኖሩን ወይም የተጠቀሰው መደምደሚያ ትክክለኛ አይደለም የሚል ሰውም ማስረጃ በማቅረብ ይህንኑ የማስተባበያ አቋሙን ማስረዳት አለበት፡፡

ዉድ ሠልጣኞች ለሚከተሉት ሁለት ቃላት ከማስረጃ መርህ አንፃር ትርጉም ስጡ፣ ተዛምዷቸዉንም አስረዱ፡፡

- ተቀባይነት
- አግባብነት

የአንድ ፍሬ ነገርን መኖር ወይም የመደምደሚያን ትክክለኛነት ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል የተፈለገው ማስረጃ በዘፈቀደ ወይም ማስረጃ አቅራቢው ስለፈለገው ብቻ ይቀርባል ማለት አይደለም፡፡ ማስረጃው ሊቀርብ የሚችለው ተቀባይነት ሲኖረው ብቻ ነው፡፡ ተቀባይነት የሌለው ማስረጃ ሊቀርብ አይችልም፡፡

የማስረጃው ተቀባይነት የሚወሰነው ደግሞ በሁለት መንገዶች ነው ፡፡ የመጀመሪያው የማስረጃ ተቀባይነት ቀዳሚ ደንብ የማስረጃን አግባብነት የሚመለከተው ነው፡፡፡ ማለትም እንዲቀርብ የተጠየቀው ማስረጃ ያስረዳዋል ለተባለው ፍሬ ነገር አግባብነት ሊኖረው ይገባል፡፡ በወ.መ.ህ.ሥ.ሥ. ቁጥር 137 (1) ላይ “በዋናው ጥያቄ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ውሳኔ ስለሚሰጥበት ፍሬ ነገር ተገቢ የሆኑትና ምስክሩ በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚያውቀውን ፍሬ ነገር ብቻ ነው፡፡” በሚል ሲደነገግ “ተገቢ የሆኑትና”

የሚለው ምስክሮች የሚያስረዱት ፍሬ ነገር ውሳኔ ለሚሰጥበት ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው መሆን እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡ "ብቻ " የሚለው ቃል ደግሞ ህጉ አግባብነት ያላቸውን ብቻ ለመቀበል መቁረጡንና አግባብነት የሌላቸውን ደግሞ ላለመቀበል መወሰኑን ያመለክታል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕጉም በቁጥር 263(1) ላይ የተደነገገውም ከ ወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ድንጋጌው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ምስክሮችን የሚመለከቱ ይሁኑ እንጂ የማስረጃው ዓይነት ሰነድም ይሁን ሌላ አግባብነት የሌላቸው ማስረጃዎች ለፍ/ቤት አይቀርቡም፡፡ ለዚህም የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. ቁጥር 33 (3)[2] እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕግ ቁጥር 138[3] እና 146[4] ድንጋጌዎችን መመልከት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ማስረጃው ውሳኔ ለመስጠት ተገቢነት ቢኖረው እንኳ እንዳይቀርብ የሚያግድ በህግ የተደነገገ ክልከላ ካለ አይቀርብም፡፡ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችለው ውሳኔ ሊሰጥበት ለተፈለገው ፍሬ ነገር አግባብነት ስላለው ብቻ ሳይሆን ህግ እንዳይቀርብ ያልከለከለው በመሆኑ ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ ሕግ እንዳይቀርብ የከለከለው ማስረጃ አግባብነት ቢኖረው እንኳን ሊቀርብ አይችልም፡፡ በዚህም መሠረት የማስረጃ ተቀባይነትን በተመለከተ ከላይ ከተገለፁት ሐሳቦች መረዳት የሚቻለው፡፡

- ✓ ማንኛውም ማስረጃ ሊቀርብ የሚችለው ያስረዳዋል ለተባለው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡
- ✓ በተጨማሪም ማስረጃው ሊቀርብ የሚችለው በህግ እንዳይቀርብ ያልተከለከለ እንደሆነ ነው፡፡

የማስረጃ ተቀባይነት ጉዳይ ብቸኛ ባይሆንም መሠረታዊ የማስረጃ ህግ ደንብ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ይህም በበቂ ምክንያቶች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ አግባባነት የሌለው ማስረጃ ሊቀርብ አይገባም የሚባለው የተያዘውን ክርክር ወይም ጭብጥ ለመወሰን ስለማይጠቅም ነው፡፡ ስለዚህም አግባብነት የሌለውን ማስረጃ እንዳይቀርብ ማገድ

---

[2] ‹……የማያስፈልገው ማንኛውም እቃ ግን ደረሰኝ በመቀበል ለተወሰደበት ሰው ተመላሽ ይሆናል፡፡›
[3] ‹ፍርድ ቤቱ ለክርክሩ አግባብ ያልሆነውን ወይም ከነገሩ ጋር ግንኙነት የሌለውን ማንኛውንም ጽሁፍ በማናቸውም ጊዜ እንዳይቀርብ ለማገድ ይችላል፡፡ ይህንንም ሲወስን ምክንያቱን በመዝገቡ ላይ መግለጽ አለበት፡፡›
[4] ስለጽሁፍ ሰነዶች አቀራራብ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የተነገረው ድንጋጌ እንደነገሩ አካባቢ ሁኔታ በማስረጃነት በሚቀርቡ ግዙፍ ነገሮች ላይም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡›

የፍ/ቤቱ እና የተከራካሪ ወገኖችን ጊዜና ወጪ ከመቆጠቡም በላይ የፍርድ ሒደት ሥርዓት ይዞ እንዲጓዝ ያደርጋል፣ ለተያዘው ጭብጥ በማይጠቅሙ ማስረጃዎች ክምችት ምክንያት የውሳኔ አሰጣጥ እንዳይወሳሰብም ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ማስረጃው አግባብነት ቢኖረው እንኳን ሕግ ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ፍሬ ነገሩን በተሻለ ሁኔታ የሚያስረዳ ሌላ ማስረጃ በመኖሩ (የሰነድ ማስረጃ ካለ ከምስክር በተሻለ ሁኔታ ያስረዳል) ወይም ሚዛናዊ ዳኝነት እንዳይሰጥ የሚያደርግ በመሆኑ (በወንጀል ጉዳይ ከጥፋተኛነት በፊት የተሰጠ ሌላ የጥፋተኛነት ውሳኔ) ወይም መሠረታዊ የህግ መርህ ወይም የሰው ልጆችን መብት የሚፃረር(በነፃ ፈቃድ ያልተገኘ የዕምነት ቃልን) በመሆኑ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

በአገራችን የማስረጃ ተቀባይነትን የሚመለከቱ ደንቦች በተለያዩ ሕጐች ውስጥ ተሰበጣጥረው ይገኛሉ፡፡ ከዚህ አንፃር፣

- አግባብነት የሌላቸው ማስረጃዎች የሚለዩት በማስረጃነት ሊገለፅ በተፈለገው ፍሬ ነገር እና ያስረዳዋል ወይም ያስተባብለዋል በተባለው ፍሬ ነገር ወይም መደምደሚያ መካከል በሚኖር ግንኙነት መሠረት ሲሆን፣
- ህግ አይቀርቡም የሚላቸው ማስረጃዎች የትኞቹ እንደሆኑ ደግሞ ህጐችን በመፈተሽ የሚገኝ ነው፡፡

በተግባር እንደሚታየውም በበርካታ የፍትሐብሔር እና የወንጀል ጉዳዮች ላይ የማስረጃ ተቀባይነትን የሚመለከቱ ክርክሮች የሚቀርቡ ሲሆን ፍ/ቤቶች ደግሞ ህጐችን በመመርመር ተገቢውን ብይን መስጠት ይገባቸዋል፡፡

## ***3.2 <u>ስለማስረጃ አግባብነት</u>***

### ***3.2.1 <u>ጽንሰ-ሀሳቡ</u>***

ዉድ ሠልጣኞች ከላይ እንደተገለፀው የማስረጃ አግባብነት የሚወሰነው በሁለት ፍሬ ነገሮች መካከል በሚኖር ግንኙነት መነሻ ነው፡፡ እነዚህ ፍሬ ነገሮችም ማስረጃው

ይገልፀዋል የሚገልጸው ፍሬነገርና ማስረጃው ያስረዳዋል ወይም ያስተባብለዋል የተባለው ፍሬ ነገር ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦች፡-

- ✓ የማስረጃው አግባብነት የሚወሰነው ይህ ማስረጃው ይገልፀዋል የተባለው ፍሬ ነገር ማስረጃው ሊያስረዳው ወይም ሊያስተባብለው ከሚፈልገው ፍሬ ነገር ጋር ያለው ትስስር በነገሮች አመክኖአዊ ግንኙነት (Logical connection) ወይም ህግ በፈጠረው ትስስር (ለምሳሌ ህፃኑ የተፀነሰበት ቀን ከዚህ በኃላ ነው ብሎ ለመገመት የተወለደበትን ቀን የሚመለከት ፍሬ ነገር) መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡
- ✓ ማስረጃው ያስረዳዋል ወይም ግምቱ እንዲወሰድ ያስችለዋል ወይም ያስተባብለዋል የተባለው ፍሬ ነገር በፍ/ቤት ክርክር ረገድ በጭብጥ የተያዘ ፍሬ ነገር (fact in issue) ወይም ለዚህ በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው ሌላ ፍሬ ነገር (another fact relevant to the fact in issue) ሊሆን ይችላል፡፡ (Ratanlal and Dhirajlalp….)
- ✓ በማስረጃነት የቀረበው ወይም እንዲቀርብ የሚፈለገው ፍሬ ነገር የሚሰጠው አገልግሎት በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር መኖር ማረጋገጥ ወይም ማስተባበል (proving or disproving existense or non — existence of fact) ወይም ይኸው ፍሬ ነገር ስለመኖሩ ወይም ስለአለመኖሩ ግምት እንዲወሰድ ማስቻል (rendering probable the existence or non existence of fact) ሊሆን ይችላል፡፡

### 3.2.2 <u>የማስረጃ አግባብነት በወንጀል ጉዳዮች</u>

በወንጀል ጉዳዮች የሚቀርቡ ማስረጃዎች ውሳኔ ለሚሰጥበት ፍሬ ነገር አግባብነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ይህም በወ.መ.ህ.ሥ.ሥ.እንደተደነገገ ቀደም ሲል ተገልፆአል፡፡ የአግባብነት ድንጋጌው ተፈፃሚ የሚሆነውም በዐቃቤ ሕግ በኩል ለሚቀርቡ ማስረጃዎች ብቻ ሳይሆን በተከሳሹ በኩል ለሚቀርቡ የመከላከያ ማስረጃዎች ጭምር ነው፡፡ ሊቀርብ የተፈለገው ማስረጃ ውሳኔ ሊሰጥበት ለተፈለገው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው መሆኑ ወይም አለመሆኑ በሁለቱ ፍሬ ነገሮች መካከል ባለው ግንኙነት ወይም ትስስር የሚወሰን ሆኖ የዚህን ግንኙነት መኖር ለማረጋገጥ ደግሞ፣

- ✓ በክስ ማመልከቻው ላይ የተገለፀውና ተላለፈ በተባለው የወንጀል ህግ ድንጋጌ ወንጀሉን ያቋቁማሉ በሚል የደነገጋቸው ፍሬ ነገሮች ሊመረመሩ ይገባል፡፡ በጭብጥ የሚያዘውን ፍሬ ነገር ለማወቅ ይረዱናል፡፡
- ✓ ማስረጃው ይገልፀዋል የተባለውን ፍሬ ነገር ደግሞ ግራቀኝ ተከራካሪ ወገኖች (ዐቃቤ ህጉና ተከሳሹ) ማስረጃውን ከማሰማታቸው በፊት ስለማስረጃው አይነትና ይገልፀዋል ስለተባለው ፍሬ ነገር ከሚሰጡት መግለጫ ለመረዳት ይቻላል፡፡ (የወ.መ.ህ.ሥ.ሥ. ቁጥሮች 136 እና 142 (2)) ፍርድ ቤቱ ይህንን መግለጫ ካደመጠ በኃላ ማስረጃውን ከመቀበሉ በፊት በአግባቡ ላይ ሊወሰን ይገባል፡፡

በወንጀል ጉዳይ የማስረጃ አግባብነት ሲወሰን ከጭብጥ ወይም በወንጀል ህጉ ላይ ከተጠቀሰው እና ተከሳሹ ተላለፈ የተባለውን ወንጀል ያቋቁማሉ ተብለው ከተገለፁት ፍሬ ነገሮች እና በክስ ማመልከቻው ላይ ከተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች አንፃር የሚታዩ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ነገር ግን ሊቀርብ የተፈለገው ማስረጃ የግዴታ ከእነዚህ ፍሬ ነገሮች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል ብሎ መደምደም ስህተት ነው፡፡ ሊቀርብ የተፈለገው ማስረጃ ከጭብጡ ጋር በቀጥታ ባይገናኝም እንኳን የወንጀሉን አፈፃፀም አካባቢያዊ ሁኔታ የሚያስረዳ ከሆነ አግባብነት ሊኖረው ይችላል፡፡ እንደነዚህ ያሉ ቀጥተኛ ሳይሆን ቀጥተኛ ያልሆኑ ማስረጃዎች በተናጠል ሲታዩ ጭብጡን የሚያስረዱ ባይሆኑም ተጠረቃቅመው ሲገናዘቡ ግን ሊያስረዱ ይችላሉ፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የማስረጃ አግባብነት የሚለካው በጭብጥነት ከተያዘው ፍሬ ነገር ወይም ለዚህ ፍሬ ነገር አግባብነት አለው ከተባለ ፍሬ ነገር ጋር ካለው አግባብነት ነው የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ እንግሊዝና ህንድን በመሳሰሉ አገሮችም በወንጀል ጉዳይ ማስረጃ አግባብነት አለው ከሚባልባቸው ምክንያቶች መካከል በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር ወይም ለዚህ ፍሬ ነገር አግባብነት ላለው ፍሬ ነገር፡-

- ✓ አንድ አካል ወይም አንድ ክፍል የሆኑ ፍሬ ነገሮች
- ✓ አጋጣሚ፣ መንስኤ ወይም ውጤት የሆኑ ፍሬ ነገሮች
- ✓ አመቺ ሁኔታዎችን የፈጠሩ ፍሬ ነገሮች
- ✓ ያነሳሱ፣ ዝግጅነትን፣ የሚያሳዩ እንዲሁም ከድርጊቱ በፊትና በኃላ የታዩ ባህርያት ይገኙበታል (May P.) በእኛ አገርም ተፈፃሚነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

### 3.2.3 <u>የማስረጃ አግባብነት በፍትሐብሔር ጉዳዮች</u>

በፍትሐብሔር ጉዳዮች የማስረጃ አግባብነትን ለመወሰን ዋነኛው መመዘኛ ማስረጃው ይገልፀዋል በተባለው ፍሬ ነገር እና በጭብጥ በተያዘው ፍሬ ነገር መካከል ያለው ትስስር ወይም ግንኙነት ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በህግ የሚወሰንበት ሁኔታም አለ፡፡ ሕጉ የማስረጃውን አግባብነት የሚወሰነውም፡-

- ✓ ሕጉ በፍሬ ነገሮች መካከል ያለውን ትስስር ሊወሰን ይችላል፡፡ ለምሳሌ የህፃኑ መፀነስ ከመቼ ጀምሮ ነው? የሚለውን ለማስረዳት የተወለደበትን ቀን ማስረዳት ይገባል በሚል በተፀነሰበት እና በተወለደበት ቀን መካከል ትስስር እንደፈጠረው ማለት ነው፡፡ እንደህ ዓይነት ትስስር የሚታይባቸው በርካታ ድንጋጌዎች አሉ፡፡
- ✓ ሕጉ የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት አግባብነት ያላቸው የተወሰኑ ፍሬ ነገሮች ብቻ ናቸው በሚል የሚደነግግበት ሁኔታ አለ፡፡ በፍ.ብ.ሕ. ቁ 1696 ላይ እንደተመለከተው ማስገደድ፣ ስህተት እና ማታለል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የሚቀርበው ማስረጃ ማስገደድ፣ ስህተት ወይም ማታለል መፈጸሙን የሚያስረዳ መሆን አለበት ነው፡፡
- ✓ እንዲሁም ሕጉ የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት አግባብነት የላቸውም በሚል የተወሰኑ ፍሬ ነገሮችን ከማስረጃነት ያስወገደበት ሁኔታም ይኖራል፡፡ በፍ.ብ.ህ.ቁ 826 በሞት ምክንያት የሚሰጥ ካሳ የዉርስ ሀብት ክፍል አለመሆን፣ ቁጥር 837 የወራሽ ፆታ እድሜ ዜግነት በዉርሱ ላይ ምንም ልዩነት ያለማምጣት፣ ቁጥር 1163(2)ተንቀሳቃሽ ነገሮችን የወሰደ ሰው ንብረቱን የወሰደው ንብረቱን ለማስተላለፍ መብት በሌለው ሰው መሆኑን ንብረቱን ከወሰደ በኃላ ቢያውቅ ጉዳት እንደማይደርስበት፣ ቁጥር 1171 የእንስሳት ልጆች ባለሀብትነትን በሚመለከት ባለሀብትነቱ እንስቲቱን የሚከተል መሆኑንና የመሳሰሉት ማለት ነው፡፡

ማስረጃው ሊገልፀው የፈለገው እና ያስረዳዋል የተባለው ፍሬ ነገር ሊገኝ የሚችለውም የተከራካሪዎች አቤቱታ ጽሁፍን፣ ግራ ቀኙ በክርክር ሂደት ከገለፁዋቸው ነገሮችን እና

ማስረጃ ሊያቀርቡ ማስረጃው ስለሚገልፀው ፍሬ ነገር የሚሰጡት መግለጫን በመመርመር ነው፡፡

## 3.3 *ማስረጃ ተቀባይነት እንዳይኖረው በህግ ስለሚደነገግበት ሁኔታ*

የማስረጃ ተቀባይነት በሚመለከት በቅድሚያ የሚቀመጠው መሰረታዊ መርህ ማስረጃ በተለይ እንዳይቀርብ በህግ ካልተከለከለ በቀር ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል የሚለው ነው፡፡ በዚህም መሠረት አግባብነት ያለው ሆኖ ተቀባይነትን የሚያጣው ሕጉ የከለከለው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በሕንድ እና በእንግሊዝ የማስረጃ ሕግ መሠረት ማስረጃ ተቀባይነት ከሚያጣባቸው ሁኔታዎች መካከል፡-

- ✓ የሰሚ ሰሚ ማስረጃ
- ✓ በግዴታ የተሰጠ የዕምነት ቃል
- ✓ የምስክር አስተያየት የሚሰጥበት ማስረጃ
- ✓ ፀባይን የሚመለከት ማስረጃ
- ✓ የትዳር፣ የሥራ ሚስጢርን የሚመለከቱ ማስረጃዎች ይገኙበታል(May pp 6-9)

በአገራችን ግን የሰሚ ሰሚ ማስረጃ እና በትዳር ጓደኛ ላይ የሚሰጥ ምስክርነት በማስረጃነት እንዳይቀርብ የሚከላከል ሕግ የለም፡፡ የምስክር አስተያየት የሚሰጥበት ማስረጃን በተመለከተም ምንም እንኳን አይቀርብም በሚል የተደነገገ ነገር ባይኖርም ምስክር የሚቀርበው ፍሬ ነገሮችን ብቻ ለመግለፅ በመሆኑ በተለይ የባለሞያ ማስረጃ ሆኖ እንዲቀርብ ፍ/ቤት የሚያዝዝ ካልሆነ በቀር አይቀርብም፡፡ ይህ እንደጠበቀ ሆኖ የህጉቻችን ድንጋጌዎች ሲፈተሹ፡-

- ✓ ፍሬ ነገሩን ለማስረዳት ተገቢ የሆነውን የማስረጃ ዓይነት፣
- ✓ ፍሬ ነገሩ (ማስረጃው) ራሱ ፍ/ቤት እንዳይቀርብ በሚል ወይም
- ✓ ማስረጃው የተገኘበት መንገድ ተገቢ ባለመሆኑ ምክንያት

ማስረጃ ተቀባይነት እንዳይኖረው ሊደረግ ይችላል፡፡

### 3.3.1 <u>ከማስረጃ አይነት አንፃር</u>

የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች አንዳንድ ፍሬ ነገሮችን ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል ሰነዶች ብቻ ሊቀርቡ እንደሚገባ እና ምስክሮች ሊቀርቡ እንደማይችሉ ያስረዳሉ በዚህም መሠረት፡-

- ✓ የፍ.ብ.ሕ.ቁጥር 2003 ላይ ውል በጽሑፍ እንደሆነ ህግ በአዘዘ ጊዜ ውሉ የተሰረቀ፣ የጠፋ፣ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ውሉን በምስክር ወይም በህሊና ግምት ማስረዳት አይቻልም በሚል ተደንግጐአል፡፡ ስለዚህ አንድ ውል በጽሑፍ እንዲሆን ሕግ በአዘዘ ጊዜ ውሉን ማስረዳት የሚቻለው የጽሑፍ ሰነድን በማቅረብ ነው፡፡ ጽሑፍ ከሌለ በምስክር ማስረዳት አይቻልም፡፡ በጽሑፍ ውል የተደረገ ከሆነም ውሉ የተሰረቀ ወይም የጠፋ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ምስክር ማቅረብ አይቻልም፡፡ በማስረጃነት የቀረበ የውል ሰነድ ላይ የተገለፁ ፍሬ ነገሮችን ማስረዳት የሚቻለው በሰነዱ ብቻ ነው፡፡
- ✓ ኑዛዜን በተመለከተም በግልፅ ወይም በተናዛዥ ጽሑፍ የተደረገ ኑዛዜ መኖሩንና በኑዛዜው ላይ የሰፈረውን ቃል ማስረዳት የሚቻለው በኑዛዜው ሰነድ ብቻ ነው (ቁጥር 896-897)፡፡

***<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በጽሑፍ የሚደረግ ውል በሁለት ምስክሮች ፊት ካልተረጋገጠ በስተቀር እንደማይፀና በፍ.ብ.ህ.ቁ 1727 (2) ላይ፤ እንዲሁም በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ በአራት ምስክሮች ፊት ካልተረጋገጠ ፈራሽ እንደሚሆን በዚሁ ህግ በቁጥር ላይ ተደንግጓል፡፡ በጽሑፍ የተደረገ ውልን ወይም ኑዛዜ በምስክር ማስረዳት አይቻልም ከሚለው አንፃር የምስክሮች መኖር ፋይዳው ምንድ ነው?
2. የወንጀልን ጉዳይ ለማስረዳት ሰነድ ብቻ ተቀባይነት ይኖረዋል የሚባልበት ሁኔታ ይኖራልን?
3. ዋናው ሳይሆን ፎቶ ኮፒው ሰነድ በማስረጃነት ቢቀርብ ተቀባይነቱ እስከምን ድረስ ነው?

4. የሚከተለውን ለፍ/ቤት የቀረበ ጉዳይ ተመልከት (ከፍ/ይ/መ/ቁ. 1730/80 የተወሰደ) ተከሳሹ በቂ ስንቅ ሳይኖረው ቼክ ፈርሞ ስለሰጠ በቼክ ላይ የተመለከተውን ብር 53.000 ይከፈለኝ በማለት ከሳሽ ለአቀረበው ክስ ማስረጃ አድርጐ የአቀረበው የቼኩን ፎቶ ኮፒ እና የወንጀል ክስ በቀረበ ጊዜ ዋናው ቀርቦ ከምርመራ መዝገቡ ጋር ተያይዞ እንደነበር ነገር ግን በኃላ ሲፈለግ የጠፋ በመሆኑ ይኸው ታውቆ ትብብር እንዲደረግለት ከዐቃቤ ህግ መ/ቤት የተፃፈለትን ደብዳቤ ነው፡፡ ተከሳሹ በሰጠው መልስ በማስረጃነት የቀረበው ቼክ ላይ ያለውን ፊርማ እንደሚክድ ገልፆ ዋናው ቀርቦ በሬጅስትራሩ በኩል እንዲረጋገጥም ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሳኔ፡-

   ሀ/ "ፎቶ ኮፒ ሰነድ በማስረጃነት ቀርቦ በሚካሄድበት ጊዜ ዋናው ቀርቦ ካልተመሳከረ ፎቶ ኮፒው ማስረጃ ተቀባይነት የለውም"

   ለ/ "ዋናውን ማስረጃ ከፎቶ ኮፒ ጋር አመሳክሮ ትክክለኛነቱን አረጋግጦ ማስረጀ መስጠት የሚችለው በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 230(ለ) መሠረት ሬጂስትራሩ ብቻ ነው"

   ሐ/ "ይግባኝ ባይ (ከሳሽ) የቼኩን ሰነድ ዋናውን ካልያዙ ክስ መመስረት አይችሉም"

   መ/ "ዐቃቤ ሕጉ ዋናውን ቼክ ለማየቱና ለመጥፋቱም ማረጋገጫ ሰጥቶኛል የሚሉት በህግ የሚደገፍ አይደለም ብሏል፡፡

   ፍርድ ቤቱ ያቀረባቸው ምክንያቶች አሳማኝና ተቀባይነት ያላቸው ናቸው ወይ?

## 3.3.2 <u>ፍሬ ነገሩ (ማስረጃው) እንዳይቀርብ የሚደረግ ክልከላ</u>

በኢትዮጲያ የወ.መ.ህ.ሥ.ሥ.ቁጥር 138 ላይ በህግ በተለይ ካልተፈቀደ በቀር የጥፋተኛነት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ተከሳሹ በወንጀል ተከስሶ የተቀጣ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ ሊቀርብ እንደማይገባ ተደንግጐአል፡፡ የቀድሞ የጥፋተኛነት ሪከርድን በሚመለከት የኢትዮጵያ ህግ የወሰደው አቋም ከአንግሎ አሜሪካን የህግ ሥርዓት የማስረጀ ህግ ጋር የሚቀራረበ ስለመሆኑ ይህ ድንጋጌ ማረጋገጭ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የቀድሞው የጥፋተኛነት ሪከርድ ከፍርድ በፊት እንዳይቀርብ የሚከላከለው አንድም አግባብነት ስለሌለው ሲሆን አግባብነት አለው የሚባል ቢሆን እንኳ ከፍርድ

በፊት ጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠርን ህገመንግስታዊ ድንጋጌ በማፋለስ ዳኞች አሁን የተከሰሰበትንም ወንጀል ፈፅሟል የሚል አቋም እንዳይዙና ማስረጃውን ፍታሐዊ በሆነ ሁኔታ የማመዛዘን አቅማቸው እንዳይዳከም ለማድረግ ነው፡፡

ከፍርድ በፊት የቀድሞ ጥፋተኛነትን የሚገልፅ ውሳኔ ሊገለፅ አይገባም የሚለው ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ተከሳሹ አሁን የተከሰሰበት ወንጀል ቀደም ሲል ተከስሶ ጥፋተኛ ከተባለበት ወንጀል ጋር ሊኖረው የሚችለውን ተመሳሳይነት ወይም ልዩነት ግምት ውስጥ ሳያስገባ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በዚህም መሠረት ቀደም ሲል ጥፋተኛ የተባለበት ወንጀል አሁን ክስ ከቀረበበት ወንጀል ጋር ተመሳሳይም ሆነ የተለያየ ግምት ውስጥ ሳይገባ እንዳይቀርብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

የፍትሐብሔርን ጉዳይ በሚመለከት ግን እንዲህ ዓይነት ክልከላ የለም፡፡ ዋናው ነገር የማስረጃው አግባብነት ነው፡፡ በፍ.ብ.ህ.ቁጥር 2149 ላይ በወንጀል መቀጣት ወይም ነፃ መውጣት በፍትሐብሔር ረገድ ጥፋት መፈፀሙን ወይም አለመፈፀሙን ለመወሰን ፍ/ቤቱን አያስገድደውም በሚል ተደንግጓል፡፡ ይህ ማለት ግን ቀደም ሲል የተሰጠ ፍርድ እንዳይቀርብ የሚከላከል ሳይሆን ፍ/ቤቱ በፍትሐብሔር ረገድ በቀረበው ክስ ላይ ጥፋት ተፈፅሞአል ወይስ አልተፈፀመም የሚለውን ሊወሰን በዚሁ ጉዳይ በወንጀል በተሰጠ ውሳኔ ሳይገደድ መወሰን እንደሚችል ለመግለፅ ነው፡፡ ለማጠቃለል በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሳኔ አግባብነት ካለው በፍ/ብሔር ጉዳይም ሊቀርብ ይችላል፡፡ ይህ ማለት ግን በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ መባሉ በፍትሐብሔርም አጥፍቷል፤ ነፃ ነው መባሉም በፍትሐብሔር አላጠፋም የሚል መደምደሚያ ላይ የግዴታ አያደርስም፡፡ ማስረጃው ግን ይመዘናል፡፡

***<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>***

በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 138(1) ላይ የቀድሞ ጥፋተኛነት ውሳኔ በተያዘው ጉዳይ የጥፋተኛነት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት እንዳይቀርብ የተከለከለ ሲሆን፣ ነገር ግን ሕግ በግልፅ የፈቀደ ከሆነ ሊቀርብ እንደሚችል ተመልክቶአል፡፡ ሕግ በተለይ የሚፈቅድባቸው ሁኔታዎች አሉን? ከፍርድ በኂላ እንዲቀርብ የተፈቀደውስ ለምን ይመስላችኂል?

### 3.3.3 ማስረጃው ከተገኘበት መንገድ አንፃር የሚደረግ ክልከላ

ማስረጃው ከተገኘበት መንገድ አንፃር የተቀባይነት ጥያቄ የሚያስነሳው ከፍ/ቤት ውጭ የተሰጠ የዕምነት ቃልና በዚህ መሠረት የተሰበሰቡ ሌሎች ማስረጃዎች ህጋዊነት አጠያያቂ ሲሆን ነው፡፡ ከፍርድ ቤት ውጪ የተሰጠ የዕምነት ቃል አግባብነት እስካለው ድረስ በማስረጃነት ሊቀርብ እንደሚችል ቀደም ሲል ተገልፆአል፡፡ ይህንን ዓይነት ማስረጃ ሲቀርብ ግን በነፃ ፈቃድ የተሰጠ መሆን ይኖርበታል፡፡ የዕምነት ቃሉ በነፃ ፈቃድ የተሰጠ መሆን እንደሚገባው በአስገዳጅነት መቀመጡ ተገቢነቱ ለፍትሐብሔርና ለወንጀል ጉዳዮች ተፈፃሚነት ቢኖረውም ጉልህ ስፍራ የሚሰጠው ግን በወንጀል ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ላይ ትኩረት ተሰጥቶበታል፡፡

የወንጀል ድርጊት መፈፀሙን በማመን ተከሳሹ ለመርማሪ ፖሊስ ወይም በምርመራ ቃሉን ለተቀበለ ፍ/ቤት የሰጠው ቃል በማስረጃነት ሊቀርብ እንደሚችል በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 27(2) ላይ በግልፅ፤ በቁጥር 35 ላይ ደግሞ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ተመልክቶአል፡፡ ነገር ግን ለመርማሪው ፖሊስ የተሰጠው የእምነት ቃል በነፃ ፈቃድ የሰጠ መሆን ይኖርበታል ፡፡ በዚህም መሠረት የዕምነት ቃሉ ተቀባይነት እንዲኖረው፡-

- ✓ ተከሳሹ የዕምነት ቃሉን ለመስጠት ሊገደድ አይገባም፡፡ ተፅዕኖ ወይም ግዴታ እንዳለ የሚያመለክቱት ደግሞ በድብደባ፣ በዛቻ፣ በማስፈራራት፣ በመደለል፣ የተሰፋ ቃል በመስጠት፣ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ እጽ ተፅዕኖ ቃል እንዲሰጥ በማድረግ የተገኘ ሲሆን ነው፡፡ በእንደዚህ ዓይነት መንገድ የተገኘ የዕምነት ቃል ደግሞ ተቀባይነት የለውም፡፡
- ✓ ተከሳሹ ቃሉን የሰጠው በነፃ ፈቃድ መሆኑ በቀረበው የዕምነት ቃል ማስረጃ ላይ መጠቀስ አለበት፣ ተከሳሹ ቃል መስጠት ያለመስጠት መብቱ መሆኑ አምኖ በነፃ ፈቃዱ የሚሰጠው ቃል ግን ወደፊት በፍ/ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል የተነገረው መሆኑ በእምነት ቃሉ ላይ ተመዝግቦ መገኘነት አለበት፡፡ (መዝገቡ ምትኬ ገፅ 48)

ከዚህ በተጨማሪ የእምነት ቃሉ በወንጀል ምርመራ ቃል ለመቀበል ሥልጣን ለተሰጠው አካል የተሰጠ መሆን እንዳለበት የሚገልፅ አቋም አለ፡፡ (መዝገቡ ምትኬ ገፅ 48-49)፡፡ በአንዳንድ የፍ/ቤት ጉዳዮች ውስጥ እንደሚታየው የእምነት ቃል የተሰጠው ምርመራ ለማድረግ በህግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ሳይሆን ለቀበሌ ገበሬ ማህበር በሆነ ጊዜ በማስረጃነት እንዲቀርብ ሊደረግ አይገባም፡፡ (የጠ/ፍ/ቤትወ.ይ.መ.ቁ.3281 ተመልከት) በሌላ በኩል ግን የእምነት ቃሉ የተሰጠው በህግ ቃል ለመቀበል ሥልጣን ላለው አካል እስከሆነ ድረስ (ፖሊስ/ ፍ/ቤት) የዕምነት ቃሉ ተቀባይነት ለማግኘት በነፃ ፈቃድ ሊሰጥ የሚገባ ሲሆን በነፃ ፈቃድ ሳይገደድ መብቱ ተነግሮት አውቆ ተረድቶ የሰጠ መሆኑ በእምነት ቃሉ በራሱ ላይ መገለፅ ይገባል፡፡

ተከሳሽ የዕምነት ቃሉን የሰጠው በነፃ ፈቃዱ አለመሆኑን የማስረዳት መብት እንዳለውም መታወቅ አለበት ከዚህ አንፃር በበርካታ የፍ/ቤት ውሳኔዎች ላይ እንደሚታየው፡-

- ✓ ተከሳሹ ቃሉን ሰጥቶ ወደ ምርመራ ክፍል ሲመለስ በአካሉ ላይ የታየበትን ጉዳት የሚያስረዱ ምስክሮችን በማቅረብ፣
- ✓ በቁጥጥር ስር በዋለበት እና የተከሳሽነት ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ መካከል ያለው ልዩነት፣
- ✓ የተከሳሽነት ቃሉን በተደጋጋሚ የሰጠበትና እየተለዋወጠ የተመዘገበበት ሁኔታ (በአንዳንድ መዝገቦች ላይ እንደሚታየው ተከሳሹ በመጀመሪያ ክዶ ቃሉን ከሰጠ በኃላ መጀመሪያ የሰጠውን ለውጦ የዕምነት ቃል ሰጥቷል በሚል የሚመዘገብበት ሁኔታ አለ፡፡)
- ✓ በፍ/ቤት የዕምነት ቃል ከሰጠ በኃላ ወደ ጣቢያ የተመለሰ ከሆነ፣

የዕምነት ቃሉ በነፃ ፍቃድ ያልተሰጠ ስለመሆኑ በማስረጃነት እየቀረቡ የእምነት ቃሉ በነጻ ፈቃድ የተሰጠ ነው የሚለውን ለማስተባበል የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ እንረዳለን፡፡

በወንጀል ጉዳይ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 19(5) ላይ እንደተገለፀው በማስገደድ የተገኘ የዕምነት ቃል በማስረጃነት ቢቀርብ ተቀባይነት እንደሌለው ተደንግጓል፡፡ የዚህ መነሻም፣

- ❖ የተከሳሽ ከፍርድ በፊት ጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠር መብት፣

❖ እንዲሁም የተከሳሹ ራሱን ያለመወንጀል መብት ናቸው፡፡

ተቀባይነት የማይኖረው በግዴታ፣ በተፅዕኖ ወይም በማባበል፣ ወይም በማታለል የተገኘው የዕምነት ቃል ብቻ ነው ወይስ በዚህ የዕምነት ቃል መነሻ የተገኘው ሌላ ማስረጃም ጭምር ነው የሚለው በህግ ምሁራን ዘንድ የክርክር መነሻ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የዕምነት ቃሉን ውድቅ አድርጎ በዚህ የእምነት ቃል መነሻ የተገኘውን ማስረጃ መቀበል ማለት ዞሮ ዞሮ "የተገኘው ውጤት የተጠቀምንበትን መንገድ ትክክለኛነት ያረጋግጣል" (The end Justifies the means) የሚለውን ህግ ሊያስወግደው የፈለገውን አስተሳሰብ ማንፀባረቅ በመሆኑ ውድቅ መደረግ የሚገባው የዕምነት ቃሉ ብቻ ሳይሆን በዚህ መነሻ የተገኘው ሌላ ማስረጃም ጭምር ነው በሚል የሚከራከሩ አሉ፡፡(መዝገቡ ምትኬ ገፅ 45)፡፡ ሕገመንግስቱ የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም፡፡ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖርም በሚል ደንግጓል፡፡ በእርግጥ በማስገደድ የሚገኝ የእምነት ቃል እውነትነቱን ለማረጋገጥ የሚያስቸግር ስለሚሆን ተቀባይነት አይኖረውም በሚል ህገመንግስቱ በግልጽ መደንገጉ ተገቢና ትክክል ነው፡፡ ይሁንና የተከሳሹን የእምነት ቃል መሰረት አድርጎ የተገኘ ወንጀል ስለመፈጸሙ የሚያስረዳ ማስረጃን አለመቀበል ግን እውነት የተፈጸመ ወንጀል ለመሆኑ እየታወቀና እየተረጋገጠም ወንጀል አድራጊው እንዲያመልጥ የሚፈቅድ ነው የሚሆነው፡፡ ስለሆነም የማስገደድ ተግባር የፈጸመው ባለስልጣን ወይም አስፈጻሚ በድርጊቱ መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ከእምነት ቃሉ ሌላ የተገኘ ማስረጃ በማስረጃነት መወሰዱ አግባብነት ይኖረዋል፡፡

***<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በምርመራ ጊዜ ከተሰጠ የተከሳሽነት ቃል ጋር በተያያዘ፡-
   ሀ. መርማሪው ፖሊስ በችሎት በተገኘበት ለወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠ የዕምነት ቃል
   ለ. መርማሪ ፖሊስ በፍርድ ቤት የተከሳሹን ቃል እንዲቀበል በጠየቀበት ደብዳቤ ላይ "ተከሳሹ በጣቢያ የሰጠውን የዕምነት ቃል እንደያረጋገጥ ይደረግልን" በሚል መግለፅ፣

ሐ. ተከሳሹ በፍርድ ቤት የዕምነት ቃሉን ከሰጠ በኃላ ወደ ማረፊያ ቤት ሳይሆን ወደ ፖሊስ ጣቢያው መመለሱ የተሰጠውን የዕምነት ቃል በነፃ ፍቃድ አይደለም ለማለት ያስችላሉን?

2. የሚከተለውን ጉዳይ ተመልከት "ተከሳሽ ቤት አቃጥሎአል ተብሎ ለተጠረጠረበት ወንጀል መርማሪ ፖሊስ ከተከሳሹ ጋር የሚያገናኝ ማስረጃ ማቅረብ አልቻለም፡፡ ፖሊሶች በቃጠሎው አካባቢ የተገኘ ቤቱን ለማቃጠል አገልግሎት ላይ የዋለ ነዳጅ የነበረበት ጠርሙስ ላይ የተነሳው አሻራ ከተከሳሹ የጣት አሻራ ጋር ተመሳሳይ መሆኑ እንደተደረሰበት የሚገልፅ ሐሰት ቃል ለተከሳሹና ለጠበቃው ነገሩዋቸው፡፡ ተከሳሹም ወዲያውኑ በጠርሙስ ነዳጅ ሞልቶ ካዘጋጀ በኋላ ከጓደኛው ጋር አብረውሔደው ቤቱን እንዳቃጠሉ በማመን ቃሉን ሰጠ፡፡" (ከ Re V. Mason (1987) 3 ALLER 481 (CA) የተወሰደ)፡፡

ይህ የእምነት ቃል በነፃ ፈቃድ የተሰጠ ነው ለማለት ይቻላልን?

# ምዕራፍ 4

# ስለ ማስረጃ አቀራረብ

**ዝርዝር አላማዎች**

ሰልጣኞች ይህንን ምእራፍ ሲያጠናቅቁ ፣

- ስለማስረጃ አቀራረብ የተከራካሪዎችን ሚና ለይተዉ አዉቀዉ ሥራ ላይ ያዉላሉ፡፡
- ማስረጃዎች በወንጀልም ሆነ በፍታብሔር መቼ፣ እንዴት እና በማን መቅረብ እንዳለባቸዉ ለይተዉ አዉቀዉ ሥራ ላይ ያዉላሉ የተሳሳቱ የልምድ አሰራሮችንም ያርማሉ፡፡

## 4.1 *ጠቅላላ*

ዉድ ሠልጣኞች ፍሬ ነገርን ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል የሚቀርብ ማስረጃ የተቀባይነትን መስፈርቶች ማሟላት አንደሚገባው ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን እንዲቀርብ የተፈለገው ማስረጃ ተቀባይነት አለው መባሉ ብቻውን ማስረጃን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ሁሉ አሟልቶ አይመልስም፡፡ የማስረጃ ተቀባይነት ጥያቄ ምን ዓይነት ማስረጃዎች ሊቀርቡ እንደሚገባና አንደማይገባ ይነግረናል፡፡ ከዚህ አልፎ ግን ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ማን ሊያቀርብ እንደሚገባ እና እንዴትና መቼ ማቅረብ አንዳለበት አይነግረንም፡፡ የዚህ ምዕራፍ ዓላማ እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ይሆናል፡፡

ዉድ ሠልጣኞች ማስረጃ የማቅረብ ግዴታና በማስረጃ የማሳመን ሸክም ያላቸዉን ተዛምዶ አብራሩ፡፡

በአገራችን እነዚህን ጥያቄዎች የሚመለከቱ ደንቦች በተለያዩ ህጐች ውስጥ ተሰግስገው እናገኛለን፡፡ አንዳንዶቹ በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ህገ ውስጥ (ማን ያቀረበዋል የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ) ሌሎች ደግሞ በ1954 እና በ1958 ዓ.ም እንደቅደም ተከተላቸው በወጡት የወንጀልና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጐች ውስጥ

(ማን? እንዴት? እና መቼ? የሚሉትን ጥያቄዎች በተመለከተ) ተሰበጣጥረው እናገኛቸዋለን፡፡ ሌሎች ህጐች ውስጥም ይኖራሉ፡፡

በአገራችንም ሆነ በሌሎች አገሮች ህጐች የሚገኙትን የማስረጃ አቀራረብን የማመለከቱ ደንቦች ሲቃኙ፣

- እንደ ጉዳዩ ዓይነት (ወንጀል ወይስ ፍታብሔር )፣
- እንደማስረጃው መንገድ (ምስክር፣ ሰነድ፣ ወይስ ሌላ ማስረጃ)
- እንዲሁም እንደሥነሥርዓት ሕጉቻቸው የአወቃቀር ፍልስፍና (የአንግሎ አሜሪካ የህግ ሥርዓት ወይስ የአህጉራዊው አውሮፖ የህግ ሥርዓት) ልዩነት ያሳያሉ፡፡

የጉዳዩን ዓይነት በተመለከተ በወንጀል ጉዳይ የማስረጃ አቀራረብ ከፍትሐብሔር ጉዳይ የማስረጃ አቀራረብ የሚስማማቸው ነጥብ ቢኖሩም በበርካታ ሁኔታዎች ልዩነትን ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ ወረድ ብለን እንደምናየው (ተከሳሹ በሰጠው የዕምነት ቃል መሠረት ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ የጥፋተኝነት ውሳኔ ካልተሰጠ በቀር) ማስረጃ የማቅረብና የማስረዳት ሸክሙ ምን ጊዜም ቢሆን የዐቃቤ ህጉ ነው፡፡ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሹ የዞርበት ሁኔታ በመሠረቱ (በፀረ ሙስና የማስረጃና የስነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 434/97 እንደተሻሻለ ላይ ከሚታይ በስተቀር) ከከሳሹ ወደ ተከሳሹ የሚዞርበት ሁኔታ የለም፡፡ በፍትሐብሔር ግን የማስረዳት ሸክሙ በመሠረቱ የከሳሽ ቢሆንም ወደ ተከሳሹ ሊዞር ይችላል፡፡

የማስረጃውን መንገድ ወይም አይነት በተመለከተ የማስረጃ አቀራረብና ተያያዥ ጥያቄዎች ከማስረጃው ዓይነት አንፃር የተለዩ ደንቦችን የሚከተሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሊቀርቡ የታሰቡት ማስረጃዎች ምስክሮች፣ ሰነዶች ወይም ሌላ ዓይነት መሆናቸው በማስረጃው አቀራረብ ላይ ልዩነት ሊፈጥር ይችላል፡፡ ምስክር በሆነ ጊዜ ምስክሩ ቀርቦ ነገሩን ለማስረዳት ያለው የመገንዘብና የመረዳት ችሎታ ግምት ወስጥ ይገባል፡፡ ሰነዶችና ኤግዚቪቶች ግን እንዲህ ዓይነት ( የአዕምሮ ሁኔታን፣ የአካል ሁኔታን) ተፈላጊውን ፍሬ ነገር ለመረዳትና ለማስረዳት ተፈላጊ የሆነ መመዘኛ አግባብነት ላይኖራቸው ይችላል፡፡

በሦስተኛ ደረጃም የማስረጃ አቀራረብና የቀረበውን ማስረጃ የመመርመር ጥያቄ (በተከታዩ ምዕራፍ በዝርዝር የሚታይ ይሆናል) እንደየህግ ሥርዓቱ የሚለያይ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ከማስረጃ አቀራረብ አንፃር የህግ ስርዓቶቹ የአንልግሎ አሜሪካ የህግ ስርዓት ተከታይ የሆኑ እንደ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ህንድ… ወዘተ የመሳሰሉ አገሮች የወንጀል ሥነ ሥርዓት (Adversarial Procedure) ከአህጉራዊው አውሮፖ የወንጀል ሥነ ሥርዓት (Inquisitorial procedure) በበርካታ ጉዳዮች የተለያየ ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት አካሔድ አጠቃላይ ባህሪያት በሁለቱም ሥርዓቶች በአብዛኛው ተመሳሳይ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃን በተመለከተ መሠረታዊ ልዩነቶች ይንፀባረቃሉ፡፡ በዚህም መሠረት፡-

- የመንግስት ሚናን በተመለከተ በአንልግሎ አሜሪካ የወንጀል ሥነ ሥርዓት (Adversarial Procedure) መንግሥት የራሱን ክስ ይመረምራል፤ ማስረጃውን ያጠናቅራል፣ በችሎት የራሱን ክስ ያቀርባል ማስረጃውንም ራሱ አቅርቦ ይመረምራል ተከሳሹም እንደሁ የራሱን ማስረጃ ያቀርባል፣ ይመረምራል፡፡ በአህጉራዊው አውሮፖ የወንጀል ሥነ ሥርዓት (Inquisitorial procedure) መንግስት የራሱንም ሆነ የተከሳሽ ማስረጃዎችን ይመረምራል፤ ክስ ያቀርባል፤ የራሱንም ሆነ የተከሳሹን ማስረጃ ፍርድ ቤት ያቀርባል፤ ይመረምራል ውሳኔም ይሰጣል፡፡
- በአንግሎ አሜሪካን የወንጀል ሥነ ሥርዓት አስተሳሰብ ስለወንጀል ጉዳይ ትክክለኛው እውነት ሊገለጥ የሚችለው ሁለቱም ተፎካካሪ ወገኖች እኩል ዕድል አግኝተው ችሎት ባቀረቡአቸው ማስረጃዎች አማካኝነት በሚደረግ ክርክርና ጥያቄ ሲሆን በአህጉራዊው አውሮፖ የወንጀል ሥን ሥርዓት አስተሳሰብ ደግሞ እውነት የሚወጣው በችሎት በሚደረግ ክርክር ሳይሆን በወንጀል ምርመራ ሒደት ነው፡፡
- ልዩ በሆነ ሁኔታ ሲታይ ደግሞ በአንግሎ አሜሪካ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ደንብ መሠረት ማስረጃ ለችሎት የማቅረብ ግዴታ፣ የቀረቡትን ምስክሮች በችሎት የመጠየቅ ግዴታ የእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ሲሆን የምስክሮችን ተራ የመወሰን መብቱም የእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ነው፡፡ የተከላካዩ ጠበቃ ሚናም ከፍተኛ ነው፡፡ በአህጉራዊው አውሮፖ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ደንብ መሠረት ደግሞ ማስረጃዎችን

የመጥራት፣ የማስቀርብ እና የመጠየቅ እንዲሁም የከሳሽንም ሆነ የተከሳሽን ምስክሮች አቀራረብ ተራ የመወሰን ሥራ የዳኛው ነው፡፡ የጠበቃ ሚና ውስን ነው፡፡ በዚህም መሠረት የሁለቱም ሥነሥረዓቶች መሠረታዊ ግብ ተመሳሳይ ቢሆንም (ማለትም እውነቱን አንጥሮ በማውጣት አጥፊን ብቻ መቅጣትና ያላጠፋውን በነፃ ማሰናበት) ወደዚህ ግብ በመድረስ ረገድ የተለየዩ መንገዶችን ይከተላሉ፡፡

*__መወያያ ጥያቄዎች__*.

ከላይ ከተገለፁት ሁለት የወንጀል ሥነ ሥርዓት ዓይነቶች አንፃር የኢትዮጵያ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ወደየትኛው ሊመደብ የችላል?

## 4.2 *__ማስረጃን የማቅረብ ግዴታ__*

ማስረጃን የማቅረብ ግዴታ "የማስረዳት ሸክም" (Burden of Proof) የሚለው ጽንስ ሀሳብ አንዱ ክፍል ነው፡፡ "የማስረዳት ሸክም" በመሠረቱ ሁለት ጽንሰ ሀሳቦችን ያዘለ ሲሆን እነርሱም፡፡

- ❖ ማስረጃ ለፍርድ ቤት የማቅረብ ግዴታ (Burden of Production) እና
- ❖ የማሳመን ሸክም (Burden of persuasion) ናቸው

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ማስረጃ ለማቅረብ ግዴታን (Burden of Production) ሲሆን ሁለተኛውና የማሳመን ሸክምን (Burden of persuasion) ደግሞ ስለማስረጃ ምዘና በሚመለከተው በምዕራፍ 6 ላይ ይገለፃል፡፡

ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ማስረጃ ማቅረብ የሚገባው ማን ነው? የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ይህም በሚከተለው አጠቃላይ መርህ የሚመራ ነው፡፡ ይኸውም ማስረጃ ሊቀርብበት በሚያስፈልገው አንድ ፍሬ ነገር ላይ ማስረጃ ማቅረብ የሚገባው ማስረጃ ሳይቀርብ ቢቀር በክርክሩ ተሸናፊ የሚሆነው ወገን ነው፡፡ በወንጀል ጉዳይ ሲሆን ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የሚወድቀው (በእምነት መሠረት ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታ ከሌለ ማለት ነው) በከሳሽ ዐቃቤ ህግ ላይ ነው፡፡ ተከሳሹ ማስረጃ ሊያቀርብ የሚገደደው ዐቃቤ ህጉ ማስረጃ አቅርቦ ካሳመነ ፍርድ ቤቱም በበቂ ሁኔታ አስረድቷል የሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ በኍላ ነው፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ

ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 136(1) ላይ "ዐቃቤ ህግ ክሱን ሲከፍት" የሚለው አገላለፅ፣ እንዲሁም በቁጥር 141 ላይ " ዐቃቤ ህጉ ማስረጃውን አስምቶ ከጨረሰ በኃላ" የሚለው ይህንን ያረጋግጣል፡፡

ስለዚህ፦

በወንጀል ጉዳይ ማስረጃ በቅድሚያ የማቅረብ ግዴታ ምን ጊዜም የዐቃቤ ህጉ ነው፡፡ በወንጀል ጉዳይ የማስረዳት ሽክም ወደ ተከሳሹ የሚዞርበት ሁኔታ የለም፡፡ በተለይ የማስረዳት ሽክም ወደ ተከሳሹ የሚዞርበት ሁኔታ (በወንጀል ጉዳይ ማለት ነው) የተደነገገው በፌዴራል የፀረ ሙስና ሥነ ሥርዓት የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 236/93 ላይ ነው፡፡

በፍትሐብሔር ጉዳይ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታን የሚመራው ከላይ የተገለፀው መርህ የተፃሚነት አለው፡፡ በመሠረቱ ማስረጃ በመጀመሪያ በማቅረብ ማስረዳት የሚገባው ምንም ማስረጃ ባያቀርብ ተሸናፊ የሚሆነው ወገን ነው፡፡ ማስረጃ ማቅረብ የሚገባው ማን ነው የሚለውን በተመለከተም በፍ.ብ.ህ ላይ በየቦታው ተሰበጣጥረው የተቀመጡ ድንጋጌዎችን እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ ያህል በቁጥር 5፣ 196(2)፣ 896፣ እና 2001 ላይ የተደነገገውን መመልከት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ኑዛዜ አለኝ የሚል ወገን ይህ ኑዛዜ መኖሩና ይዘቱንም በተመለከተ የማስረዳት ሽክም አለበት፡፡ ውል አለ የሚል ወገንም ውሉ መኖሩን የማስረዳት ሽክም አለበት፡፡ በተጨማሪም በፍትሐብሔር ጉዳይ ማስረጃ የማቅረብ ሽክም ሁል ጊዜ ተሸካሚ የሚሆነው ከሳሽ ነው ማለት አይቻልም፡፡ በዚህም መሰረት

- ❖ ተከሳሽ ያቀረበበትን ክስ ተከሳሽ አምኖ ነገር ግን ህጋዊ መከላከያ የአቀረበ እንደሆነ ማስረጃ የማቅረብ ሽክሙ ወደ ተከሳሹ ይዞራል (የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት) ህግ ቁጥር 258 (1)፡፡
- ❖ ከሳሽ ለአቀረበው ክስ ተከሳሹ ክሱን አምኖ የማቻቻያ ጥያቄ የአቀረበ እንደሆነ የማቻቻያ ጥያቄውን በሚመለከት (ከሳሹም የማቻቻያ ጥያቄውን የተቀበለው ካልሆነ በቀር) የማስረደት ሽክሙ የተከሳሹ ይሆናል፡፡
- ❖ ከሳሹ ክሱን ሲያቀርብ ያስረዱልኛል በሚል የዘረዘራቸው ሰነዶች በተከሳሹ እጅ የሚገኙ መሆናቸውን ጠቅሶ እያለ ተከሳሹ ማስረጃው በእጁ መኖሩን ሳይክድ ነገር ግን ለማቅረብ ፈቃደኛ ካልሆነ የማስረዳት ሽክሙ ወደርሱ ይዞራል፡፡

## 4.3 ማስረጃ ስለሚቀርብበት ጊዜና ሁኔታ

### 4.3.1 የምስክሮች አቀራረብ

አጠቃላይ በሆነ አገላለፅ በማስረጃነት የሚቀርቡ ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር፤ ወይም ለዚህ ፍሬ ነገር አግባብነት ላለው ሌላ ፍሬ ነገር አግባበነት እስከአለው ድረስ የመመስከር ብቃት አላቸው፡፡ የእንግሎ አሜሪካ የህግ ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች ውስጥ የተደነገጉት ማስረጃን ብቃት የለውም የሚያሰኙ የተለያዩ ምክንያቶችን በአገራችን በቀጥታ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ማለት አይቻልም፡፡ ዋናው ነገር ምስክሩ ሊመሠክር ስለመጣበት ጉዳይና ስለሚጠየቀው ጥያቄ የመረዳት ችሎታው ነው፡፡ በአዕምሮ መናወጽ፣ በአካል ላይ በደረሰ ጉዳት የተነሳ ለመረዳት አለመቻል ወይም ተፈላጊውን ፍሬ ነገር ለመግለፅ ባለመቻል (በንግግርም ሆነ በምልክት መግለፅ የማይቻል) ካልሆነ በቀር መመስከር ይችላል፡፡ ስለዚህም አዘውትረው በመቃወሚያነት የሚቀርቡት፣

- ❖ ህፃናት ስለሆኑ ሊመሰክሩ አይገባም (የዉልና የኑዛዜ ጉዳዮች የተጠበቁ ሆነዉ)
- ❖ ከተከራካሪ ወገኖች ጋር ፀብ ወይም ዝምድና ያላቸው ስለሆነ ሊመሰክሩ አይገባም፣
- ❖ አብረን በግብር አበርነት የተከሰስን በመሆኑ ለመመስከር ብቁ አይደሉም

የሚሉ መቃወሚያዎች ተቀባይነት የላቸውም፡፡ እነዚህ የመቃወሚያ ነጥቦች ማስረጃን በመመዘን ረገድ የራሳቸው ድርሻ የሚኖራቸው ቢሆንም (ይህም በምዕራፍ 7 ላይ እንመለከተዋለን) ማስረጃዎች ብቃት የላቸውም ለማስባል ግን አይችሉም፡፡

ይህ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ግን በህጋችን የተደነገጉትን የሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡

- ❖ በወንጀል ሕግ ላይ እንደተደነገገው አንድ ሰው በፈፀመው ወንጀል ምክንያት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተላለፈበት፣ ፍርድ ቤቱ ከሚወስነው መደበኛ ቅጣት በተጨማሪ የምስክርነት መብቱን ሊያግደው የሚችል ሲሆን ፍርድ ቤቱ እንዲህ አይነት ቅጣትን ሲወስን ምስክሩ የመመስከር ብቃቱን ያጣል፡፡

❖ በምስክርነት የተቆጠሩት ሰዎች ልዩ እውቀት ያላቸው (ኤክስፐርቶች) ከሆኑ ለምስክርነት ሊቆሙ የሚችሉት ተፈላጊው ዕውቀት እንዳላቸው ማረጋገጫ ሲገኝ ነው፡፡ ማረጋገጫው የእውቀት ደረጃቸውን አስከምን ደረጃ ድረስ እንደሆነ ሊያረጋግጥ ይገባል የሚለው እንደተያዘው ጉዳይ የሚለያይ ሲሆን ነገር ግን ባለሞያ ያስረዳዋል በተባለው ፍሬ ነገር ወይም ይገልፃዋል ከተባለው አስተያየት አኳያ የባለሞያነት ማረጋገጫ ከሌለው ምስክር ለመሆን ብቃት የለውም ለማለት ይቻላል፡፡

በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር ምስክሮች መቼ ይቀርባሉ ለሚለው ጥያቄ መልሱ ተመሳሳይ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በወንጀል ጉዳይ ዐቃቤ ህጉ ክስ ሲያቀርብ ያስረዱልኛል የሚላቸውን ምስክሮች ስም ዝርዝር አያይዞ ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን በፍትሐብሄር ጉዳይም ከሳሽ ክሱን ሲያቀርብ የምስክሮቹን ስም ዝርዝር ከክሱ ጋር አባሪ በሆነ ጽሑፍ ገልፃ ማቅረብ ይገባዋል፡፡ ተከሳሹም እንዲሁ መልሱን ሲያቀርብ ከመልሱ ጋር አባሪ በሆነ ጽሑፍ ያስረዱልኛል የሚላቸውን ምስክሮች ስም ዝርዝር ገለጾ ማቅረብ አለበት፡፡ (የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 124፣ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 222-223፣ 234)፡፡ በዚህም መሠረት በህግ በተፈቀደ ልዩ ሁኔታ ካልሆነ በቀር (የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 256(1) እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 143) በመጀመሪያ ዝርዝራቸው ለፍርድ ቤቱ ገቢ ያልተደረገ ምስክሮች ሊቀርቡ አይገባም፡፡ ለማጠቃለል ጉዳዩ ወንጀልም ሆነ ፍትሐብሔር፤

❖ ዝርዝሩ ማስረጃ ከመስማቱ በፊት ለፍርድ ቤቱ ሊቀርብ ይገባል፡፡
❖ ነገሩ ሲሰማ (ማለትም ማስረጃ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ) ግራ ቀኙ ለቆጠሯቸው ምስክሮች መጥሪያ አውጥተው አድርሰው አቅርበው ማሰማት ይገባቸዋል፡፡
❖ መጥሪያ ደርሶአቸው ያልቀረቡ ምስክሮች ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተገድደው ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡
❖ በዝርዝሩ ያልተጠቀሱ ምስክሮች እንዲቀርቡ እንደመብት መጠየቅ የማይቻል ሲሆን ሊፈቀድ የሚቻለው መቅረባቸው ለትክክለኛ ፍርድ አስፈላጊ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አምኖ የፈቀደ እንደሆነ ነው፡፡

***<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. የሚከተለውን ጉዳይ መርምራችሁ አስተያየት ስጡበት፣

"ዐቃቤ ህግ ተከሳሽ ሰውን በግፍ ገድሎአል በሚል ለአቀረበው ክስ ሰባት ሰዎች በምስክርነት በመጥራት ዝርዝራቸውን የአቀረበ ሲሆን ምስክሮች እንዲቀርቡ በተቀጠረበት ዕለት ሁለቱ ቀርበው "ድርጊቱ ሲፈፀም አልነበርንም፣ አናውቅምም" በማለት መስክረዋል፡፡" ዐቃቤ ህጉ " ቀሪዎቹን ፈልገን ማግኘት ስላልቻልን ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶ እንድናቀርብ ይታዘዝልን" በማለት ጠይቋል፡፡ በዚሁ መሠረት ለተለዋጨ ቀጠሮ ቀሪዎችን ምስክሮች አንዲያቀርብ ትዕዛዝ የተሰጠ ቢሆንም በተለዋጨ ቀጠሮም ምንም ምስክር አልቀረበም ዐቃቤ ሕጉ ተመሳሳይ ምክንያት በመስጠት ለ3ኛ ጊዜ  አንድናቀርብ ይታዘዝልኝ ሲል የጠየቀ ሲሆን ተከሳሹ በበኩሉ ለረጅም ጊዜ ታስሮ መቆየቱን በመጥቀስ በተሰማው ምስከር ብቻ ብይን እንዲሰጥ ጠይቋል፡፡ (ከጠቅላይ ፍርድ ቤት የወ.ይ.መ.ቁ... የተወሰደ)፡፡  ፍርድ ቤቱ ምን ዓይነት ትዕዛዝ ሊሰጥ ይገባል?

2. በውል ጉዳይ ምስክር እንዲሆኑ የሚመረጡ ሰዎች አካለ መጠን ያደረሱና ያልተከለከሉ መሆን እንደሚገባቸው በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1729 ላይ የተደነገገ ሲሆን ኑዛዜን በተመለከተም በዚሁ ህግ ቁጥር 892 ላይም በተመሳሳይ ተደንግጉአል፡፡ ይህ ምን ማለት ነው?  እድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላቸው ህፃናት በውሉ ወይም በኑዛኔው ላይ በምስክርነት የተፃፉትና የፈረሙ ቢሆን በውሉ ወይም በኑዛዜው ጉዳይ በምስክርነት ለመቅረብ ብቃት የላቸውም ማለት ይቻላል?

## 4.3.2 የሰነዶችና ኢግዚቪቶች አቀራረብ

በተለመደው የአገራችን የፍርድ ቤቶች አሠራር የወንጀል ጉዳይን በሚመለከት ሰነዶችና ማስረጃ የሚሆኑ ሌሎች ነገሮች  ለፍርድ ቤት የሚቀርቡት ምስክሮች ከተሰሙ በኃላ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ዐቃቤ ህግ ስለሰነድ ማስረጃ ሲጠየቅ ምስክሮች ከተሰሙ በኃላ አንደሚያቀርብ የሚገልፅ ሲሆን ስለኢግዚቪት ማስረጃ ሲጠየቅ ደግም "ፖሊስ ጋ ስለሚገኙ እንዲያቀርባቸው ለፖሊስ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ" በሚል እያሳሰበ

ፖሊስ በታዘዘው መሠረት ኢግዚቪቶችን አላቀረበም እየተባለ ተደጋጋሚ ትዕዛዝ የሚሰጥበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ ይህ ትክክለኛ የማስረጃ አቀራረብ ነውን? የሚለውን ደግሞ ከህጉ ጋር በማገናዘብ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 124 ላይ እንደተደነገገው ነገሩ በሚሰማበት ቀን መረጃዎች (ኤግዚቪቶች) ሁሉ ፍርድ ቤት መቅረብ ይገባቸዋል፡፡ ከየት ነው የሚቀርቡት? ለሚለው ደግሞ ቁጥር 97 መልስ ይሰጣል፡፡ ቁጥር 97 መረጃዎች (ኢግዚቪቶች) እና የተከሳሽነት እና የምስክር ቃሎች ፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ቀርበው መዝገብ ቤቱ ተረክቦ ቁጥርና ምልክት እንደሚያደረግባቸው ከዚያም በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት በተጠበቀ ሥፍራ እንደሚጠበቁ የሚወጡትም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብቻ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ እነዚህ መረጃዎች የተሰጣቸውን ቁጥርም በወንጀል መዝገቡ ውስጥ እንደሚመዘገብ ቁጥር 97(1)( በ) ያመለክታል፡፡ በዚህም መሠረት

- ❖ ሰነዶች እጅግ ቢዘገይ የክስ ማመልከቻው ፍርድ ቤት ሲቀርብ አብረው መቅረብና መዝገብ ቤት መቀመጥ የሚገባቸው ሲሆን፣ ለማስረጃነት ሲፈለጉም በዳኞች ትዕዛዝ ወጪ ይደረጋሉ፡፡
- ❖ ኢግዚቪቶችም አስቀድመው ፍርድ ቤት ቀርበው በተጠበቀ ስፍራ መቀመጥ የሚገባቸው ሲሆን ለማስረጃነት ሲፈልጉም የሚቀርቡት ከዚሁ ነው፡፡

በፍትሐብሔር ጉዳይም ተከራካሪ ወገኖች ይጠቅመኛል ወይም ያስረዳልኛል የሚሉትን ሰነድ ከአቤቱታዎቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ ይገባቸዋል (የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 137(1)፣ 223(1)(ለ)፣ 234(1))፡፡ በልዩ ሁኔታ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ካልፈቀደ በስተቀር (ቁጥር 256(1)፣ 145(1)፣ 115፣ 119፣ 264) ዘግይተው ሊቀርቡ አይችሉም፡፡ ማስረጃው በእጅ የማይገኝ ከሆነ በትዕዛዝ እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱን መጠየቅ የሚቻል ሲሆን (ቁጥር 145)፣ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ መጥሪያ ከመስጠቱ በፊት ይህ ማስረጃ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት ይገባዋል፡፡ በትዕዛዝ እንዲቀርብለት የጠየቀው ተከሳሹ ከሆነም መልሱን ከመስጠቱ በፊት ፍርድ

ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቶ ማስረጃውን እንዲያስቀርብለት መጠየቅ ይኖርበታል፡፡ ፍርድ ቤቱም በዚሁ መሠረት ማስረጃው እንዲቀርብ ትዕዛዝ እንደሚሰጥ ይጠበቃል፡፡

# ምዕራፍ 5

# ምስክሮችን ስለመመርመር

**ዝርዝር አላማዎች**

ሰልጣኞች ይህንን ምእራፍ ሲያጠናቅቁ ፣

- ስለምስክሮች ምርመራ በቂ እዉቀት አግኝተዉ ሥራ ላይ ያዉላሉ፤
- ምስክሮች ስለሚመረመሩበት ሥርዓት በቂ ግንዛቤ አዳብረዉ ሥራ ላይ ያዉላሉ፤
- ምስክሮች በሚመረመሩበት ወቅት ሊወሰድ ስለሚገባዉን ጥንቃቄ ተረድተዉ ሥራ ላይ ያዉሉታል፡፡
- ዋና ጥያቄ፣ መስቀለኛ ጥያቄ እና ድጋሚ ጥያቄ የሚቀርብበትንና የሚጠየቅበትን ሥርዓት አዉቀዉ ተግባር ላይ ያዉላሉ፡፡

## 5.1. ጠቅላላ

ዉድ ሠልጣኞች ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ በሆነው ፍሬ ነገር ላይ ሊያስረዱ የሚችሉ ማስረጃዎች ፍርድ ቤት የሚቀርቡበት ሁኔታ ተገልፆአል፡፡ ማስረጃን ማን፣ እንዴትና መቼ ማቅረብ እንደሚገባውም ተጠቅሶአል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የቀረቡት ማስረጃዎች እንዴት አንደሚመረመሩ ማለትም ተፈላጊውን ፍሬ ነገር ለፍርድ ቤቱ እንዴት እንደሚያስረዱ ይገልፃል፡፡ በመሠረቱ ፍሬ ነገርን ለማስረዳት የሚቀርቡት ምስክሮች ብቻ ሳይሆኑ ሰነዶች እና ሌሎች ገላጭ ማስረጃዎች ጭምር ቢሆኑም ነገር ግን ምስክሮች የሚመረመሩበት ሥርዓት ለየት ያለ በመሆኑ በምስክሮች ቃል አቀባበል ሁኔታ ላይ ይህ ምዕራፍ እንዲያተኩር ተደርጐአል፡፡ ምስክሮች በማስረጃነት ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ማስረጃ ተብሎ የሚቆጠረው በችሎት የሰጡት ቃል በመሆኑና በውሳኔ ጊዜም የሚመረመረው ይኸው ምስክሮች የሰጡት ቃል በመሆኑ የምስክሮች ቃል አቀባበል መሠረታዊ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ችሎአል፡፡

ወደ ዋናው ጉዳይ ከመገባቱ በፊት ግን የሚከተሉት ሁለት ነጥቦች ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡

- ❖ በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር ጉዳይ ምስክሮች የሚመረመሩበት ሁኔታ የተወሰነ ልዩነት ቢኖረውም በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በሁለቱም ጉዳዮች ምስክሮች ዋና ጥያቄ፣ መስቀለኛ ጥያቄ፣ እና ድጋሚ ጥያቄ ይጠየቃሉ፡፡ ዳኞችም አስፈላጊ በሆነ ጉዜ በፍትሀብሄርም በወንጀል ክስ ለምስክሮች ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
- ❖ በኢትዮጵያ የወንጀልም ሆነ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጐች መሠረት ምስክሮችን ችሎት የማቅረብ፣ የቀረቡት ምስክሮች የሚያስረዱትን ፍሬ ነገር የማስመዝገብ እና የመመርመር ወይም የመጠየቅ መብቱም ግዴታውም የተከራካሪ ወገኖች ነው፡፡ ፍርድቤቱ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በራሱ አነሳሽነት ማስረጃ የማስቀረብና ራሱም ሆነ ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡአቸውን ምስክሮች የመጠየቅ ሥልጣን ቢኖረውም ዋነኛው ግዴታ የሚወድቀው ግን በተከራካሪ ወገኖች ላይ ነው፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ የአንግሎ አሜሪካን የወንጀል ሥነ ሥርዓት አካሔድ (Adversarial Procedure) የሚከተል ነው ማለት ይቻላል፡፡

## *5.2. ምስክሮች በተከራካሪ ወገኖች ፊት ቀርበው መመስከር የሚገባቸው ስለመሆኑ*

ምስክሮች ቃላቸውን የሚሰጡበትና የሚመረመሩት ተከራካሪ ወገኖች ባሉበት መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ጉዳዩ ወንጀልም ሆነ ፍትሐብሔር በመሠረቱ ልዩነት የለውም፡፡ ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ እንዲሰማ የታዘዘ በሆነ ጊዜ(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.70(ሀ) እና የወ.መ.ህ.ሥ.ሥ.ቁጥር 161 ይመለከታል) ምስክሮች ተከሳሽ በሌለበት ሊቀርቡ የሚችሉ ቢሆንም ነገር ግን ችሎት ቀርበው ቃላቸውን መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም አንድ ምስክር የሰጠው የምስክርነት ቃል እውነተኛነት ወይም ሐሰተኛነቱ፣ እርግጠኛነቱ ወይም አጠራጣሪነቱ የሚፈተነው በሚቀርብለት መስቀልኛ ጥያቄ በመሆኑና ይህ ሊፈፀም የሚችለውም ምስክር በችሎት የቀረበ ከሆነ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡

በተጨማሪም በወንጀል ጉዳይ ሊመሠከሩበት የቀረቡበትን ምስክሮች መመርመር የተከሳሹ ህገ-መንገሥታዊ መብት በመሆኑ ነው(የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ-መንግስት አንቀጽ 19(4))። ስለዚህ ምስክር ተከራካሪ ወገን ባለበት ቀርቦ ማንነቱን አረጋግጦ የምስክርነት ቃሉን ሊሰጥ ይገባዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በወንጀል ጉዳይ በዐቃቤ ህግ በኩል የተቆጠረ ምስክር በተከሳሹ ፊት ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን መስጠቱ ወይም የቀረበ ቢሆን እንኳ ማንነቱንና አድራሻውን በተከሳሹ ፊት መግለፁ ለደህንነቱ አላስፈላጊ ሁኔታ የሚፈጥርበት ቢሆንስ? ተከሳሹ ሳያየውና ማንነቱንና አድራሻውን ሳይገልፅ የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ሊደረግ ይችላልን? የሚለው ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። በዚህ ጭብጥ ላይ ሌሎች አገሮች አዲስ አሠራር እየተከተሉ ይገኛሉ። በዚህም መሠረት በእንግሊዝ ህግ የዐቃቤ ህግ ምስክር ማንነቱን በግልፅ ሳይናገር ወይም በአካል ችሎት ቀርቦ ሳይታይ የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥበት ሁኔታ ያለ ሲሆን ይህም፡-

- ✓ ችሎት ቀርቦ ማንነቱንና አድራሻውን ተከሳሹ እየሰማ ከመናገር ይልቅ በጽሑፍ ለፍ/ቤቱ በመግለፅ፣ ወይም
- ✓ በተለየ ሁኔታ ደግሞ በችሎት ሳይገኝ የምስክርነት ቃሉን ሊሰጥ ይችላል(May ,p 433) ።

እንዲህ ዓይነት ምስክርነት እንዲሰጥ የመወሰን ስልጣኑ የፍ/ቤቱ ሆኖ ነገር ግን ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት፡-

- ✓ ምስክሩ ተጨባጭ የሆነ ስጋት ያለበት መሆኑ፣
- ✓ ምስክሩ የሚሰጠው ቃል ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለውና የምስክርነት ቃሉን ሳይሰጥ ቢቀር ፍትህን የሚያዛባ መሆኑን፣ እና
- ✓ ምስክሩ ችሎች ሳይቀርብ ምስክርነቱን ቢሰጥ በተከሳሹ ላይ ከባድ ተፅዕኖ የሚያሳድር አለመሆኑን ማረጋገጥ አለበት (May p.433)

***<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በኢትዮጵያ ምስክር ችሎት ሳይቀርብ ወይም ቀርቦ ማንነቱን ሳይገልፅ የምስክርነት ቃሉን ሊሰጥ ይችላል?
2. የማስረጃ አቀባበልን በተመለከተ የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁጥር 261(3) ድንጋጌ "ፍርድ ቤቱ በቂ ነዉ ሲል መዝግቦ በሌላ ሁኔታ እንዲፈፀም ካላዘዘ በቀር ምስክሮች የምስክርነት ቃል የሚሰጡት በጽሁፍ ሳይሆን በችሎት ፊት ቀርበዉ በግልጽና በቀጥታ ነዉ" ሲል ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምንድነው? ከቁጥር 121 አንፃር እንዴት ሊገናዘብ ይገባል?

## 5.3 *ምስክሮች ስለሚመረምሩበት ሥነ-ሥርዓት*

### 5.3.1 ጭብጥን ስለመያዝ

ዉድ ሠልጣኞች በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር ጉዳይ በማስረጃነት የሚቀርብ ማናቸውም ማስረጃ ውሳኔ ስለሚሰጥበት ጉዳይ አግባብነት ሊኖረው እንደሚገባ በምዕራፍ 3 ላይ ተገልፆአል፡፡ ማስረጃው አግባብነት እንዳለው ለመወሰን ደግሞ አስቀድሞ ውሳኔ የሚሰጥበት ተፈላጊውና አከራካሪው ፍሬ ነገር ተለይቶ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ይህ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው አከራካሪውና ይቀርባል የተባለው ማስረጃ ጭብጥ በመባል የሚታወቅ ሲሆን ማስረጃው ከመቅረቡና ከመስማቱ በፊት አስቀድሞ መታወቅ አለበት፡፡ ይህ በወንጀልም ሆና በፍትሐብሔር ጉዳይ መፈፀም ያለበት ሲሆን የጭብጥ አያያዝ መሠረቶችም በዚያው በምዕራፍ 3 ላይ ተመልክተዋል፡፡

### 5.3.2 ለምስክሮች ስለሚደረግ ምርመራ

ምስክር ችሎት ሲቀርብ (በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር) ማንነቱን እና አድራሻውን ካስመዘገበ እና መሃላ ከፈፀመ ወይም እውነት ለመመስከር ካረጋገጠ በኋላ ጥያቄ፣ የሚቀርብለት ሲሆን የሚቀርቡለት ጥያቄዎችም ዋና ጥያቄ፣ መስቀልኛ እና ድጋሚ ጥያቄ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፍ/ቤቱም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማናቸውም ጊዜ

ምሰክሩን ሊጠይቀው ይችላል፡፡ ቀጥሎ ዋና ጥያቄ መስቀልኛ ጥያቄ እና ድጋሜ ጥያቄ ላይ መሠረዊ ነጥቦች ይገልፃሉ፡፡

ሀ. **ዋና ጥያቄ**

ዋና ጥያቄ የሚባለው ምስክሩን የአቀረበው ወገን በመጀመሪያ የሚያቀርበው ጥያቄ ነው፡፡ አላማውም ምስክሩን የጠራው ወገን በክርክሩ ያለውን አቋም እንዲደግፍለት ማድረግ ሲሆን ምስክሩም በጭብጥ ስለተያዘው ፍሬ ነገር በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚያውቀውን ያስረዳል፡፡ ከዚህ አንፃር፣

- ✓ በምስክር ምርመራ ሂደት ዋና ጥያቄ ወሳኝ ወይም መሠረታዊ ነው፡፡ ዋና ጥያቄ ከሌለ መስቀልኛም ሆነ ድጋሚ ጥያቄ አይኖርም፡፡
- ✓ በዋና ጥያቄ ላይ የመምራት ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም፡፡
- ✓ እንዲሁም ምስክር አቅራቢው በመሠረቱ የራሱን ምስክር ዋና ጥያቄ ሲጠይቅ የማስተባበል ጥያቄ ሊጠይቀው አይገባም፡፡

**የመምራት ጥያቄ** ሲባል

- ✓ ጥያቄ አቀራቢው እንዲመለስለት የሚፈልገውን መልስ የሚጠቁም፤ ወይም
- ✓ አስቀድሞ ምሰክሩ መልስ ሰጥቶበት ያላረጋገጠውን ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ በመቁጠር በዚህ ላይ በመመስረት የሚቀርብ ጥያቄ ለማመልከት ነው፡፡

በዋና ጥያቄ ላይ የመምራት ጥያቄ መጠየቅ ተገቢ የማይሆነው፣

- ✓ ምስክር አቅራቢው ወገን ምስክሩ ደግፎት ይመሠክራል ተብሎ የሚጠበቅ ስለሆነ እንዲመለሰለት የሚፈልገውን መልስ በጥያቄ መልክ ለምስክሩ ካቀበለ ምስክሩ የሚያውቀውን ሳይሆን ምስክር አቅራቢው የሚፈልገውን ምስክርነት እንዲሰጥ የሚያደርግ ስለሆነ፣
- ✓ ምስከሩ ያላረጋገጠውን ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ በመቁጠር ወይም በማስመሰል በማለፍ ወሳኝ የሆነ ፍሬ ነገር መኖር አለመኖሩ ሳይታወቅ መታለፍና ስህተት መፍጠር ስለሌለበት ነው(Hermann ,p-z)

የማስተባበያ ጥያቄ መጠየቅ በመሠረቱ የተከለከለውም ምስክር አቅራቢው ወገን ምስክሩን ያቀረበው ያስረዳልኛል በሚል በመሆኑና ያቀረበው ምስክር ደግፎት እንደሚመሠክር የሚጠበቅ ሲሆን ራሱ ያቀረበው ምስክር የሰጠው መልስ ትክክለኛ አለመሆኑን ወይም የሚያጠራጥር መሆኑን ወይም አስቀድሞ ከሰጠው ቃል ጋር የሚጋጭ መሆኑን የሚያመለክት ጥያቄ መጠየቅ ምስክሩ ሲያቀርብ ከተገመተው ግምት ጋር የሚጋጭ ነው፡፡ እውነት ይናገራል ብሎ ያቀረበውን ምስክር ሐሰተኛ መሆኑን እንዲገልፅ ማድረግ እርስ በርሱ የሚጋጭ ነው፡፡ ሆኖም በተወሰኑ ሁኔታዎች የማስተባበል ጥያቄ በዋና ጥያቄ ላይ የሚቀርብበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይኸውም

- ✓ ምስክሩ ለመመስከር ፈቃደኛ ያልሆነበት ሁኔታ ወይም
- ✓ አስጠቂ (hostile)በሆነ ጊዜ ነው፡፡

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁጥር 145 ምስክር በፖሊስ ምርመራ ጊዜ የሰጠው የምስክርነት ቃል ፍርድ ቤት ሊመለከተውና ለትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥ የሚጠቅም መስሎ ከታየው የተከሳሹ ቃል ግልባጭ ደርሶት ምስክሩ የሰጠውን ቃል ለማስተባበል እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ለምሳሌ አቃቤ ህጉ ለምስክርነት የጠራው ሰው በሚመሰክርበት ጊዜ በፖሊስ ምርመራ ጊዜ ከተሰጠው ምስክርነት ጋር የማይጣጣም ከሆነ ይህ የምስክርነት ቃል እንዲቀርብ በማድረግ ምስክሩን ተአማኒ እንዳልሆነ እራሱ አቃቤ ህጉ ጥያቄ እንዲጠይቅ ሊፈቅድ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ የፀረሙስና ሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 40 ላይም ይህ ተደንግጉአል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር ምስክሩ መጀመሪያ ሲጠየቅ በሰጠው መልስና በማስተባበያ ጥያቄ ጊዜ በሰጠው መልስ መካከል ልዩነት ቢፈጠር የትኛው ተቀባይነት ይኖረዋል? የሚለው በማስረጃ ምዘና ወቅት የሚታይ ይሆናል (ምዕራፍ 7 ተመልከት)፡፡

## ለ. መስቀለኛ ጥያቄ

መስቀለኛ ጥያቄ ምስክሩን የአቀረበው ወገን ዋና ጥየቂ ጠይቆት እንደአበቃ ሌላኛው ወገን የሚያቀርበው ጥያቄ ነው፡፡ ዓላማዎቹም

- ✓ ምስክሩ ለዋና ጥያቄ በሰጠው መልስ ውስጥ ሐሰተኛ፣ የማይታመን ወይም አጠርጣሪ ቃል መኖሩን መለየት፣
- ✓ እንዲሁም ከዚሁ ምስክር ላይ መሰቀለኛ ጥያቄ ጠያቂው ሌሎች ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ማስቻል ናቸው፡፡

መስቀለኛ ጥያቄን በተመለከተ የሚከተሉት ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡

- ✓ መስቀልኛ ጥያቄ  ዋነኛ ዓላማው በዋና ጥያቄ ላይ የተሰጠውን መልስ ሀሰተኛነት አጠራጣሪነት ወይም የማይታመነ መሆኑን ማሳየት በመሆኑ የዋና ጥያቄ መኖርን ግድ ይላል፡፡ ምስከር አቅራቢው የራሱን ምስከር አልጠይቀውም፤ አልፈልገውም ያለ እንደሆነ መስቀልኛ ጥያቄ አይቀርብም፡፡
- ✓ በመስቀልኛ ጥያቄ ጊዜ የመምራት ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡
- ✓ የመስቀልኛ ጥያቄ አግባብነት የሚለካው በዋና ጥያቄ ጊዜ ከተጠየቀ ጥያቄ ሳይሆን ለጥያቄው ከተሰጠው መልስ አንፃር ነው፡፡

እንደ አጠቃላይ በዋና ጥያቄ ከሰጠዉ መልስ አንፃር ይጠየቃል፡፡

<u>ሐ. ድጋሚ ጥያቄ</u>

ምስክሩን የአቀረበው ወገን ምሰክሩ መሰቀልኛ ጥያቄ ተጠይቆ ከአበቃ በኃላ የራሱን ምስክር ለሁለተኛ ጊዜ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው፡፡ ድጋሜ የተባለውም ምስክር አቅራቢው ለሁለተኛ ጊዜ ምስክሩን ስለሚጠይቀው ነው፡፡ ዓላማውም በመስቀልኛ ጥያቄ የተነሳውን ነገር ለማጣራት ነው፡፡ ድጋሚ ጥያቄን በተመለከተም

- ✓ መስቀልኛ ጥያቄ ያልተጠየቀ ከሆነ ድጋሚ ጥያቄ ሊቀርብ አይገባም፡፡
- ✓ የመምራት ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም፡፡
- ✓ ለመስቀልኛ ጥያቄ ምስክሩ የሰጠውን መልስ ማጣራትን ብቻ የሚመለከት ነው፡፡

***<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>***

በወንጀል ጉዳይ በዋና ጥያቄ ጊዜ የመምራት ጥያቄ እንዲቀርብ ዐቃቤ ህጉ በፍትሐበሔር ጉዳይ ደግሞ ፍ/ቤቱ ሊፈቅዱ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች ምንድናቸው?

# ክፍል ሦስት

# ማስረጃን ስለመመዘን

## ምዕራፍ 6

## የማስረጃ አስረጅነት መመዘኛ (ደረጃ)

***ዝርዝር አላማዎች***

ሰልጣኞች ይህንን ምእራፍ ሲያጠናቅቁ ፣

- ሠልጣኞች በወንጀልም ሆነ በፍታብሔር ጉዳይ ማስረጃን መመዘን የሚችሉበትን ክህሎት ያዳብራሉ ይህንን ክህሎት በሥራ ላይም ያዉላሉ፤

ዉድ ሠልጣኞች ይህንን ክፍል ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግላችሁ ሞክሯቸዉ፡፡

ሀ. አስረጅነት መመዘኛዉ (standard of proof) መለኪያዉ ምንድነዉ?
ለ. በአንድ ጉዳይ ላይ የቀረበ ማስረጃ አስረድቷል የሚባለዉ በምን ያህል/ጥራት ሲያስረዳ ነዉ? (ወንጀል ? ፍታብሔር?)

### 6.1. *ጠቅላላ*

የሚቀርበው ማስረጃ ሊያስረዳው ወይም ሊያስተባብለው ለተፈለገው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው መሆኑ፤ እንዲሁም በህግ እንዳይቀርብ ክልከላ ያልተደረገበት መሆኑ ብቻውን ተፈላጊውን ፍሬ ነገር አስረድቷል ወይም አስተባብሏል ለማለት አያስችልም፡፡ አግባብነት የአለው ማስረጃ ሊያስረዳ ከተፈለገው ፍሬ ነገር ጋር ግንኙነት ሊኖረው እንደሚችል የታወቀ ነው፡፡ ምክንያቱም ምንም አግባብነት የሌለው ማስረጃ አስቀድሞም አይቀርብምና፡፡ ይህ ማለት ግን ማስረጃው የተፈለገውን ፍሬ ነገር መኖር አስረድቷል ወይም አስተባብሏል ማለት ላይሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም የቀረበው ማስረጃ ከተፈላጊው እና ውሰኔ ለመስጠት ተገቢ ከሆነው ፍሬ ነገር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ቢኖረውም እንኳን ይህንን ተፈላጊውን ፍሬ ነገር የግዴታ አስረድቷል ወይም አስተባብሏል ማለት

አይደለም፡፡ ከተፈላጊው ፍሬ ነገር ጋር የደበዘዘ ግንኙነት ያለው ማስረጃ እንደሚቀርብ ሁሉ ግንኙነቱ ምን ቢወፍር ደግሞ መቶ በመቶ በርግጠኛነት ያስረዳዋል ወይም ያረጋግጠዋል ለማለት አይቻልም፡፡ ከዚህ አንፃር የቀረበው ማስረጃ ከተፈላጊው ፍሬ ነገር ጋር ያለው ግንኙነት እስከምን ድረስ ነው? ሊያስረዳው የቀረበውን ፍሬ ነገር አስረድቷል ወይስ አላስረዳም? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ማስረጃን መመዘን አስፈላጊ ነው፡፡

የቀረበው ማስረጃ ተፈላጊውን ፍሬ ነገር አስረድቷል ወይስ አላስረዳም? የሚለው ጥያቄ በማናቸውም በፍ/ቤት ለተያዘና ማስረጃም ለቀረበበት ጉዳይ አግባብነት አለው፡፡ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ማስረጃን ከመመርመር አልፎ ከተፈላጊው ፍሬ ነገር አንፃር ማገናዘብ ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም ማስረጃው ሲመዘን የሚደረስበት መደምደሚያ አስረድቷል ወይም አላስረዳም የሚል ከመሆኑ አንፃር ማስረጃው አስረድቷል ለማለት የሚቻለው ምን ሁኔታዎችን ሲያሟላ ነው? የሚለውም ወሳኝ ነጥብ ነው፡፡

ይህ ማስረጃው ተፈላጊውን ፍሬ ነገር አስረድቷል የምንልበት መስመር ወይም ደረጃ የአስረጅነት መመዘኛ (Standard of proof) ይባላል፡፡ ማስረጃው አስረድቷል ወይም አላስረዳም ለማለት የሆነ መመዘኛ ወይም መስመር ማበጀት የሚያስፈልግ ሲሆን ይህንን መመዘኛ የአሟላ ወይም የአለፈ ማስረጀ አስረድቷል የሚባል ሲሆን ያላሟላ ከሆነ ደግሞ አላስረዳም ስለሚባል ይህንን መስመር ወይም መመዘኛ አስቀድሞ መወሰን ያስፈልጋል፡፡

የአስረጅነት ደረጃ ወይም መመዘኛ የሚባለውም ይህንን ጽንሰ ሀሳብ የሚመለከት ነው፡፡ አስረጅነት መመዘኛ (Standard of proof) ከዚህ አንፃር ሲታይ የሚኖረው ትክክለኛ ፍቺ "ከሳሽ (በወንጀል ጉዳይ ከሆነ ዐቃቤ ህጉ) ረቺ ለመሆን እንዲያስችለው በክስ መሰማት ሂደት ሊያቀርብ የሚገባው የማስረጃ መጠን ነው፡፡" ("The amount of evidence which a plaintiff (or prosecuting attorney in a criminal trial) must produce in order to win …") ማለት ነው፡፡ በዚህም መሠረት፡-

- የአስረጅነት መመዘኛ ከሳሽ አሸናፊ ለመሆን ወይም ፍ/ቤቱን ለማሳመን የሚያስችለውን የማስረጃ መጠን የሚመለከት ነው፡፡

- የ 'ማስረጃ' መጠን ሲባል ግን በቁጥር ደረጃን ለመግለፅ ሳይሆን (ማለትም ይህንን ያህል ምስክር፣ ይህንን ያህል ገጽ ሰነድ በሚል ሳይሆን) የማስረጃውን ጥራት ወይም የማስረዳት ብቃት ደረጃ ለማመልከት ነው፡፡
- ይህንን 'መጠን' የአሟላ ከሳሽ አሸናፊ ወይም አስረድቷል ሲባል ካላሟላ ግን አስረድቷል አይባልም፡፡

የአስረጅነት መመዘኛ በሚመለከት በህግ የሚወሰደው አቋም እንደአገሩ የህግ ሥርዓት እና እንደ ጉዳዩ ዓይነት የሚለያይ ነው፡፡ ማለትም የአንግሎ አሜሪካን የህግ ሥርዓት ተከታይ አገሮች ማስረጃን አስረድቷል የሚሉበት መመዘኛ ከአህጉራዊው አውሮፖ የህግ ሥርዓት ተከታይ አገሮች የአስረጅነት ደረጃ ወይም መመዘኛ የሚለይ ሲሆን እንዲሁም ይኸው የአንግሎ አሜሪካ የህግ ሥርዓት የአስረጅንት መመዘኛ እንደ ጉዳዩ ወንጀል ወይም ፍትሐብሄር መሆን የተለየ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ምዕራፍ ተከታይ ክፍሎች

- ማስረጃ አስረድቷል ለማለት ተፈላጊው የአስረጅነት ደረጃ ወይም መመዘኛ በሁለቱ የህግ ስርዓቶች ስላለው ገፅታ እና
- የማስረጃ አስረጅት መመዘኛ በኢትዮጵያ ህግ ያለው ገፅታ ይገለፃል፡፡

## *6.2. የማስረጃ አስረጅነት መመዘኛን በሚመለከት የሌሎች አገሮች አቀራረብ*

### *6.2.1. የአንግሎ አማሪካ የህግ ሥርዓት (Common Law) አቀራረብ*

በአንግሎ አሜሪካ የህግ ሥርዓት ተከታይ አገሮች የማስረጃ አስረጅነት መመዘኛው ለፍትሐብሄርና ለወንጀል ጉዳዮች ተመሳሳይ አይደለም፡፡ የአሜሪካንን (ዩናይትድ ስቴትስ) የማስረጃ ህግ ወስደን ጉዳዮን ብንመረምር ሦስት ዓይነት የአስረጅነት መመዘኛዎች እንዳሉ መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህም፣

- ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት መመዘኛ-ለወንጀል ጉዳዮች የሚያገለግል (Beyond reasonable doubt Standard)

- ግልፅና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ የማስረጃ መመዘኛ (Clear and Convincing Evidence Standard) -ለተወሰኑ የፍትሐብሄር ጉዳዮች የሚያገለግል፡፡
- በተሻለ ሁኔታ ማሳመን የማስረዳት መመዘኛ (Preponderance of evidence) ለአብዛኛው የፍትሐብሄር ጉዳዮች የሚያገለግል መመዘኛ ናቸው፡፡

*ሀ. <u>በወንጀል ጉዳይ የአስረጅነት ደረጃ /መመዘኛ/</u>*

በአንግሎ አሜሪካ የህግ ሥርዓት ተከታይ አገሮች በወንጀል ጉዳይ የአስረጅነት መመዘኛው "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" ማስረዳት ነው፡፡ በወንጀል ጉዳይ ከሳሽ ዐቃቤ ህግ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈፀሙ ምክንያታዊ ጥርጣሬ በማያስነሳ ሁኔታ የማስረዳትና ፍ/ቤቱን (በአብዛኛው ከህዝብ መካከል የተመረጡ ዳኞች ነው በዚህ ላይ የሚወስኑት) ማሳመን ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲባል "ጉዳዩን የሚመለከቱ ዳኞች" በዕለት ተዕለት የኑሮ ሂደት ውስጥ ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚከሰትና በውሳኔዎች ላይ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ጥርጣሬ ነው፡፡ (Ratanlal and Dhirajlal, pp. 31-32)፡፡ ከዚህ አንፃር ዐቃቤ ህግ በወንጀል የተከሰሰ ሰው የተከሰሰበትን ድርጊት ስለመፈፀሙ ምክንያታዊ ጥርጣሬ በማያስነሳ ሁኔታ ማስረዳት አለበት ሲባል የዐቃቤ ህጉን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ተከሳሹ ድርጊቱን ፈፅሟል ወይም አልፈፀመም ብለው ጥርጣሬ እንዲያድርባቸው የሚያደርግ ሁኔታ ነው፡፡ ስለዚህም

- ጥርጣሬው ምክንያታዊ ሊሆን ይገባል፡፡
- የጥርጣሬው ምንጭም የዓቃቤ ህጉ ማስረጃ ወይም የተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ የፈጠረው ሊሆን ይችላል፡፡
- ምክንያታዊ ጥርጣሬ መኖር አለመኖሩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት መነሻው ከመደበኛ ባለሞያ ዳኞች አመለካከት አንፃር ሳይሆን የሚለካው ተራ ሰው በኑሮ ልማድ ካለው አመለካከት በመነሳት ነው፡፡ ከህዝብ መካከል የተመረጡ ዳኞች በዚህ ረገድ ውሳኔ እንዲሰጡ መደረጉ የዚህ ነፀብራቅ ነው፡፡
- በማናቸውም ሁኔታ ማስረጃው ምክንያታዊ ጥርጣሬን በማያስነሳ ሁኔታ ተከሳሹ ድርጊቱን ስለመፈፀሙ የማያስረዳ ከሆነ ማለትም የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ያስረዳው

ፍሬ ነገር አጠራጣሪ ሁኔታዎች ካሉና ጥርጣሬውም ምክንያታዊ ከሆኑ ተከሳሹ የጥርጣሬው ተጠቃሚ መሆን ይገባዋል (Ratanlal and Dhirajalal,p. 36)፡፡

በወንጀል ጉዳይ ተፈላጊው የአስረጅነት መመዘኛ ከምክንያቲዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳት እንዲሆን ያስፈለገው "በወንጀል የተከሰሰ ሰው ድርጊቱን መፈፀሙ በሚገባ እስኪረጋገጥ ድረስ ነፃ ሆኖ የመቆጠር መብት አለው" የሚል መርህ ለማስፈፀም ነው፡፡ ስለዚህም ከሳሽ ዐቃቤ ህግ ይህንን "ነፃ ሆኖ የመገመት/የመቆጠር መብት" ለማስቀረት ወይም ለማስተባበል ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮችን በሙሉ እርግጠኛ ለመሆን በሚጠጋ ሁኔታ ማስረዳትና ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑን ማሳመን ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም በወንጀል ጉዳይ በማስረጃ ምዘና ወቅት በሚፈፀም ስህተት ምክንያት ወንጀሉን ያልፈፀመ ሰው በስህተት ወይም ባልተረጋገጠ ማስረጃ ምክንያት ጥፋተኛ እንዳይሆን መከላከል ነው፡፡ በአንግሎ አሜሪካ የህግ ሥርዓት መሠረት ወንጀል ያልፈፀመና ነፃ ሊባል የሚገባውን ሰው በስህተት ጥፋተኛ ማድረግ የሚያስከትለው ኪሳራ ጥፋተኛ ሊባል ይገባ የነበረን ሰው በስህተት በነፃ ማሰናበት ከሚያስከትለው ኪሳራ ሲነፃፀር እጅግ የከፋ ተደርጐ ይወሰዳል፡፡ "በስህተት ምክንያት አንድ ሰው ከሚቀጣ አስር ወንጀለኖች በነፃ ቢለቀቁ ይመረጣል" እንደሚባለው ማለት ነው፡፡ (Clermont p. 16)፡፡ ሌላው ምክንያት ተብሎ የሚገለፀው ደግሞ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የአስረጂነት መመዘኛ ህብረተሰቡ ለወንጀል ህግ አክብሮትና መተማመን እንዲኖረው ያደርጋል የሚል ነው፡፡ ማለትም ወንጀል ያልፈፀሙ ሰዎች ጥፋተኛ ተደርገው ይቀጣሉ የሚል ስጋት እንዳይኖረው ያደርጋል የሚል አመለካከት አለ፡፡ (Clermont P. 16)

## ለ. <u>በፍትሐብሔር ጉዳይ የአስረጅነት ደረጃ /መመዘኛ/</u>

ከላይ እንደተገለፀው የፍትሐብሔርን ጉዳይ ለማስረዳት የሚቀርብ ማስረጃ አስረድቷል ለማለት ተፈላጊ የሆነው የአስረጂነት ደረጃ ወይም መመዘኛ ከወንጀል ጉዳይ የተለየ ነው፡፡ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳትን የሚፈልገው መመዘኛ ለፍትሐብሔር ጉዳዮች ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ በአሜሪካ ህግ መሠረት በፍትሐብሔር ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃ የአስረጂነት ደረጃ ወይም መመዘኛ ሁለት ሁለት መልክ አለው፡፡ እነዚህም፡-

➢ በተሻለ ሁኔታ በማሳመን የማስረዳት መመዘኛ (Preponderance) እና
➢ ግልፅና አሳኝ በሆነ ሁኔታ የማስረዳት መመዘኛ (Clear and Convincing Evidence) ናቸው

ከነዚህ መካከል በስፋት የሚታወቀውና እጅግ በሚበዙት የፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ያለው በተሻለ ሁኔታ በማሳመን የማስረዳት ደረጀ ወይም መመዘኛ ነው፡፡

የተሻለ አስረጅ በማቅረብ የማስረዳት መመዘኛ (Preponderance) ማለት በፍትሐብሔር ጉዳይ የማሳመን ሸክም ያለበት ወገን (በአብዛኛው ከሳሹ ነው) የአቀረበው ማስረጃ ያስረዳል ተብሎ የቀረበበትን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር በተመለከተ የማይመስል ከሚባል ይልቅ ይመስላል በሚል ደረጃ ማስረዳት መቻሉን የሚመለከት ነው (More likely than not)፡፡ በዚህም መሠረት ክስ የአቀረበ ከሳሽ አቋሙን ያስረዳልኛል በሚል የአቀረበው ማስረጃ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ቢኖሩ እንኳን፣ እንዲሁም እነዚህ አጠራጣሪ ሁኔታዎችም ምክንያታዊ ቢሆኑም እንኳን ከሳሹ የአቀረበው ማስረጃ ያስረዳዋል ከተባለው ጭብጥ አንፃር ፍሬ ነገሩ የለም ከማለት ይልቅ አለ ያስብላል በሚባል ደረጃ ከደረሰ አስረድቷል ይባላል፡፡ ስለዚህ የዚህ የማስረዳት መመዘኛ ማዕከላዊ ነጥብ አከራካሪ ከሆነው ጭብጥ የትኛውን የተሻለ (መኖሩን ወይም አለመኖሩን) ያስረዳል? የሚለው ነው፡፡ ለምሳሌ ተወላጅነትን ለማስረዳት የቀረቡት ምስክሮች ከፊሉ አመልካቹ በጋብቻ ውስጥ የተወለደ መሆኑን ሲመሰክሩ፣ ከፊሉ ደግሞ ሟች የተወለደ ጊዜ ተከሳሹ (አባት ነው በሚል ክስ የቀረበበት ሰው) ከከሳሹ (አመልካቹ) እናት ጋር አብረው ይኖሩ እንደነበር ነገር ግን በጋብቻ ውስጥ አለመሆኑን የመሠከሩ ቢሆን ማስረጃዎች የሰጡት ቃል በአንድ ላይ ሲመዘን "አመልካቹ በጋብቻ ውስጥ አልተወለደም ከማለት ይልቅ በጋብቻ ውስጥ የተወለደ መሆኑን በተሻለ ያስረዳል" ማለት ይቻላል፡፡ ከጥርጣሬ በላይ አስረድቷል? የሚል ጥያቄ ማቅረብ አያስፈልግም፡፡

በፍትሐብሔር ጉዳዩ ይህንን የመሠለ ቀለል ያለ የአስረጅት መመዘኛ ተመራጭ የሆነው በወንጀል የተቀመጠው ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት ግዴታ የተፈለገበት ምክንያት በፍትሐብሔር ጉዳይ ቦታ ስለሌለው ነው፡፡ በፍትሐብሔር የተከሰሰ ሰው ኃላፊነቱ እስኪወሰን ድረስ ንፁህ ሆኖ ይገመታል የሚል መርህ የለም፡፡ አንድ ሰው

ያለአግባብ ጥፋተኛ ቢሆን የሚፈጥረው ኪሳራ አስር ጥፋት የፈፀሙ ሰዎች በነፃ ቢለቀቁ ከሚደርሰው ኪሳራ የከፋ ነው የሚል መርህ በፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ አግባብነት የለውም፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳይ በአንድ ሰው ላይ የሚደርስ ኪሣራ በሌላ ሰው ላይ ከሚደርስ ኪሳራ ጋር እኩል ክብደት አለው፡፡ ስለዚህ ተገቢ የሚሆነው ማስረጃው <u>የበለጠ</u> ያስረዳው የትኛውን ፍሬ ነገር ነው? የሚለው መመዘኛ ነው፡፡

ግልፅና አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት የአስረጅነት መመዘኛ (Clear and Convincing Evidence Standard of Proof) ተቀባይነቱ (በአሜሪካ ህግ መሠረት ማለት ነው) በተወሰኑ ጉዳዮች ነው፡፡ ለምሳሌ የአስተዳዳሪነትን ወይም ሞግዚቱ ይህንን ተግባር ለማከናወን ብቃት እንደሌለው በግልፅና ፍ/ቤቱን በሚያሳምን ማስረጃ ማስረዳት ይገባል እንደሚባለው ዓይነት ማለት ነው (Clermont, p.1)፡፡ ይህ ማለት ማስረጃው ተከሳሹ ለሞግዚትነት ወይም ለአሳዳሪነት በቂ አለመሆኑን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ እንዲያስረዳ አይጠበቅም፡፡ ተፈላጊው ነገር ማስረጀው ተከሳሹ የሞግዚትነት ሥራውን ለመስራት አልቻለም ወይም አይችልም ለማለት በቂና ፍ/ቤቱም እንዲያምን ማድረግ መቻሉ ነው፡፡

ይህ በቂና አሳማኝ ማስረጀ በማቅረብ የማስረዳት መመዘኛ መካከለኛ ደረጃ ወይም መመዘኛ (Intermediate Standard) ሊባልም ይችላል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ከማስረዳት ዝቅ ይላል፤ በይመስላል ወይም የትኛውን የበለጠ ያስረዳል (Preponderance) ከሚለው ደግሞ ከፍ ማለቱ ነው፡፡

### <u>*6.2.2. የሲቪል ህግ ሥርዓት አቀራረብ*</u>

ይህን የህግ ሥርዓት በሚከተሉ አሮች የማስረጀው የአስረጅነት ደረጀ ወይም መመዘኛ በወንጀልና በፍትሐብሔር ጉዳዮች መካከል ልዩነት አይንፀባረቅም፡፡ በሁለቱም ጉዳዮች ማስረጃው እንዲያስረዳ የሚጠበቀው የተፈለገው ፍሬ ነገር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ከፍ ባለ ደረጃ ማስረዳቱ ነው፡፡ ማስረጃው ምክንያታዊ ጥርጣሬ በማያስነሳ ሁኔታ እንዲያስረዳ አይጠበቅበትም (በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር ጉዳይ ማለት ነው)፡፡ እንዲሁም በተሻለ ደረጃ ያስረዳ በሚልም የወረደ መመዘኛ አይቀበልም፡፡ መመዘኛው

የሚሆነው ማስረጃው በተቻለ መጠን ግልፅና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ተፈላጊው ፍሬ ነገር ስለመኖሩ ወይም አለመኖሩ ሊያስረዳ ይገባል የሚለው ነው፡፡

በዚህም መሠረት የሲቪል ህግ ሥርዓት የማስረጃ አስረጂነት መመዘኛ ከአንግሎ አሜሪካ የህግ ስርዓት ጋር ሲነፃፀር ከላይ ከተጠቀሰው የአሜሪካ ህግ በተወሰኑ የፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ የሚፈልገውን በቂና አሳማኝ ማስረጃ የማቅረብ የማስረዳት መመዘኛ (Clear and Convincing Evidence standard of proof) ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ይህንን ለወንጀልም ሆነ ለፍትሐብሔር ጉዳዮች በተመሳሳይ ይጠቀማሉ፡፡ ለዚህ የህግ ስርዓት ጀርመንን፣ ፈረንሳይን እና ጃፖንን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ (Clermont, PP. 2-3,13-14)

### ***6.2.3. ልዩነቱ ስለሚያስከትለው ዉጤት***

ሁለቱ የህግ ሥርዓቶች የተለየ መመዘኛ መከተላቸው የተለያዩ ውጤቶችን የሚያስከትል ሲሆን እነዚህም፡-

- በወንጀል ክስ የጥፋተኛነት ውሰኔ ከማስገኘት (Conviction Rate)
- ወጪን ከመቀነስ (Cost minimization) እንዲሁም
- ጥንቃቄ እንዲደረግ ከማበረታታት አንፃር (Providing Incentives) ሊገለፅ ይችላል፡፡

በወንጀል ክስ የጥፋተኛነት ውሳኔ ከማስገኘት አንፃር ሲታይ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት የአስረጂነት መመዘኛ ከፍተኛ በመሆኑና በጥርጣሬ መነሻ ተከሳሾች በነፃ ሊለቀቁ የሚችሉበት ዕድልም የሰፋ በመሆኑ በቂና አሳማኝ መመዘኛን ከሚጠቀሙ አገሮች ጋር ሲነፃፀር ክስ ከቀረበባቸው ተከሳሾች መካከል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው በነፃ እንዲሰናበቱ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ የጥፋተኛነት ውሳኔ የማሰጠት መቶኛው የቀነሰ ነው፡፡

ወጪን ከመቀነስ አንፃር በማነፃፀሪያነት የሚታየው የፍትሐብሔር ጉዳይ ነው፡፡ ማስረጃው አስረድቷል ለማለት ከፍ ያለ መመዘኛ የሚጠይቅ ስርዓት ተፈፃሚ የሚደረግ

ከሆነ ይህንን ደረጃ የሚያሟላ ማስረጃ ማቅረብ የሚያስፈልግ ሲሆን ለዚህም ተከራካሪ ወገን (በአብዛኛው ከሳሹ) ማስረጃውን ለማሟላት ከፍተኛ ወጪ ያወጣል፡፡ በአንፃሩ የተሻለ ወይም በይመስላል አስረጅነት ደረጃ ተፈፃሚ የሚደረግ ከሆነ ይህንን መመዘኛ የሚያሟላ ማስረጃ በቀላሉ ማግኘት ስለሚቻል ማስረጃን ለመሰብሰብ የሚወጣውን ወጪ ይቀንሳል፡፡

ጥንቃቄ እንዲደረግ ከማበረታታት አንፃር ሊነፃፀር የሚችለውም በፍትሐብሔር ጉዳይ ሆኖ በተለይ በቸልተኛነት ላይ የተመሠረተ ኃላፊነትን ከመወሰን ጋር ነው፡፡ የአስረጅነት መመዘኛው ከፍተኛ ነው ማለት (እንደሲቪል ህግ ስርዓት ማለት ነው) ተከሳሹ በቸልተኛነት አጥፍቷል ለማስባልና ቸልተኛነት መኖሩን ለማስረዳት ከሳሽ ያለውን እድል ያጠብበታል፡፡ ደካማ ማስረጃ በማቅረብ ቸልተኛነትን ማስረዳት አስቸጋሪ ይሆናልና፡፡ ስለዚህም ከማስረጃው በቂ አለመሆን የተነሳ ጥፋት የፈፀሙ ሰዎች ከኃላፊነት የሚያመልጡበትን እድል ስለሚያሰፋው ቸልተኛ ላለመሆን እንዳይተጉ ያደርጋል፤ ወይም ትጋታቸውን ይቀንሳል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቀለል ባለ መመዘኛ (ለምሳሌ ቸልተኛነት ያለ ይመስላል የሚል) በመጠቀም ቸልተኛነትን ማስረዳት የሚቻል ከሆነ ከሳሽ ቸልተኛነትን በቀላሉ እና ደከም ባለ ማስረጃ የማስረዳት ዕድሉን ስለሚያሰፋለት ሰዎች ቸልተኛ እንዳይሆኑ እንዲጠነቀቁ ያበረታታል (Demalgin, P. 21 Clermont, p. 8)::

## *6.3. የአስረጅነት መመዘኛ ከኢትዮጵያ ህግ አንፃር*

### *6.3.1. በወንጀል ጉዳይ*

በወንጀል ጉዳይ የቀረበ የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል መፈፀሙን ያስረዳል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የወ.መ.ህ.ሥ.ሥ.ቁ. 141 እና 142 ድንጋጌን አጣምሮ ማየት ያስፈልጋል፡፡ ቁጥር 141 ርዕሱ "ዐቃቤ ህጉ ክስን ባላስረዳ ጊዜ ስለተከሳሹ መለቀቅ" የሚል ሆኖ ዝርዝሩ ደግሞ "ዐቃቤ ህጉ ማስረጃውን አሰምቶ ከጨረሰ በኋላ ማፍረሻ ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ሳይሆን ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ እና ማስረጃው በቂ ሆኖ ሳያገኘው የቀረ እንደሆነ

ተከሳሹ በነፃ እንዲለቀቅ ፍርድ ቤቱ ያዝዛል" ይላል፡፡ ቁጥር 142/1/ ደግሞ ተከሳሹ ማስተባበያ (የመከላከያ) ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው "በቀረበበት ማስረጃ መሠረት የተመሠከረበት ከሆነ" ነው ይላል፡፡ በዚህም መሠረት እነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች ተጣምረው ሲታዩ፡-

- ተከሳሹ መከላከያ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው ተከሳሹ "በቀረበበት ማስረጃ መሠረት የተመሠከረበት ከሆነ" ነው፡፡
- ተከሳሹ በቀረበበት ማስረጀ መሠረት ተመስክሮበታል የሚባለው ይህ የዐቃቤ ህግ ማስረጃ "ተከሳሽን ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ" የተገኘ እንደሆነ ነው፡፡
- ማስረጃው ተከሳሹን ጥፋተኛ ሊያደርገው የሚችለው ደግሞ በፍ/ቤቱ አስተያየት ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማድረግ በቂ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

ከዚህ የምንረዳው ማስረጃው ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማድረግ በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን የሚወስነው ፍ/ቤቱ መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ይህ አባባል የተሟላ ስዕል አይሰጥም፡፡ ጥፋተኛ ሆኖ ለመገኘት በቂ ማስረጃ እንደሚያስፈልግ ከመግለፅ አልፎ "በቂ" ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አይነግረንም "በቂ ነው" ሲባል ምን ማለት ነው? ምክንያታዊ ጥርጣሬ በሚያስነሳ ሁኔታ ማስረዳት? ወይስ ግልፅና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ማስረዳት? ወይም በተሻለ አስረድቷል በሚል መመዘኛ ማስረዳት?

የቁጥር 141 ድንጋጌን አተረጓጐም በተመለከተ የአገራችን ፍርድ ቤቶች በአብዛኛው የሚቀበሉት ጥርጣሬ በማያስነሳ ሁኔታ ማስረዳትን ነው፡፡ በበርካታ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ላይ እንደሚታየው ዐቃቤ ህግ በሚያቀርበው ማስረጃ ተከሳሹ ወንጀሉን ስለመፈፀሙ ጥርጣሬ በማያስነሳ ሁኔታ ማስረዳት እንደሚገባው አቋም ይያዛል (ለምሳሌ

ሆኖም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 141 ላይ የተደነገገው 'በቂ' የሚለው ቃል ምንም ጥርጣሬ በማያስነሳ ሁኔታ ማስረዳትን የሚመለከት አይደለም፡፡ 'በቂ' የሚለው ቃል 'ፍፁም የተሟላ' የሚለውን ያመለክታል ለማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ በዚህም መሠረት፡-

- በቁጥር 141 መሠረት 'በቂ' ነው የሚለው መመዘኛ በአንግሎ አሜሪካ የህግ ስርዓት በወንጀል ጉዳይ ተፈላጊው የሆነውን "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት"

መመዘኛ ይመለከታል ለማለት አይቻልም፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" ሲባል የአስረጂነት ደረጃው ወደ መቶ በመቶ የተጠጋ እውነተኛነቱ የተረጋገጠን ማስረጃ የሚመለከት ሲሆን ይህ ደግሞ ከበቂ በላይ እንጂ 'በቂ' ለማለት የማይቻል ነው፡፡ ቁጥር 141 ግን አስረጅነቱ 'በቂ' እንዲሆን እንጂ "ከበቂ በላይ" ይሁን በማለት አይናገርም፡፡ ከውሳኔ በፊት ጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠር መብት በኢትዮጵያ ህግ ውስጥም የተካተተ ቢሆንም ይህ ማለት ግን (ከኛ ህግ አኳያ) ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳትን አይመለከትም፡፡

- እንዲሁም በቁጥር 141 መሠረት ማስረጃው 'በቂ' ለመሆን በአንግሎ አሜሪካ የህግ ስርዓት ተከታይ አገሮች ለአብዛኛው የፍትሐብሔር ጉዳዮች አስረጅነት በመመዘኛነት የሚያገለግለውን በይመስላል ወይም በተሻለ አስረድቷል (Balance of Probability or Preponderance) ያመለክታል ለማለት አይቻልም፡፡ ለወንጀል ጉዳይ እንዲህ ዓይነት መመዘኛ የማይታወቅ ሲሆን ቁጥር 141 ላይ ይህን መመዘኛ ለማንፀባረቅ ተፈልጐ ቢሆን ኖሮ "ማፍረሻ ማስረጃ ሳያስፈልግ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ … ተከሳሽ በነፃ እንዲለቀቅ ፍ/ቤቱ ያዝዛል" ማለት ብቻ ይበቃ ነበር፡፡ ይህም ይበዛል፡፡ ህጉ ግን ከዚህ በተጨማሪ "… እና ማስረጃው በቂ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር …" የሚል ጨምሮበታል፡፡ ስለዚህ ያስረዳ ይመስላል የሚል መመዘኛ መጠቀም አንችልም፡፡
- ይልቁንም ቁጥር 141 የሚቀርበው በአንግሎ አሜሪካን የህግ ስርዓት ተከታይ አገሮች (ለምሳሌ በአሜሪካ) በጣም ለተወሰኑ የፍትሐብሔር ጉዳዮች ብቻ የሚውለው፣ በሲቪል ህግ ሥርዓት ደግሞ ለፍትሐብሔርና ለወንጀል ጉዳዮችም ተመሳሳይ አገልግሎት ያለው ግልፅና አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት መመዘኛ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ በኛ አገር የወንጀል ጉዳይ የአስረጅነት ደረጃው ዐቃቤ ህግ ተከሳሽ ወንጀሉን ስለመፈፀሙ ግልፅና ፍርድ ቤቱን የሚያሳምን ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት አለበት የሚለው ነው፡፡

ይህ መመዘኛ በእኛ ህግ ተፈፃሚነት ካለው፣

- ዐቃቤ ህግ የአቀረበው ማስረጀ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለማቋቋም አስፈላጊ የሆኑን ነገሮች ሁሉንም በበቂ ሁኔታ (ከላይ የተጠቀሰው መመዘኛ ማለት ነው)

ማስረዳት የሚጠበቅበት ሲሆን ከነዚህ መካከል አንዱን እነኳን ግልፅና አሳማኝ በሆነ ሁንታ ማስረዳት ካልቻለ መመዘኛውን አላሟላም ማለት ነው፡፡

- ዐቃቤ ህግ ያቀረበው ምስክር በቀረበለት መስቀልኛ ጥያቄ ወይም በተከሳሽ መከላከያ ማስረጀ አማካኝነት ክብደት ከአጣ (አሳማኝ ካልሆነ) ማስረጃው በቂ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ክብደት የአጣ ማስረጃ በሚያሳምን ሁኔታ ሊያስረዳ አይችልምና፡፡
- እንዲሁም ዐቃቤ ህጉ የአቀረበው ማስረጃ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ የማይታመን በመሆኑ የተነሳ የጥፋተኛነት ውሳኔ ለመስጠት የማያስችል ሲሆን (When the evidence adduced by the prosecution is so manifestly unreliable…) በቂ ነው ለማለት አንችልም (Fisher, P. 310)፡፡

## *6.3.2. በፍትሐብሔር ጉዳይ*

በኢትዮጵያ የፍትሐብሔርን ጉዳይ ለማስረዳት የቀረበ ማስረጃ አስረድቷል ለማለት መመዘኛው ምንድነው? የሚለውን በተመለከተ የተቆረጠ መልስ ለማግኘት ያስቸግራል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ የሚደነግገው የማስረዳት ሸክም ያለበት ሰው አስቀድሞ ማስረጃውን ካቀረበ በኋላ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ደግሞ በመቀጠል የሚያቀርብ መሆኑን እንጂ የማስረጃው አስረጅነት እስከምን ደረጃ መሆን እንዳለበት አይደነግግም፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን በፍትሐብሔር ጉዳይም ቢሆን የቀረበ ማስረጃ ሁሉ በደፈናው አስረድቷል የማይባልና ይልቁንም የሚመዘን በመሆኑ ማስረጃው ተፈላጊውን ፍሬ ነገር አስረድቷል ለማለት የሚቻልበትን መመዘኛ ማበጀት የማይቀር ነው፡፡

የማስረጃውን አስረጅት ለመወሰን የሚረዱ መመዘኛዎች ከፍትሐብሔር ህጉና ከሌሎችም ህጐች ማግኘት ይችላል፡፡ ለምሳሌ በፍትሐብሔር ህግ ውስጥ ይህንን መመዘኛ የሚያመለክቱ ድንጋጌዎችን ማግኘት ይቻላል፡፡ እነዚህ መመዘኛዎች ሲታዩም አንድ ወጥ ሳይሆኑ እንደተፈላጊው ፍሬ ነገር ሊለያዩ የሚችሉ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት የሚቀጥለውን ማጠቃለያ ለመስጠት ይቻላል፡-

- ከፍ ያለ የአስረጅነት ደረጃን የሚጠይቁ ድንጋጌዎች የሚገኙ ሲሆን እነዚህም በህጉ ተለይተው በተቀመጡ ጊዜ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡ በነዚህ ድንጋጌዎች ላይ የማስረጃው የአስረጅት ደረጃ "እርግጠኛ በሆነ አይነት" (ቁጥር 161/1/፣ 878)፣ "በቂ በሆነ ሁኔታ" (በቁጥር 184/2/)፣ "ከፍ ያለ አስረጅነት" (ቁጥር 1699/ለ/) ፣ "ግልፅ በሆነ ዓይነት በማስረዳት" (ቁጥር 756/2/) …ወዘተ በሚል ተቀምጠዋል፡፡
- በሚመስል ሁኔታ ማስረዳት ብቻ በቂ መሆኑ በግልፅ የተነገረባቸው ድንጋጌዎችም አሉ፡፡ ለምሳሌ በቁጥር 157/1/ አነጋገር አንድ ሰው ጠፍቷል በሚል ውሳኔ ለመስጠት የጠፋው ሰው የሞተ <u>የሚመስል</u> መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ማግኘት በቂ ነው (ቁጥር 157/1/)፡፡ ህግ በዚህ አይነት ቋንቋ ማስረዳት ይቻላል በሚል ሲያስቀምጥ በሚመስል ማስረዳት (Preponderance) በቂ ነው፡፡ ሌሎችም በቁጥር 862/1/፣ 2341/3/፣ 2342/3/፣ 2344/2/ መመልከት ይቻላል፡፡
- ድንጋጌዎች በግልፅ ቋንቋ "መስሎ ሲታይ" በሚል የማያስቀምጡ ቢሆን እንኳን ከፍ ያለ አስረጅነትን የሚገልፅ የተለየ ድንጋጌ እስከሌለ ድርስ ለፍትሐብሔር ጉዳይ "በሚመስል ሁኔታ" ማስረዳት በቂ ነው፡፡

***<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በወንጀል ጉዳይ በዐቃቤ ህግ በኩል የቀረበ ማስረጃ ያስረዳው ተከሳሹ ፈፅሟል ተብሎ በክስ ማመልከቻው ላይ የተጠቀሰውን ሳይሆን ሌላ ወንጀል ቢሆን ፍ/ቤቱ ምን ማድረግ አለበት? የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል መፈፀሙን አላስረዳም በሚል በነፃ እንዲሰናበት ይወስናል? ወይስ ማስረጀው ወደአስረዳው ሌላ ወንጀል ቀይሮ በዚሁ ላይ መከላከያ እንዲያቀርብ ያዝዛል?
2. በወንጀል ጉዳይ ተከሳሹ ተመስክሮበታል በሚል መከላከያ እንዲያቀርብ ብይን ከተሰጠ በኋላ መከላከያ ሳያቀርብ ቢቀርና በመጨረሻ ውሳኔ ሲሠራ መዝገቡ ሲመረመር ማስረጃው ያላስረዳ መሆኑ ቢረጋገጥ ምን ይደረጋል? አንድ ጊዜ ተመስክሮበታል ተብሎ ውሳኔ ይሰጥበታል? ወይስ አልተመሠከረበትም ተብሎ በነፃ ይሰናበታል?
3. ከሳሽ ለፍ/ቤት በአቀረበው ክስ "ከተከሳሹ ጋር በነበረን የጋብቻ ቤተሰብነት ምክንያት ከአሠሪዬ ኤ.ል.ካ. ከተባለ ዓለም አቀፍ ድርጅት ሊከፈለኝ የሚገባው

31,012.75 የአሜሪካ ዶላር በእንግሊዝ አገር ለንደን ከተማ በሚገኘው ባንክ ባለው የተከሳሽ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርግልኝ አመልክቼ ገንዘቡ በተከሳሹ ሂሳብ ገቢ ሆኖአል፡፡ ተከሳሽ ግን በርሱ ፈቃድ በባንክ ሂሳቡ የገባውን የእኔን ገንዘብ እኔ ወደማውቀው የባንክ ሂሳብ እንዲያስገባልኝ ብጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ገንዘቡ ወደ ኢትዮጵያ ብር ተለውጦ /ተመንዝሮ/ ብር 155,063.80 እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ" በማለት ጠይቋል ከክሱ ጋርም የተያያዙት ማስረጃዎች፡-

i. ከሳሹ ለኤ.ል.ካ ሠራተኛ አስተዳደር በፃፈው ደብዳቤ የጡረታ አበሉን በለንደን ሲቲ ባንክ በተከሳሽ ስም ወደ ተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1579290 እንዲያስተላልፍ መጠየቁን የሚያመለክተው፣
ii. በለንደን ሲቲ ባንክ 31012.76 የአሜሪካን ዶላር በኤ.ል.ካ አማካኝነት ወደ ሒሳቡ ገቢ የተደረገለት ስለመሆኑ ለሂሳቡ ባለቤት ለተከሳሽ ባንኩ የፃፈው ደብዳቤ፣
iii. ገንዘቡ በተከሳሹ ሂሳብ ገቢ የተደረገ መሆኑንና ይህንን ገንዘብ ወደ ሒሳቡ እንዲያዛውርለት ከሳሽ ለተከሳሽ የፃፈው ደብዳቤ ናቸው፡፡

እንዲሁም ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር የጋብቻ ዝምድና እንዳለው (ማለትም የተከሳሽ እህት የከሳሽ ሚስት መሆኗን) የሚያስረዳ ምስክር ያቀረበ ሲሆን ምስክሩም በዚሁ አይነት መስክሯል፡፡

ተከሳሽ በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ "ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንድከፍል የሚያስገድደኝ የውልም ሆነ የህግ ግንኙነት የለኝም፡፡ የእኔ ላይ ክስ ለመመስረትም ከሳሽ ምንም ዓይነት በቂና ህጋዊ ምክንያት የለውም፡፡ በበኩሌ በለንደን ከተማ ውስጥ በሚገኘው ባንክ ሂሳብ የለኝም፡፡ ከሳሽ ክሱን የመሠረተው በስመ ሞክሼ ሊሆን ከሚችል በስተቀር በለንደን ባንክ ሂሳብ አለኝ ብዬ የሰጠሁት ማረጋገጫ የለም፡፡ ከሳሽ ከክስ ማመልከቻው ጋር አያይዞ ያቀረበው ማስረጃም የከሳሽ አሠሪና ባንክ ያደረጉትን ግንኙነት ከሚያስረዳ በስተቀር ከተከሳሽ ጋር ግንኙነት መኖሩን አያሳይም" ብሏል፡፡ ነገር ግን ተከሳሽ ያያየዘው ወይም ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ (ከፌ/ጠ/ፍ/ቤት ፍ/ይ/ም/ቁ. 436/88 የተወሰደ)

ሀ. ከሳሹ ክሱን አስረድቷል ወይስ አላስረዳም?

ለ. ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የበለጠ ለማጣራት ሊወስድ የሚገባው ምን ተጨማሪ እርምጃ አለ?

# ምዕራፍ 7

# የምስክሮችን ቃል አስረጅነት ስለመመዘን

**ዝርዝር አላማዎች**

ሰልጣኞች ይህንን ምእራፍ ሲያጠናቅቁ ፣

- ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ ምዘና መሠረታዊ ነጥቦችን ተገንዝበዉ ሥራ ላይ ማዋል ይችላሉ፤
- ዕድልና አጋጣሚን መሠረት በማድረግ የምስክሮችን ቃል የመመዘን ክህሎት ያዳብራሉ፤
- አንድነትና ልዩነት፣ ከፊል እዉነትነት ያላቸዉን፣ በማቅናት የተሰጡ ቃሎችና፣ ማጋነን የሚታይባቸዉን ምስክርነቶችን፣ ተመሳሳይነት የሚታይባቸዉን፣ ጥቅም ያላቸዉ ምስክሮችን ቃል እና ልዩ መደብ ያላቸዉን ምስክሮች ቃል የመመዘን ክህሎት ያዳብራሉ ሥራ ላይም ያዉላሉ፡፡

## 7.1 ጠቅላላ

ዉድ ሠልጣኞች የማስረጃ የመጨረሻ ግብ ሊያስረዳው የቀረበበትን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ማስረዳት መቻል ነው፡፡ ማስረጃው ሊያስረዳ የቀረበበትን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር አስረድቷል የሚባለው መቼ ነው? የሚለው የማስረጃ አስረጅነት መመዘኛ (ወይም ደረጃን) የሚመለከት ሲሆን ባለፈው ምዕራፍ ተገልፆአል፡፡ ያም ሆኖ ግን ማስረጃው አስረድቷል? ወይስ አላስረዳም? የሚለውን ለመመለስ የቀረበውን ማስረጃ መመዘን ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም አስረድቷል? ወይስ አላስረዳም? የሚለውን ለመወሰን የቀረቡ ማስረጃዎች ይመረመራሉ፤ ይገናዘባሉ፤ ይተቻሉ፡፡ በዚህ ሂደት ድክመትና ጥንካሬያቸው ተጣርቶ ይወጣል፡፡ ከዚህ ሂደት የሚገኘው ውጤት

ደግሞ ማስረጃዎች አስረድተዋል ለማለት የሚያስፈልገውን መመዘኛ አሟልተዋል፤ ስለዚህም አስረድተዋል፤ ወይም አላሟሉም ስለዚህ አላስረዳም የሚል መደምደሚያ ላይ ያደርሳል፡፡

የዚህና የተከታይ ሁለት ምዕራፎች ትኩረትም የቀረቡ ማስረጃዎችን በመመዘን ሂደት መሠረታዊ የሆኑና ግምት ውስጥ ሊገቡ ስለሚገባቸው ጉዳዮች መግለፅ ይሆናል፡፡ የማስረጃ ምዘና ሂደት ፍሬ ነገርን ያስረዳል ወይም ያስተባብላል በሚል በሚቀርበው የማስረጃ ዓይነት ላይ የሚመሠረት በመሆኑ ከቀረበው የማስረጃ ዓይነት አንፃር ልዩነት ሊያሳይ ይችላል፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ምዕራፍ የምስክሮች ቃል ሲመዘን ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ጉዳዮች የሚገለፁ ሲሆን በተከታይ ሁለት ምዕራፎች ደግሞ የሰነድ፣ ኤግዚቢትና የዕምነት ቃል ማስረጃዎች ምዘናን የሚመለከቱ ጉዳዮች ይታያሉ፡፡

ወደ ማስረጃው አመዛዘን ዝርዝር ጉዳዮች ከመግባት አስቀድሞ የሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ማስረጃው ያስረዳባቸዋል የተባሉ ፍሬ ነገሮች ማስረጃው ከመቅረቡ በፊት በሚገባ ተለይተው መታወቅ አለባቸው፡፡ ማስረጃው ተፈላጊውን ፍሬ ነገር አስረድቷል ወይስ አላስረዳም? ከማለት አስቀድሞ ማስረጃው ሊያስረዳው የተፈለገው ፍሬ ነገር በሚገባ ተለይቶ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ይህ ከጭብጥ አያያዝ ጋር ተያይዞ ተገልፆአል፡፡ በሁለተኛ ደረጃም በፍትሐብሔርም ሆነ በወንጀል ጉዳዮች የምክንያትና የውጤት ግንኙነቶች ማስረጃን በመመዘን ረገድ ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡ ማለትም የቀረበው ማስረጃ ከሚገልፀው ፍሬ ነገር አንፃር ተከራካሪውን ወገን የሚኖረው መብት ወይም ኃላፊነት ተጣርቶ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በተለይ ብዙ ሰዎች በአንድነት ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በሆኑበት ሁኔታ የእያንዳንዱን ተከራካሪ ወገን መብትና ኃላፊነት መለየትና ከተገኘው ውጤት ጋር ያለውን ግንኙነት ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ በርካታ ሰዎች በአንድነት በተከሰሱበት ጉዳይ የቀረቡት ማስረጃዎች ክሱን አስረድተዋል ወይስ አላስረዱም? የሚለውን ለመወሰን ማስረጃዎቹ በሚመረመሩበት ወቅት፣

- ማስረጃዎች እያንዳንዱን ተከሳሽ በተመለከተ ፈፀመ ወይም ተሳተፈ በሚል ያስረዱት መለየትና መመዘን አለበት፡፡

- እያንዳንዱ ተከሳሽ ፈፀመ ተብሎ በማስረጃ የተነገረበት ድርጊት ተፈላጊውን ውጤት ለማስከተል ያለው ብቃት ወይም አስተዋጽኦ እስከምን ድረስ እንደሆነ ተለይቶ መታወቅና መመዘን አለበት፡፡

## 7.2. ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ ምዘና መሠረታዊ ነጥቦች

ከተፈላጊው እና በጭብጥ ከተያዘው ፍሬ ነገር ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር ማስረጃ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ በሚል ሊፈረጅ እንደሚችል በምዕራፍ 1 ውስጥ ተገልፆአል፡፡ የማስረጃ ምዘናን በተመለከተ ጉዳዩ ወንጀልም ሆነ ፍትሐብሔር (የአስረጅነት ደረጃው የሚያሳየው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ) ሁለቱም ዓይነት (ማለትም ቀጥተኛም የሆኑ ቀጥተኛ ያልሆኑ ማስረጃዎች) አግባብነት እስካላቸው ድረስ እና አይቀርቡም እስካልተባሉ ድረስ ቀርበው ይመዘናሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቀጥተኛ ማስረጃ ቀጥተኛ ካልሆነ ማስረጃ የተሻለ አስረጅነት አለው ብሎ መገመት ስህተት ሊሆን ይችላል፡፡ በፍርድ ቤት የቀረበ የዓይን ምስክር (የሚያስረዳው ፍሬ ነገር ሲፈፀም ያየ) ወይም ስለፍሬ ነገሩ ቀጥታ በሆነ ሁኔታ አውቃለሁ በሚል የሚመሰክር ምስክር አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ገልፆ ከሚያስረዳ ማስረጃ የተሻለ አስረጅነት አለው ብሎ መደምደምም አይቻልም፡፡ እንደዚህ ያለ ፍፁም የሆነ መደምደሚያ ተገቢነት የለውም፡፡ ዋናው ቁም ነገር የቀረበው ማስረጃ ከብዙ አጋጣሚዎች አንፃር ሲመዘን የሚኖረው የአስረጅነት ብቃት እንጂ ቀጥተኛ መሆን አለመሆን ላይ አይደለም፡፡

በዚህም መሠረት ማስረጃ ሲመዘን፣

- ድርጊቱ ሲፈፀም በአይን አየሁ የሚል የምስክርነት ቃል ፍሬ ነገሩን ለማስረዳት ብቸኛው ተዓማኒ ወይም ሁልጊዜም የተሻለ አስረጂ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ አይቻለሁ በሚል ምስክሩ የተናገረ ቢሆንም ወረድ ብለን እንደምንመለከተው ምስክሩ በጉዳዩ አወሳሰን አንፃር ካለው የግል ፍላጎት፣ ድርጊቱን ለማየት አጋጣሚውን ካገኘበት ሁኔታ አኳያ ሲመዘን እውነተኛ ላይሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ማስረጃው የአይን ምስክር (ወይም በጠቅላላው አነጋገር ቀጥተኛ ማስረጃ መሆኑ) ተፈላጊው

ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖሩን በተመለከተ ለመድረስ የምንወስደውን ግምት (Inference) ይቀንስልን ወይም ያስወግድልን እንደሆን እንጂ በራሱ ከአካባቢያዊ ማስረጃ በላቀ ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እምነት የሚጣልበት ነው አያሰኝም፡፡

- አካባቢያዊ ማስረጃን የተለየ የሚያደርገው ማስረጃው ሊያስረዳው ከተፈለገው ፍሬ ነገር አንፃር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው በመሆኑ ወደ ተፈላጊው ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር የሚያመራን በቀጥታ ሳይሆን በመገመት (Inference) መሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን አካባቢያዊ ማስረጃ ዝቅተኛ ግምት የሚሰጠው ነው ሊባል አይገባም፡፡ በርካታ ወንጀሎች በባህሪያቸው የአይን ምስክር በሌለበት ሁኔታ ሊፈፀሙ የሚችሉ መሆናቸው ሲታወቅ አካባቢያዊ ማስረጃ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ አካባቢያዊ ማስረጃም ይገመገማል፤ ይመዘናል፡፡ በምዘናው ሂደት ክብደት አጥቶ እንደሚወድቅ ሁሉ አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ሊያስረዳም ይችላል፡፡ ስለዚህ አካባቢያዊ ማስረጃ ቀጥተኛ ማስረጃዎችን የመደገፍ ሚና ብቻ እንደሚጫወት የሚወስድ አቋም ትክክለኛ አይደለም፡፡

የሰሚ ሰሚ ማስረጃን በተመለከተ አግባብነት እስካለው ድረስ ባስረጅነት ሊቀርብ ይችላል (በህጋችን ማለት ነው)፡፡ ነገር ግን ይህ ማስረጃ ሲመዘን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳይ የሰሚ ሰሚ ማስረጃ ጥብቅ ምዘና ባይካሔድበትም የሚያስከትለው ጉዳት የተወሰነ ነው፡፡ በወንጀል ጉዳይ ግን ጥፋተኛ ያልሆነ ሰው ጥፋተኛ ተብሎ ቢቀጣ ከሚያስከትለው ጉዳት አንፃር የሰሚ ሰሚ ማስረጃ በጥንቃቄ መመዘን ይኖርበታል፡፡ በተለይ ደግሞ

- ዋናው ማስረጃ (ማለትም ድርጊቱ ሲፈፀም ያየ የሰማ...) ያልቀረበበትና የሰሚ ሰሚ ማስረጃ ተክቶት እንዲቀርብ የተደረገበት ምክንያት በትክክል መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ዋናው ቀጥተኛ ማስረጃ ሊቀርብ እየቻለ እንዳይቀርብ ተደርጐ ትርጉም ያለው መስቀልኛ ጥያቄ የማይቀርብበት የሰሚ ሰሚ ማስረጃ ቀርቦ ቢመሠክር ወይም የፍሬ ነገርን መኖር ወይም አለመኖር ቢገልፅ ለዚህ ቃል ክብደት መስጠት ተገቢ አይደለም፡፡
- ለሰሚ ሰሚ ማስረጃው የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለገለው ዋናው ወይም ቀጥተኛ ማስረጃ ፍሬ ነገሩን ከማወቅ ረገድ ያለው ቅርብት፣ እድል፣ ወይም አጋጣሚ የሰሚ

ሰሚ ማስረጃን ለመመዘን አስፈላጊ ነጥብ ነው፡፡ ችሎት ለቀረበው የሰሚ ሰሚ ማስረጃ መረጀውን የሰጠው የግል ተበዳይ ራሱ ወይም ደግሞ ሌላ ሰውም ሆኖ በነበረው አጋጣሚ መረጃውን ለማግኘት የቻለ ከሆነ ለማስረጃው አስረጅነት የተሻለ ክብደት የሚሰጠውን ያህል የመረጃ ምንጭ የሆነው ሰው ለሰሚ ሰሚ ማስረጃው መረጃ ለመስጠት የቻለበት ሁኔታ በሚገባ ካልታወቀ፤ ወይም ችሎት የቀረበው ምስክር ከሌላ የሰሚ ሰሚ ማስረጀ መረጃውን ያገኘ ከሆነ ለዚህ ዓይነት ማስረጃ ክብደት ሊሰጥ አያገባም፡፡ የመረጃው ምንጭ ከተፈላጊው ፍሬ ነገር ጋር ያለው ግንኙነት ቀጥተኛ ከመሆን በራቀ ቁጥር በሰሚ ሰሚ ማስረጃው (ወይም ምስክሩ) የሚሰጠው ምስክርነት ወሬ የመሆን እድሉ እየሰፋ እንደሚሔድ ሊታወቅ ይገባል፡፡

## *7.3. ዕድልና አጋጣሚን መሠረት በማድረግ የምስክሮችን ቃል መመዘን*

ምስክሮች የሰጡት ቃል ትክክለኛነት ከሚመዘንባቸው መስፈርቶች መካከል አንዱ ዕድልና አጋጣሚ ነው፡፡ ማለትም ምስክሩ ችሎት ቀርቦ የገለፀውን ፍሬ ነገር እሱ እንደሚለው ለማየት፣ ለመስማት… ወዘተ እንዴት ቻለ? በሚል መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ጥያቄ አግባብነቱ ለፍትሐብሔርና ለወንጀል ጉዳዮች ሲሆን ከጊዜ፣ ከቦታ እና ድርጊቱ ሲፈፀም የነበረው የምስክሩ ባህርይን መሠረት በማድረግ ሊታይ የሚችል ነው፡፡

### *7.3.1 ድርጊት ከተፈፀመበት ቦታ አንፃር፣*

ድርጊቱ የተፈፀመበት ቦታ ማስረጃን ለመመዘን ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ በዚህም መሠረት፡-

- ማስረጃው (ምስክሩ) ያስረዳው ድርጊት የተፈፀመበት ቦታ ለመገኘት የቻለበት ዕድል ወይም አጋጣሚ ሊመረመር ይገባል፡፡ ለምሳሌ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ተፈፀመ የተባለን የወንጀል ድርጊት ያስረዳል በሚል የቀረበ ምስክር ድርጊቱ ሲፈፀም አይቻለሁ የሚል ቢሆን በዚያ ቤት ውስጥ ሊገኝ የቻለበት ዕድል ወይም አጋጣሚ

(ቤተሰብ፣ እንግዳ፣ ጩኸት ሰምቶ የደረሰ…) ሊመረመር እና ትክክለኛነቱ ሊመዘን ይገባል፡፡

- ማስረጃው ያስረዳበትን ፍሬ ነገር ለማወቅ የቻለው የተለየ የሥራ ግንኙነት በመኖሩ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ምስክሩ በዚያ ስፍራ ሊገኝና ሊያውቅ የቻለበት ምክንያት ሊመዘን ይገባል፡፡ የመንግስት ንብረት ከመጋዘን ሲወሰድ አይቻለሁ የሚል ሰው ድርጊቱን ለመፈፀም የቻለበት ዕድል ወይም አጋጣሚ የሚመረመር ሲሆን ገንዘብ ማጉደሉን አስረዳለሁ የሚል ምስክር የተከሳሹን ሂሳብ ለመመርመር ያለው ዕድል ወይም አጋጣሚ መታወቅ አለበት፡፡ ይህ የሚጠቀመውም ምስክሩ የተናገረው በትክክል የሚያውቀውን ወይም ግምቱን መሆኑን ለመለየት ያስችላል፡፡

### *7.3.2. ድርጊት ከተፈፀመበት ጊዜ አንፃር፣*

ማስረጃው ያስረዳው ድርጊት የተፈፀመበት ጊዜን ማረጋገጥ በማስረጃ ምዘና የተለየ ቦታ ይኖረዋል፡፡ ከጊዜ አንፃር ምስክሩ ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ቦታ ሊገኝ መቻል አለመቻሉን፤ የተገኘ ቢሆን እንኳን መለየት መቻል አለመቻሉን ለማረጋገጥ ይጠቅማል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

- ድርጊቱ የተፈፀመው በቀን ወይም በሌሊት መሆኑ የምስክሩን ቃል ለማመንም ሆነ ላለማመን መሠረት ሊሆን ይችላል፡፡ በጨለማ የተፈፀመ ከሆነ የተለየ ሁኔታ ከሌላ በቀር የድርጊቱን አፈፃፀም ዝርዝርና ድርጊት ፈፃሚውን ለመለየት መቻልን አጠራጣሪ እንደሚያደርገው ዓይነት ማለት ነው፡፡ ጨለማ ከመሆኑ የተነሳ እዚያ ቦታ ለመገኘት የቻለበት ምክንያት አጥብቆ እንዲጠየቅ በር ይከፍታል፡፡
- ድርጊቱ የተፈፀመበትን ጊዜ ማወቅ ምስክሩ ምስክርነት የሰጠበትን ፍሬ ነገር ለማወቅ የተጠቀመባቸውን መንገዶች ተዓማኒነት ለመመዘን ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡ ለምሳሌ ድርጊቱ የተፈፀመው በሌሊት ሆኖ ምስክሩ ድርጊቱን የፈፀመውን ሰው ለመለየት የቻለው በድምፅ ነው ቢል ከዚህ ድምፅ ጋር ያለው ትውውቅ፣ በጨረቃ ብርሐን ነው ቢል ምስክሩ ከነበረበትና ድርጊቱ ከተፈፀመበት ቦታ ርቀት አንፃር በጨረቃ ብርሃን መለየት መቻል አለመቻሉን….. ወዘተ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

### *7.3.3. ያልተለመዱ ባህሪያት፣*

ምስክሩ ያስረዳው ድርጊት ተፈፀመ በተባለ ጊዜና ቦታ የነበረና የተገለፀ የምስክር ባህሪይ ያልተለመደ መሆን በማስረጃ ምዘና ጊዜ መጠቀም አዘውትሮ የሚሰራበት ነው (በተለይ ለወንጀል ጉዳይ)፡፡ አንዳንድ ምስክሮች ከድርጊቱ አፈፃፀም አንፃር ከገለፁት ፍሬ ነገር በመነሳት ያንን ድርጊት በስፍራው ሆነው መከታተል መቻላቸው ያልተለመደ ባህርይ (unnatural conduct) የሚባልበትና በዚህ የተነሳ ማስረጃው እውነተኛ አይደለም የሚል ዝንባሌን የሚፈጥር ሊሆን ይችላል፡፡ በመሠረቱ የዓይን ምስክር የነበረ ሰው ድርጊቱ ሲፈፀም መሸሽ ወይም መጮህ ነበረበት በሚል ምክንያት ውድቅ ሊደረግ አይገባም (Ratanlal Dhirajilal P. 50)፡፡ በዚህም መሠረት ምስክሩ ሳይሸሽ በስፍራው ሆኖ የድርጊቱን አፈፃፀም እስከ መጨረሻው ተከታትየዋለሁ ማለቱ ያልተለመደና የማይጠበቅም በመሆኑ ቃሉ ሊታመን አይችልም በማለት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ ነገር ግን የምስክሩ ያልተለመደ ባህሪይ የሰጠውን ቃል ትክክለኛነት በጥንቃቄ እንድንመረምር ያደርጋል፡፡ ማስረጃውን ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር አገናዝበን መመርመር ይገባናል፡፡

***መወያያ ጥያቄዎች***

ዐቃቤ ህግ በተከሳሹ ላይ የአቀረበውን የሰው መግደል ወንጀል ክስ ያስረዳሉ በሚል አራት ምስክሮችን የአቀረበ ሲሆን ምስክሮችም ተመሳሳይ በሆነ አገላለፅ፡-

"ድርጊቱ በተፈፀመበት ቀን ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ አባያ እርሻ ልማት 4ኛ ካምፕ ውስጥ ከሚገኘው ቤቴ ሽንት ቤት ወጥቼ ነበር፡፡ ሌሎችም ሠራተኞች እንዲሁ ወጥተው ውጭ እንዳለን ከኋላችን የባትሪ መብራት ስናይ ወደየቤታችን ጥግ ሔደን ተሰበሰብን፡፡ ባለባትሪውን ስንመለከት ሟች ከኋላችን ቀርቶ ስለነበረ እየጮኸ ወደራሱ ቤት ገባ፡፡ የቤቱን በር ዘጋ፡፡ መብራት ከቤቱ ውስጥ ሲበራ ይታይ ነበር፡፡ ተከሳሹ ኤም ዋን ጠመንጃ በአንድ እጁ፣ ባትሪ በሌላ እጁ ይዞ በመምጣት የሟች ቤት መዝጊያው ቆርቆሮ ስለሆነ በጠመንጃው ሰደፍ መትቶ በመብሳት በተባለው ቀዳዳ መሳሪያውን ደግኖ አንድ ጥይት ተኩሶ ደረቱን መቶት መሞቱን ቤት ውስጥ ገብቶ በባትሪ ካረጋገጠ በኋላ የመጣበት ተመልሶ ሄደ፡፡ እኔም መሞቱን ሔጄ አረጋገጥኩ፡፡ እኛ

ተከሳሹን ስለፈራን ለመያዝ አልሞከርንም፡፡ ድርጊቱን የፈፀመው ተከሳሽ መሆኑን ለእርሻ ልማት ሪፖርት አድርገናል፡፡ ተሰውሮ ታይቶ ከ20 ቀን በኂላ ጧት ሽጉጥ ይዞ በካምፕ ሲዘዋወር ከሌሎች ጋር ቁም ስንለው በእኔ ላይ አንድ ጥይት ተኩሶ ስቶኝ እንደገና አምልጧል፡፡ ተከሳሹ ድርጊቱን መፈፀሙና የያዘውን መሳሪያ መለየት የቻልነው ተከሳሹ በያዘው ባትሪ ነው" የሚል ሆኖ ኤግዚቢትም ሆነ የህክምና ማስረጃ አልቀረበም፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው ጠ/ፍ/ቤት ማስረጃውን ውድቅ በማድረግ ተከሳሹን በነፃ ያሰናበተ ሲሆን ማስረጀውን ውድቅ ካደረገባቸው ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡-

ሀ/ "የዐቃቤ ህግ ምስክሮች በተመሳሳይ ቃል ከምሽቱ 2 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ከሟቹ ጋር ለሽንት ወጥተን ነበር የማለታቸው ሁኔታ ሲታይ ከየቤታቸው ተጠራርተው በማታ ለሽንት አብረው ይወጣሉ ለማለት አያስደፍርም፡፡"

ለ/ "ተከሳሹ ከኂላችን በአንድ እጁ ባትሪ ይዞ እያበራ በሌላ እጁ ደግሞ ኤም. ዋን ጠመንጃ ይዞ ሲመጣ አይተን ወደየቤታችን ጥግ ሄደን እርሱ በአበራው የባትሪ ብርሐን ስንመለከት ነበር ማለታቸው ፈፅሞ የማይታመን ነው፡፡"

ሐ/ "ሟች ከእኛ ኂላ ቀርቶ ነበር ማለታቸውም አብረው ተጠራርተው ወጥተው ነበር ከተባለ እርሱ በዚያ ምሽት ከነርሱ ኂላ የቀርበትና እነርሱ ትተውት የሚሔዱበት ምክንያት የለም"

መ/ "ድርጊቱ ተፈፀመ የተባለው በወታደሮች ካምፕ ውስጥ እንደመሆኑ መጠን ተከሳሹ ሟችን ሲያሳድድ፣ የቤቱን በር ሲሰብርና አነጣጥሮ ተኩሶ ሲገድል፣ መሞቱን ለማረጋገጥ ቤት ውስጥ ገብቶ በባትሪ መብራት ተመልክቶ እስከሚሄድ፣ ድረስ ጩኸት አሰምተው ወታደሮችን ቀስቅሰው አስከብበው ለማስያዝ የሚከላከላቸው ነገር ባልነበረበት ሁኔታ በርግጥ በስፍራው የነበሩ ቢሆኑ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ

ድረስ ተከሳሽ የሚፈፀመውን ድርጊት ምንም ሳይተነፍሱና ሳይንቀሳቀሱ ይመለከታሉ ለማለት አያስደፍርም፡፡”

(ከጠ/ፍ/ቤት ወ/ይ/መ/ቁ. 112/80 የተወሰደ፡፡)

ከላይ የተጠቀሱት አራት የፍ/ቤቱ ትችቶች ተቀባይነት አላቸውን?ለምን? ትችቶቹ ምንን መሠረት ያደረጉ ናቸዉ?

## 7.4. የምስክሮች ቃል ልዩነትን እና አንድነትን መሠረት በማድረግ መመዘን

በችሎት የቀረቡ ምስክሮች የሰጡት ቃል ትክክለኛነት ከሚመዘንባቸው መንገዶች መካከል አንዱና ዋነኛው እርስ በርስ ያለው ግንኙነት ነው፡፡ የማስረጃ ምዘና አላማው ምስክሮች የሰጡት ቃል የተሳሳተ ወይም ትክክለኛ መሆኑን፣ እውነት ወይም ሐሰት መሆኑን፣ አጠራጣሪ ወይስ እርግጠኛ መሆኑን ለመለየትና ተፈላጊ የሆነውን የአስረጂነት መመዘኛ አሟልቷል ወይም አላሟላም? የሚለውን ለመወሰን በመሆኑ በዚህ ረገድ ምስክሮች የሰጡት ቃል አርስ በርሱ ሲገናዘብ የሚስማማ ወይም የሚለያይ መሆኑን መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ የማስረጃው ቃል እርስ በርሱ ይገናዘባል ሲባል ደግሞ እያንዳንዱ ምስክር ለዋና፣ ለመስቀልኛ፣ እና ድጋሚ ጥያቄ የሰጠው መልስ ካለው ግንኙነት፤ አንድ ምስክር የሰጠውን ቃል ከሌላ ምስክር ቃል ጋር ያለው ግንኙነት፤ እንዲሁም ምስክር የሰጠው ቃል ከሌላ ዓይነት ማስረጃ (ሰነድ ወይም ኢግዚቢት ሊሆን ይችላል) ጋር ያለውን ግንኙነት መመርመርና መመዘንን ያጠቃልላል፡፡ በምስክሮች ቃል  እና በሰነዶች መካከል የሚኖር ቅራኔ ወይም ልዩነት ምዘናን በሚመለከት በተከታዩ ምዕራፍ ይታያል፡፡

### 7.4.1. የምስክሮች ቃል ልዩነት ምዘና

#### ሀ. መሠረቱ

የምስክሮች ቃል ልዩነት በሚከተለው መርህ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይኸውም ሀሰተኛ ወይም የማይታመን ማስረጃን በመቀበል በዚህ መሠረት መወሰን ተገቢ አይደለም

የሚለው ነው፡፡ የአስረጅነት ደረጃው ፍትሐብሔር ወይም ወንጀል ከመሆኑ አንፃር ልዩነት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ሀሰተኛ ወይም የማይታመን ማስረጃ የአስረጅነት ደረጃውን እንደአሟላ ሊቆጠር አይቻልም፡፡ ከዚህ አንፃር የምስክሮችን ቃል ልዩነት በመመርመር መመዘን የምስክርነት ቃሉ ሐሰተኛ ወይም የማይታመን መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ዋነኛው መሳሪያ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ማስረጃ የሚታመን ወይም የማይታመን፤ እውነት ወይም ሐሰት መሆኑ ሲመዘንና ሲወሰን የሰዎችን የግንዛቤ ደረጃ ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ በምስክሮች ቃል መካከል ልዩነት መኖሩ አጠራጣሪ፣ ሐሰተኛ ወይም የማይታመን ነው ለማለት ግዴታን አያስከትልም፡፡ ሰዎች ስለአንድ ነገር ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ የተለያየ ስለሚሆን ልዩነት የሚጠበቅ ነው፡፡ ዋናው ቁም ነገር ልዩነቱ ፍሬ ነገሩ መኖር አለመኖሩን በተመለከተ በሚወሰድ መመዘኛ ላይ የሚያሳድረው ትፅዕኖ ነው፡፡ (Ratanlal and Dhirajilal P.28)፡፡ ስለዚህም በምስክሮች አመሠካከር መካከል የሚታዩ ልዩነቶች አንዳንዶቹ መሠረታዊ በመሆናቸው የተነሳ የማይታመን፣ ወይም ሐሰተኛ ወደሚል መደምደሚያ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ቀላል (minor) ወይም የማይጐዱ (tolerable) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በምስክሮች መካከል ያለው ተቃርኖ ወይም ልዩነት መሠረታዊ መሆን ወይም ቀላል ወይም የማይጐዳ መሆኑን መወሰን ቀላል አይደለም፡፡ ይህንን በርግጠኛነት ለመለየት የሚያስችል ሁሉንም የሚያስማማ መፍቻ (Checklist) ለማዘጋጀት አይቻልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የልዩነቱ ከባድነትና ቀላልነት እንደ ጉዳዩ ዓይነት (ወንጀል ወይም ፍትሐብሔር)፣ እንደምስክሮች አቋም (ፍላጐት የሚያሳዩ ወይም ገለልተኛ እንደመሆናቸው)ምስክሮች ለፍሬ ነገሩ እንዳላቸው ቅርበት (ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ)፣ እንደምስክሮች የግል ሁኔታ (ህፃናት ወይም አዋቂዎች) ሊወሰን የሚችል ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህን ጉዳዮች ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

ከላይ የተገለፀው ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው አጠቃላይ መርህ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

- ምስክር በተናገራቸው ቃላት መከከል፣ ወይም የምስክሮች ቃል እርስ በርሱ ሲገናዘብ የሚታየው ልዩነት ሊያስረዱበት ከመጡት ፍሬ ነገር አንፃር መሠረታዊ (Substantial) ከሆነ የማይታመን ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡-

  ሀ/ ምስክሩ ለዋና ጥያቄ በሰጠው መልስ "ተከሳሽ ድርጊቱን ሲፈፀም በስፍራው ሆኜ አይቻለሁ" ካለ በኋላ "አንተ በዚያን ጊዜ ወህኒ ቤት አልነበርክም ወይ?" በሚል ለቀረበለት መስቀልኛ ጥያቄ በሰጠው መልስ "አይቻለሁ ያልኩት በስህተት ነው፡፡ ዛሬ ከእኔ ጋር ምስክር ሆኖ የቀረበው ሰው ነግሮኝ ነው" ቢል ልዩነቱ መሠረታዊ ነው፡፡ ምክንያቱም ተከሳሹ ድርጊቱን ፈፅሟል የሚለውን መደምደሚያ አይሰጥምና፡፡

  ለ/ ምስክሩ ለዋና ጥያቄ በሰጠው መልስ "ተከሳሹ ድርጊቱን ሲፈፅም በስፍራው ሆኜ አይቻለሁ፡፡" ከአለ በኋላ "በጭለማ አንተ በዚያ ቦታ ምን ታደርጋለህ?" በሚል ለቀረበለት ጥያቄ "እኔ መግደሉን ያወቅኩት በዚያን ዕለት ቀን ላይ ዛሬ ማታ ዋጋውን እሰጠዋለሁ እያለ ሲዝት በመስማቴ ነው" የሚል መልስ ቢሰጥ ይህ ልዩነት መሠረታዊ ነው፡፡ ምክንያቱም ምስክሩ አይቻለሁ በሚል በቀጥተኛ ምስክርነት ከሰጠ በኋላ ደረጃውን ወደ አካባቢያዊ ማስረጃ የለወጠ ሲሆን ተከሳሹ ገድሏል በሚል ለመደምደም አያስችልም፡፡

  ሐ/ 1ኛ ምስክር ሆኖ የቀረበ ሰው በሰጠው የምስክርነት ቃል "ድርጊቱ ሲፈፀም በስፍራው የነበርኩና ያየሁ እኔ ብቻ ነኝ፡፡ ሌላ ሰው ባለመኖሩ ተከሳሹን ማስያዝ አልቻልኩም" የሚል መልስ የሰጠ ሆኖ በዚሁ ጉዳይ የቀረበ 2ኛው ምስክር ደግሞ "ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው የነበርኩት እኔ ብቻ ነበርኩ፣" ቢል ወይም "1ኛው ምስክር በስፍራው አልነበረም፣ እኔ ቤቱ ሔጄ ቀስቅሼው መጣ እንጂ ተከሳሹ ድርጊቱን በፈፀመ ጊዜ አልነበረም" ቢል በሁለቱ ምስክሮች ቃል መካከል ያለው ልዩነት መሠረታዊ ነው፡፡ ምስክሮቹ በስፍራው የነበሩና የተመለከቱ ናቸው ለማለት አያስችልም (Ratanlal and Dhirajilal p. 28)

በዚህ ዓይነት በርካታ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ዋናው ልዩነት ተፈላጊውን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማረጋገጥ የማያስችል መሆኑ ነው፡፡ መሠረታዊ ያልሆነ ልዩነትን በተመለከተም ለምሳሌ፡-

☞ የአይን ምስክር ሆኖ የቀረበ ሰው ለዐቃቤ ህግ ዋና ጥያቄ በሰጠው መልስ እያንዳንዱ ተከሳሽ ስለፈፀመው ድርጊት ሲያስረዳ "1ኛ ተከሳሽ በዱላ ጀርባው ላይ ደጋግሞ መታው፤ 2ኛው ተከሳሽ በድንጋይ እግሩ ላይ ደጋግሞ መታው፤ 3ኛው ተከሳሽ በጩቤ አንገቱ ላይ ደጋግሞ ወጋው" በሚል ከመሰከረ በኋላ ለመስቀልኛ ጥያቄ በሰጠው መልስ "1ኛው ተከሳሽ በዱላ እግሩ ላይ ደጋግሞ መታው፣ 2ኛው ተከሳሽ በድንጋይ ጀርባው ላይ 1 ጊዜ መታው፤ 3ኛው ተከሳሽ በጩቤ አንድ ጊዜ አንገቱን ወጋው" ቢል ይህ ልዩነት መሠረታዊ ነው ለማለት አያስችልም ይህ ልዩነት በሁለት ምስክሮች ቃል መካከል ቢከሰትም እንዲሁ መሠረታዊ ነው ለማለት አያስችልም። ምክንያቱም 3ቱም ተከሳሾች በድርጊቱ ተሳታፊ እንደነበሩ፣ እና ከያዙዋቸው መሳሪያዎች ጭምር ተመሳሳይነት በመኖሩ ነው።

ቀላል ልዩነቶች የሚታለፍበት ምክንያት የአንድን ድርጊት አፈፃፀም በሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ በሰዎች መካከል የመታዘብ (observation) የማስተዋል (Perception) እና የማስታወስ (memory) ልዩነት በመኖሩና ይህም ተፈጥሮአዊ በመሆኑ ነው። (Ratanlal and Dhirajilal p. 38)። የሆነ ሆኖ በጥንቃቄ ሊመረመር የሚገባው ጉዳይ ነው።

## *ለ. ከፊል እዉነት ያላቸው የምስክር ቃሎች (Partial Truth)*

ምስክር የሰጠው ቃል እርስ በርሱ ሲመረመር ልዩነት የሚታይበት ሆኖ ነገር ግን አንድነት የሚታይበትና ሊታመን የሚችል ቃልን ያቀፈ ሊሆን ይችላል። ወይም በአንድ ፍሬ ነገር ላይ የቀረቡ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ልዩነት የሚታይበት ሆኖም እያለ ስምምነት የሚታይባቸውና ሊታመኑ የሚችሉ ቃሎችም ይኖራሉ። ነገር ግን ልዩነቱ ሲመዘን መሠረታዊ ሆኖ የታየውን ስምምነት የሚያናጋ ከሆነ (ለምሳሌ ከላይ መሠረታዊ ልዩነት ነው በሚል በተገለፁት ምሳሌዎች ላይ ያለው ልዩነት ምስክሮች በስፍራው አልነበሩም የሚል መደምደሚያ ላይ እንደአደረሰው ዓይነት ማለት ነው) መሠረታዊ ልዩነት በመሆኑ ይመሳሰላሉ የሚባሉት ፍሬ ነገሮችም አብረው ይጣላሉ። ነገር ግን ምስክሮች በቦታው ላይ እንደነበሩ የሚታወቅ ሆኖ አንዱ በጀርባው በኩል ተኮሰበት ቢልና ሌላኛው በደረቱ በኩል ተኮሰበት ቢሉ በየት በኩል ተኮሰ በሚለው ላይ ልዩነት ቢኖርም በሌሎች ፍሬ ነገሮች ላይ የሰጡት ምስክርነት በስፍራው ነበሩ

የሚያስብላቸው ከሆነ ማስረጃው ሙሉ በሙሉ ውድቅ ሊደረግ አይገባም፡፡ እውነተኛ የሆኑትን ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ፣ ከድርጊቱ አፈፃፀም አካባቢያዊ ሁኔታ ጋር እና ከሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች (ለምሳሌ የህክምና ማስረጃ) ጋር በማገናዘብ መመዘን ያስፈልጋል፡፡

## ሐ. *<u>በማቅናት የተሰጠ የምስክርነት ቃል (Improvement)</u>*

አንድ ምስክር ለዋና ጥያቄ መልስ መስጠት ሲጀምር የተናገረው ቃል ጠያቂውን ያላረካው በመሆኑ ለሚያቀርብለት ቀጣይ ጥያቄ ቀደም ሲል የሰጠውን መልስ የሚያርም ወይም የሚያስተካክል መልስ ሊሰጥ ይችላል፡፡ እንዲሁም ለመስቀልኛ ጥያቄ መልስ መስጠት ጀምሮ ለዋና ጥያቄ የሰጠው መልስ የተበላሸበት መስሎ ሲሰማው በማስተካከል መልስ የሚሰጥበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ወይም ደግሞ ለድጋሚ ጥያቄ በሚሰጠው መልስ ለመስቀልኛ ጥያቄ የሰጠውን መልስ የሚያርም ወይም የሚያስተካክል መልስ ሊሰጥ ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የምስክርነት ቃል በማቅናት የተሰጠ (Improvement) ይባላል፡፡ ከማስረጃ ምዘና አንፃር የሚፈጥረው ችግር ተፈላጊውን ፍሬ ነገር ከማስረዳት አኳያ መጀመሪያ የተሰጠው መልስ እና ተቃንቶ የተሰጠው መልስ የተለያዩ መደምደሚያ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉበት ዕድል ሊኖር መቻሉ ነው፡፡

በመሠረቱ ይህ በማቅናት መልስ መስጠቱ በራሱ ምስክርነቱን ውድቅ አያደርገውም፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር ምስክሩ ቃሉን ለማቅናት የቻለበት ምክንያት ሊመረመር ይገባዋል፡፡ ማለትም፣

- በአነጋገር የተሳሳተውን ለማስተካከል መሆኑ፣ ወይም
- ጥያቄውን በሚገባ ሳይረዳ የሰጠውን መልስ ለማስተካከል መሆኑ ከታወቀ ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ የሚቻል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በማቅናት መልሱን የሰጠው ትክክለኛውን ነገር ለመሰወር ከሆነ ወይም ለማቅናት ምክንያት የሆነው ነገር የማይታወቅ ከሆነ መጀመሪያ የሰጠው ቃል ይወሰዳል (Rtanlal and Dhirajilal p. 39)::

## መ. *<u>ማጋነን የሚታይበት የምስክርነት ቃል (Exaggeration)</u>*

አንዳንድ ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ሊያስረዱበት ከቀረቡበት ፍሬ ነገር አፈፃፀም አንፃር የተጋነነ ሊሆን ይችላል፡፡ በተመሳሳይ ጉዳይ ለማስረዳት የቀረቡት ምስክሮች ከገለፁት በተለየ የድርጊቱን አፈፃፀም ወይም የተከሳሽ ተሳትፎን በማጋነን የምስክርነት ቃል ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ምስክርነታቸው እንዲታመንላቸው ሲሉ የመገንዘብ ችሎታቸውን ከፍ በማድረግ ወይም በማጋነን ይገልፃሉ፡፡ ሊመሠከርበት የመጣው ጉዳይ በጨለማ የተፈፀመ በሆነበት ሁኔታ ጨለማም ቢሆን የማየት ብቃት እንዳለው ለማስመሰል "በሌሊት ጥበቃ ሥራ የረጅም ጊዜ ልምድ ስላለኝ ከጨለማ ጋር ተለማምጃለሁ" እንደሚል ምስክር ዓይነት ማለት ነው፡፡

የተጋነነው የምስክርነት ቃል የሚኖረው ዋጋ የሚለካው ከተያዘው ጉዳይ አንፃር እየታየ (Case by case) ሲሆን ማስረጃው ሲመዘንም ከሌሎች ጋር ያለው ዝምድና ወይም ግንኙነት በጥንቃቄ እየተፈተሸ መሆን አለበት፡፡ የተጋነነውን ነጥሎ ማውጣት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ምስክሩ ሊያስረዳበት የመጣው ፍሬ ነገር አፈፃፀምና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ሊገቡ ይገባል፡፡

*__መወያያ ጥያቄዎች__*

1. ዐቃቤ ህግ በሦስት ተከሳሾች ላይ የአቀረበው ክስ በሰው ጤና ላይ የአካል ጉዳት ለማድረስ አስበው ‹ሀ› የተባለውን የግል ተበዳይ መኖሪያ ቤቱ ድረስ በመሔድ ሦስቱም ድንጋይ ወርውረው መላ ሰውነቱን በመምታትና የግራ ዓይኑን በማጥፋት ከባድ የአካል ጉዳት አድርሰዋል የሚል ሲሆን ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል፡
    1. 1ኛ ምስክር የግል ተበዳይ ሲሆን "ሦስቱም አንዳንድ ድንጋይ ወርውረው አንዱ ድንጋይ አይኔን ሌላው ማጅራቴን ሌላው ደግሞ ትከሻዬን መቱኝ"
    2. 2ተኛ ምስክር "ሦስቱም ድንጋይ ወርውረውበታል፡፡ አንዱ የግል ተበዳይን ሲመታ የቀሩት ደግሞ መሬት ወድቀዋል፡፡ አልመቱትም"
    3. 3ተኛ ምስክር "1ኛው ተከሳሽ የወረወረው ድንጋይ የተበዳዩን አይን፣ 2ኛው ተከሳሽ የወረወረው የተበዳይን ጭን፣ 3ኛው ተከሳሽ የወረወረው ድንጋይ

የተበዳይን ትከሻ መታው" ብለዋል፡፡ ምስክሮች የተከሳሾቹ ጐረቤት መሆናቸውን ጠቅሰው ድርጊቱ የተፈፀመው ከምሽቱ 3 ሰዓት ላይ መሆኑን ጭለማ እንደነበር "አንተ ቦጅቧጃ ዶሮ አናቂ" በማለት የግል ተበዳይን ሲሰድቡት ሰምተው እንደለዩዋቸው መስክረዋል፡፡ (ከጠ/ፍ/ቤት ወ/ይ/መ/ቁ. 4/80 የተወሰደ፡፡)

የምስክሮች ቃል ሲታይ ክሱን አስረድተዋል ማለት ይቻላልን?

2. በአንድ የወንጀል ክስ ጉዳይ ተከሳሹ በተለያዩ ጊዜያት ሁለት ወንጀሎችን ፈፅሟል ተብሎ ለቀረበበት ክስ ሁለቱንም ክሶች ያስረዳሉ በሚል የቀረቡት ምስክሮች የመሠከሩ ሲሆን (ድርጊቱን ፈፅሟል ብለዋል) ተከሳሹ ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ ሁለተኛው ድርጊት ተፈፀመ በተባለበት ጊዜ በወህኒ ቤት ታስሮ እንደሚገኝ የሰነድ ማስረጀ አቅርቦአል፡፡ (ከጠ/ፍ/ቤት የወ/ይ/መ/ቁ. 112/80 ላይ የተወሰደ፡፡)

ምስክሮች በሁለተኛው ድርጊት ላይ የሰጡት ምስክርነት ሀሰተኛ መሆኑ በመጀመሪያው ድርጊት ላይ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ውድቅ ያደርገዋልን?

### *7.4.2. የምስክሮች ቃል ተመሳሳይነት ስለሚያስከትለው ዉጤት*

የምስክሮች ቃል ዕርስ በርስ ሲገናዘብ ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፍተኛ ደረጃ ተመሳሳይ መሆኑ የሚደገፍ ነው፡፡ ነገር ግን ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ሙሉ ለሙሉ መመሳሰል የምስክሮች ቃል ምንም የማይወጣለት እውነት ነው ብሎ በርግጠኛነት መደምደም አይቻልም፡፡ ስለዚህም ማስረጃው ተመሳሳይ ሆኖ ቢገኝ እንኳን መገምገምና መመዘን አስፈላጊ ነው፡፡

የአገራችን ፍ/ቤቶች ማስረጃ ተመሳሳይ በሆነ ጊዜ የሚወሰዱት አቋም ሲታይ በአብዛኛው የማስረጃው ግምገማ የሚያተኩረው በመከላከያ ማስረጃዎች የምስክርነት ቃል ላይ ነው፡፡ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቃል ተመሳሳይ ሲሆን "ልዩነት በሌለው ሁኔታ አስረድቷል"

የሚል መደምደሚያ ሲሰጡ፤ የመከላከያ ማስረጃ ቃል ተመሳሳይ ሲሆን ደግሞ "የመከላከያ ምስክሮች የሰጡት ቃል ተመሳሳይነት ቢኖረውም በጥናት ላይ የተመሠረተ ነው" በማለት ውድቅ ሲያደርጉት ይስተዋላል፡፡ ይህ እንደአቋም መወሰድ የሌለበት ነው፡፡ የምስክርነት ቃሉ ተመሳሳይነት ቢኖረውም የተለያዩ የመመዘኛ ስልቶችን በመከተል እውነትነቱ ሊጣራ የሚገባው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ምዘናው ግን የዐቃቤ ህግንም ሆነ የመከላከያ ማስረጃን የሚያጠቃልል ነው፡፡ በዚህም መሠረት እንዲህ ዓይነት የምስክርነት ቃል ሲመዘን፡

- ✓ የምስክሮቹ ቃል ትክክለኛነት ሊያስረዱ ከቀረቡበት ጭብጥና ከተከሰተበት ጊዜና ቦታ አንፃር ሊመዘን ይገባል፡፡ ምስክሮች በዚያ ጊዜና ቦታ ለመገኘት ያላቸው አጋጣሚ ይመረመራል፡፡
- ✓ ምስክሮች ያስረዱበታል የተባለው ድርጊት ተከሰተ በተባለበት እና ምስክሮቹ ችሎት ቀርበው በመሰከሩበት ጊዜ መካከል ያለው ርቀት ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል ልዩነቱ-ሰፊ በሆነ መጠን በተመሳሳይ ሁኔታ የማስታወስ ዕድል እየጠበበ ይሄዳል፡፡
- ✓ ማስረጃው ሊያስረዳ የቀረበበት ፍሬ ነገር ዓይነት ግምት ውስጥ ሊገባ ይችላል (አደጋን፣ ሐይማኖታዊ በዓላትን በሚገባ በማስተዋል ከረጅም ጊዜ በኋላም ለማስታወስ የሚቻል ሲሆን ተራ ክስተቶችን ግን ብዙ ሰዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ከረጅም ጊዜም በኋላም ለማስታወስ ይከብዳቸዋል)፡፡
- ✓ ምስክሮች የመሠከሩበትን ፍሬ ነገር አንድ ላይ ሆነው እንዴት ለመከታተል እንደቻሉ መመርመር አለበት፡፡
- ✓ ምስክሮች ከምስክር አቅራቢው ሰው (የዐ/ህግ ምስክር ከሆነ ከግል ተበዳይ) ጋር ያላቸው የግል ወይም ማህበራዊ ግንኙነቶች ሊታዩ ይገባል፡፡ በዝምድና፣ በወዳጅነት የሚተሳሰሩ ምስክሮች ከማይተዋወቁ ምስክሮች የተሻለ የመጠናናት ዕድልና ፍላጐት ሊኖራቸው ይችላልና፡፡

## *7.5. ሳይጠቀሱ የታለፉ ፍሬ ነገሮች (Omissions) የሚያስከትሉት ዉጤት*

ስለ አንድ ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት የቀረቡ ምስክሮች በቂና የተሟላ መረጃ ቢሰጡ ምስክሮች የሰጡት ቃል የአስረጅነት መመዘኛውን ማሟላት

አለሟሟላቱን ለመወሰን የበለጠ እንደሚረዳ የሚታወቅ ነው፡፡ ሆኖም የቀረቡት ምስክሮች ሳይጠየቁ በመቅረታቸው፣ ወይም ተጠይቀውም ማስታወስ ባለመቻላቸው ምክንያት ያልተጠቀሱ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ሳይጠቀሱ የታለፉ ነገሮች በማስረጃ ምዘና ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ጉዳዩ ወንጀል ወይም ፍትሐብሔር መሆኑ ልዩነት ሊፈጥር የሚችል ቢሆንም ሳይጠቀሱ የሚታለፍ ፍሬ ነገሮች በሁለቱም ጉዳዮች ላይ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ማወቅ ይገባል፡፡

ሳይጠቀሱ ወይም ሳይገለፁ ወይም ሳይቀርቡ የሚታለፉ ፍሬ ነገሮች በመሠረቱ ምስክሮች በሰጡት ቃል ውስጥ የሚንፀባረቁ ቢሆኑም ከዚህ አልፎም ሌሎች ማስረጃዎችንም ሊመለከቱ ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንፃር አስተማማኝ መደምደሚያ ለመስጠት የሚያስችሉ ሌሎች ማስረጃዎች አለመቅረብም አብሮ ሊታየ የሚገባው ነው፡፡ በዚህም መሠረት፡-

- ✓ ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳ ምክንያት (motive) ሳይገለፅ ቢቀር፣
- ✓ ድርጊቱ መፈፀሙን ወይም ተፈፅሞም ከሆነ የምክንያትና ውጤት ግንኙነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ማስረጃ አለመቅረብ (የህክምና ማስረጃ አለመቅረብ)
- ✓ ድርጊት የተፈፀመበት መሳሪያ አለመቅረብ ወይም አለመታወቅ
- ✓ ጊዜና ቦታው አለመገለፅ አዘውትረው የሚያጋጥሙ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ (ማለትም መነሻ ምክንያት አለመገለፅ፣ የሀኪምና ማስረጃ አለመቅረብና ድርጊቶች የተፈፀሙበት መሳሪያ አለመቅረብ) የምስክሮችን ቃል በመመዘን ረገድ የሚያስከትለውን አስተዋጽኦ ቀጥሎ ይገለፃል፡፡

### *<u>7.5.1. ድርጊትን ለመፈፀም ያነሳሳ ምክንያት (motive) አለመገለፅ</u>*

ማስረጃ ሊያስረዳበት የቀረበው ጭብጥ ወይም ፍሬ ነገር አንድ አድራጐትን የሚመለከት የሆነ እንደሆነ ይህንን ድርጊት ለመፈፀም ያነሳሳ ምክንያቶች መታወቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በተለይ በወንጀል ጉዳይ ላይ ይህ መታወቁ አስፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው የጥፋተኛነት ውሳኔን ከማስገኘት አንፃር ወንጀሉን የሚያቋቁመውን የሀሳብ ክፍል ለማረጋገጥ ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳው ምክንያት መታወቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የቀረበው ማስረጃ ድርጊቱን መፈፀሙን ቢያስረዳም ለመፈፀም ምክንያት የሆነውን ፍሬ ነገር አለመጥቀሱ ማስረጃውን ሁል ጊዜም ሚዛን ያሳጠዋል ለማለት አይቻልም፡፡ በብዙ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳ ምክንያት ከሀሳብ ክፍሉ ጋር የማይገናኝ ሊሆን እንደሚችል መታወቅ አለበት፡፡ ለምሳሌ በቸልተኛነት ለሚፈፀም ወንጀል የሀሳብ ክፍሉ ተገቢ ጥንቃቄ አለማድረግ ስለሚሆን ከዚህ አልፎ ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳው ምክንያት (motive) መረጋገጥ አለበት የሚል አቋም መውሰድ አይገባም፡፡ በተጨማሪም የድርጊቱን አፈፃፀም የሚያስረዳ ማስረጃ እግረ መንገዱን ምክንያቱን ለማረጋገጥ ሊረዳ ይቻላል፡፡ ከባለቤቱ ፈቃድ ውጭ የሰው ቤት ዘው ብሎ ገብቶ ዕቃ ወስዶ የተገለገለበት እንደሆነ ንብረቱን የወሰደው "ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት በማሰብ" መሆኑን ድርጊቱ ራሱ ያረጋግጥልናል፡፡ ስለዚህም፡-

- ✓ ድርጊቱን ለመፈፀም መነሻ ምክንያት መጠየቅ አስፈላጊ መሆኑን አስቀድሞ መመርመር ያስፈልጋል፣
- ✓ ድርጊቱን ለመፈፀም ምክንያቱ ከድርጊቱ አፈፃፀም ሊታወቅ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ማወቅ ያስፈልጋል፡፡
- ✓ ይኸው ምክንያት አስፈላጊ መሆኑ ተረጋግጦ ነገር ግን የቀረበው ማስረጃ ላይ ያልተገለፀና ከተጠቀሰው የማስረጃ ቃልም የማይገኝ ከሆነ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚያስከትለውን ውጤት ከድርጊቱ አፈፃፀም አካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

### *7.5.2. የህክምና ማስረጃ አለመቅረብ*

በአካል ወይም በህይወት ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት ለሚቀርብ የወንጀል ወይም የፍትሐብሔር የጉዳት ካሳ ክስ ጉዳይ የህክምና ማስረጃ መቅረቡ የሚሰጠው አገልግሎት ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ ማስረጃ መቅረቡ፡-

- ✓ በምክንያትና በውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት ለማረጋገጥ ያስችላል፣

- ✓ የተከሰሰው ሰው ፈፀመው የተባለውና በምስክሮች የተናገረው ድርጊት (ግድያ፣ ወይም አካል ማጉደል) በርግጥም የተፈፀመ መሆኑን ለማረጋገጥ
- ✓ የጉዳቱን ደረጃና መጠን ለማወቅ (በወንጀል ከባድ የአካል ጉዳት ነው ወይስ ቀላል የሚለውን ለማወቅ፤ በፍትሐብሔር ደግሞ የጉዳቱን ደረጃና የካሳውን መጠን ለመወሰን) ያገለግላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ተፈላጊው ፍሬ ነገር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለማረጋገጥ የህክምና ማስረጃ የግዴታ መቅረብ አለበት መባል የለበትም። ሰው ሲሞት ወይም የአካል ጉዳት ሲደርስበት በሐኪም መመርመር አለበት የሚል አስገዳጅ ደንብ በሌለበት ሁኔታ፤ ህክምና ለማግኘት የማይቻልበት በርካታ ምክንያት መኖሩ እየታወቀ ፍሬ ነገሩ መኖሩ ወይም አለመኖሩ በህክምና ማስረጃ አልተረጋገጠም፤ ወይም አልተደገፈም በሚል ምክንያት የምስክሮችን ቃል ማጣጣል ተገቢ አይደለም። የህክምና ማስረጃ ሊቀርብ ያልቻለበትን ምክንያት መጠየቅ ተገቢ ይሆናል። ነገር ግን ይህ ማስረጃ ባይኖርም ምስክሮች የሰጡትን ቃል መመዘንና ይኸው ቃል በራሱ ፍሬ ነገሩ መኖሩን የሚያረጋግጥ ከሆነ ወደዚህ መደምደሚያ ላይ መድረስ ይገባል። ስለዚህ ጠንካራ መሠረት ያለው የምስክርነት ቃል በህክምና ማስረጃ አልተደገፈም ተብሎ ውድቅ ሊደረግ አይገባም።

### *7.5.3. ሌሎች ያልተገለጹ ፍሬ ነገሮች ወይም ማስረጃዎች*

በወንጀል ጉዳይ ወንጀል የተፈፀመበት መሳሪያ ወይም የወንጀል ውጤት የሆነ ነገር በማስረጃነት ሳይቀርብ ሊታለፍ ይችላል፤ ወይም ምስክሮች ሳይገልፁት ሊያልፉ ይችላሉ ወይም ቀርቦ እያለ ምስክሮች ለይቶ ለማመልከት ሊቸገሩ ይችላሉ። ወይም ድርጊቱን ፈፀመ በሚል ስሙን የገለፁትን ሰው እንዲያሳዩ ሲጠየቁ ማሳየት ሊያቅታቸው ይችላል። ይህ በምስክሮች ቃል ምዘና ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ ምንድ ነው? የሚለው በጥንቃቄ መታየት የሚገባው ነው።

ወንጀል የተፈፀመበት መሳሪያ ወይም የወንጀል ፍሬ የሆነ ዕቃ በኤግዚቢትነት ያለመቅረቡ ማስረጃውን ውድቅ ያደርገዋል በሚል መደምደም አይቻልም። ኤግዚቢቱን

በማየት ፍ/ቤቱ የተሻለ ግንዛቤ መውሰድ ይችል የነበረውን ዕድል ያስቀርበታል፡፡ ነገር ግን የምስክርነት ቃሉን ራሱን ችሎ እንዳይመዘን ከማድረግ አይከለክልም፡፡

ምስክሩ ድርጊቱ የተፈፀመበትን መሳሪያ ሳይገልፅ ቢያልፍ ወይም ድርጊቱ ያስገኘውን ዕቃ ሳይገልፅ ቢቀር ይህ ጉድለት የሚለካው የክስን መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች ለማረጋገጥ ካለው ድርሻ አንፃር ነው፡፡ ስርቋል የተባለውን ንብረት ምስክሩ ሳይገልፅ ከቀረ የስርቆት ወንጀል ተፈፅሟል ለማለት አያስችልም፡፡ ገድሏል ተብሎ ለቀረበ ክስ ድርጊቱ የተፈፀመበት መሳሪያ ሊገለፅ ይገባዋል፡፡ ይህ መሠረታዊ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን በጠመንጃ መሆኑ ተገልፆ ባለበት ሁኔታ "የጠመንጃውን አይነት ለይቶ አልገለፀም በሚል" "ገድሏል" የሚለውን የምስክርነት ቃል ውድቅ ማድረግ አይቻልም፡፡

ችሎት የቀረበው ምስክር የምስክርነት ቃሉን ከሰጠ በኂላ ድርጊቱን ፈፅሟል፡፡ በሚል የጠቀሰውን ሰው ወይም ፈፅሞበታል ያለውን መሳሪያ እንዲያሳይ ሊጠየቅ ይችላል፡፡ ይህ የሚያስከትለው ውጤት ግን በጥንቃቄ ሊመዘን ይገባዋል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

- ✓ ምስክር ድርጊቱን ፈፀመ በማለት በስም የጠቀሰውን ሰው እንዳያሳይ ወይም እንዲለይ ተጠይቆ ማሳየት ቢያቅተው ይህ ሁኔታ በማስረጃ ምዘና ላይ ከሚያስከትለው ተፅዕኖ አንፃር ሊፈተሽ ይገባዋል፡፡ ድርጊቱን ፈፅሟል የተባለውን ሰው በጊዜው እንዴት አወቀው? ስሙን ማን ነገረው? አሁንስ እንዴት ማሳየት አቃተው? የሚሉት ጥያቄዎች ሊቀርቡና ማስረጃው ለነዚህ ጥያቄዎች በሚሰጠው ምላሽ መሠረት ሊመዘን ይገባል፤
- ✓ ማስረጃውን ወይም ዕቃውን ማሳየት አለመቻልም እንዲሁ ምስክሩ ድርጊቱ ሲፈፀም ከነበረው ቅርበት፣ ከጊዜው ሁኔታ … አንፃር መለካት አለበት፡፡ (Ratanlal and Dhirajilal p. 38)

***<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>***

ዐቃቤ ህግ 3 ተከሳሾች ሆን ብለው ሰውን ለመግደል በማሰብ ሟች ‹በ› የተባለውን ገበያ ውሎ ወደ ቤቱ ሲመለስ ከኂላው ተከታትለው ደርሰው በዱላ

ደብድበውና በጩቤ በመውጋት ጨካኝና ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ገድለውታል በሚል ላቀረበባቸው ክስ የቀረቡት ምስክሮቹ በሰጡት ቃል "(እኛ) ምስክሮች ከሟች ጋር ገበያ ውለን ስንመለስ ተከሳሾች ውሃ ከበላው ጉድባ መሬት ላይ ተነሱና ወደ እኛ መጡ። ከዚያም ፊትና ኋላ ሆነን ስንሄድ በመካከላችን ያለውን ሟች በዱላ መትተው እና በጩቤ ወግተው ጣሉት። ከዚያ ወድቆ ሞተ። ተከሳሾች እና ሟች ይተዋወቃሉ። በመካከላቸው ፀብ ይኑር አይኑር አናውቅም" በማለት የመሠከሩ ሲሆን ፍ/ቤቱ ማስረጃው በተከሳሾች ላይ አላስረዳባቸውም በማለት በነፃ ሲያሰናብታቸው ከሰጣቸው ምክንያቶች ውስጥ "ለድርጊቱ መፈፀም ምክንያት የሆነው ነገር ባልተገለፀበት ሁኔታ በዱላ ደብድበውና በጩቤ ወግተው ገደሉት ተብሎ የተሰጠው የምስክርነት ቃል ለጥርጣሬ የተጋለጠ ነው" የሚለው ይገኝበታል። (ከጠ/ፍ/ቤት የወ/ይ/መ/ቁ. 67/80 የተወሰደ)።

ፍ/ቤቱ የሰጠው ምክንያት ተገቢ ነውን?

## *7.6. <u>ጥቅም ያላቸው ምስክሮች የምስክርነት ቃል ምዘና</u>*

በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር ጉዳይ (የአስረጅነት ደረጃው እና በማስረጃ ምዘና ሂደት የሚሰጠው ክብደት የተለያየ ቢሆንም) በምስክርነት የሚቀርቡ ሰዎች በሚመሠክሩበት ጉዳይ አወሳሰን ላይ የተለየ ጥቅም ወይም ፍላጐት ሊኖራቸው ይችላል። ተከራካሪ ወገኖች በራሳቸው ጉዳይ ምስክር በመሆን (በወንጀል ጉዳይ የግል ተበዳዩን ይጨምራል)፣ ወይም ምስክሮቹ ከተከራካሪ ወገኖች ጋር ባላቸው ፀብ፣ ዝምድና ወይም የተለየ የጥቅም ተጋሪነት ወይም ወዳጅነት መነሻ ወገንተኛነት በማሳየት በጉዳዩ አወሳሰን የተለየ ፍላጐት ሊኖራቸው ይችላል። ወይም ደግሞ አብረው በግብረ አበርነት ከተከሰሱት መካከል ወይም በፍትሐብሔር ጉዳይ ተጣምረው ከከሰሱት መካከል አንደኛው በሌላኛው ላይ ወይም ሌላኛው ምስክር ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ። በዚህ ሁኔታ ግንኙነት ያላቸው እና ወገንተኛ ይሆናሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎች የተለየ ጥቅም ያላቸው ምስክሮች (Interested witnesses) የሚባሉ ሲሆን የምስክርነት ቃላቸው ሲመዘን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በዚህ ክፍል እንደነዚህ ዓይነት ምስክሮች የሚሰጡት ቃል ሲመዘን ግምት ውስጥ ማስገባት የሚገቡ ነገሮች በአጭሩ ይገለፃሉ።

### *7.6.1. ፀብ ወይም ዝምድና*

ምስክሮች ከተከራካሪ ወገኖች ጋር ፀብ ወይም ዝምድና ቢኖራቸውም ከመመስከር ሊከለከሉ አይችሉም፡፡ ሆኖም ፀብ ወይም ዝምድና መኖሩ ከታወቀ የምስክርነት ቃላቸው እውነተኛ መሆኑ ወይም ደግሞ በዚህ ፀብ ወይም ዝምድና መነሻ የተፈጠረ፣ የተጋነነ ወይም የተምታታ መሆኑ በጥንቃቄ ሊመዘን ይገባዋል፡፡

ፀብ ወይም ዝምድና መኖሩ አስቀድሞ ሊረጋገጥ የሚገባው ነገር ነው፡፡ ዝምድና ትርጉሙ ሊሰፋም ሊጠብም የሚችል መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ በጉሳ ላይ የተመሠረተ ዝምድና ሊጠቀስ የሚችለውን ያህል ቅርብ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድናም ከዝምድና የማይቆጠርበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ፀብን በተመለከተም ማናቸውም ዓይነት አለመግባባት ፀብ ያሰኛል ማለት አይቻልም፡፡ የሆነ ሆኖ ፍ/ቤቱ የምስክርነት ቃሉን ሲመዝን ይመሠክሩበታል ከተባለው ፍሬ ነገር ወይም ጭብጥ አካባቢያዊ ሁኔታ አንፃር ማየትና የተሰጠው የምስክርነት ቃል እውነተኛ መሆኑን፣ ወይም ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት በማሰብ የተቀነባበረ፣ የተጋነነ ወይም የወረደ መሆኑን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

### *7.6.2. የተከራካሪ ወገን ምስክርነት*

በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር ተከራካሪ ወገኖች በራሳቸው ጉዳይ የምስክርነት ቃል ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ በወንጀል ጉዳይ የግል ተበዳዩ (በከሳሽ ዐቃቤ ህግ በኩል) እና ተከሳሹ፤ በፍትሐብሔር ጉዳይ ደግሞ ከሳሽና ተከሳሽ ለራሳቸው ጉዳይ ምስክር መሆን ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ምስክሮች በጉዳዩ አወሳሰን የተለየ ፍላጐት ሊኖራቸው እንደሚችልና እንደሚጠበቅም መታወቅ አለበት፡፡ ከዚህ አንፃር፡፡

- ☞ ከግል ተበዳይ ውጭ ያሉ ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ የሚሰጡት ቃል ክርክራቸውን የሚያጠናክር በመሆኑ ምስክርነታቸው ክብደት ሊሰጠው አይገባም፡፡
- ☞ በወንጀል ጉዳይ የግል ተበዳይ ምስክር ሆኖ በራሱ ላይ ስለአደረሰው ጉዳት የሚሰጠው የምስክርነት ቃል እውነተኛነቱ ተፈፀመ ከተባለው ድርጊት ከባድነት እና ከአፈፃፀሙ አካባቢያዊ ሁኔታ አንፃር ሊገመገም ይችላል፡፡ ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰበትና (ለምሳሌ አይን መጥፋት) ይህንን ለማስረዳት የመጣ የግል ተበዳይ አይኑ መጥፋቱ እስከተረጋገጠ ድረስ አይኑን ያጠፋውን ሰው ትቶ ሌላ ሰው ይወነጅላል ለማለት አዳጋች ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ዋናው መመዘኛ ምስክሩ ድርጊቱን የፈፀመው ተከሳሽ መሆኑን ሊያረጋግጥ የቻለበት ሁኔታ ነው፡፡ በሌላ በኩል ቀላል ጉዳት ወይም የእጅ እልፊት ወይም ስም ማጥፋትን ለማስረዳት የሚቀርብ የግል ተበዳይ የሚሰጠው የምስክርነት ቃል ከሆነ እውነቱ በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊመረመር ይገባል (Ratanlal and Dhirajlal ገፅ 22)፡፡
- ☞ እንዲሁም አንዳንድ ወንጀሎች በባህሪያቸው ከግል ተበዳይ ሌላ ማስረጃ ሊገኝ የማይችልባቸው፤ ወይም የግል ተበዳይ በርግጥ ካልተፈፀመበት በስተቀር አደባባይ የማያወጣቸው ሊሆኑ ስለሚችሉ ይህም በማስረጃ ምዘና ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡ ለምሳሌ በአብዛኛው የመድፈር ወንጀል የሚፈፀመው ከግል ተበዳይ ውጭ ሌላ ሰው በሌለበት ሁኔታ ሲሆን ተደፍራለች የተባለችው ሴትም መደፈርዋ እርግጥ ካልሆነ በስተቀር (አንዳንዴ ተደፍሬያለሁ የሚባልበት የተለየ ምክንያት ቢያጋጥምም) ተደፍሬያለሁ ብላ አደባባይ ስለማትወጣ ማስረጃው ክብደት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በሌላ ደጋፊ ማስረጃ አላስረዳህም በሚል ውድቅ ማድረግም አይገባም፡፡

### *7.6.3. የግብረ አበር ምስክርነት*

በመሠረቱ ግብረ አበር የሆነ ሰው አብሮት በተከሰሰው ላይም ሆነ ለዚሁ ሰው ምስክር እንዳይሆን የሚከላከል ህግ የለም፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳይ በጣምራ የከሰሱ ወይም የተከሰሱ ሰዎችም አንደኛው ለሌላኛው ሊመሰክሩ ይችላሉ፡፡ ያም ሆኖ ግን አብሮት ለከሰሰው ወይም ለተከሰሰው ሰው በመርዳት ወይም ኃላፊነቱን ከራሱ አውርዶ አብሮት የተከሰሰው ሰው ኃላፊነቱን እንዲሸከም በማድረግ ዓላማ በመጉዳት የምስክርነት ቃሉን

ሊሰጥ ይችላል፡፡ ስለዚህ የምስክርነት ቃላቸው ሲመዘን በዋናነት ለመመስከር የተነሳሱበት ምክንያት ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

## *7.7. ልዩ መደብ ያላቸው ምስክሮች ቃል ምዘና*

### *7.7.1. የህፃናት ምስክርነት ቃል ምዘና*

ህፃናት የሚጠየቁትን ጥያቄ መገንዘብና መልስ መስጠት እስከቻሉ ድረስ በምስክርነት ከመቅረብ እንደማይከለከሉ አስቀድሞ ተገልፆአል፡፡ ነገር ግን የሚሰጡት የምስክርነት ቃል በጥንቃቄ ሊመዘን ይገባዋል፡፡ በጥንቃቄ ሊመዘን ይገባል የተባለውም "ህፃናት ማስረጃ ስለሚሆኑበት ጉዳይ በሌሎች ሰዎች ተፅዕኖ ስር በቀላሉ ሊወድቁ ስለሚችሉና ሊደለሉም ስለሚችሉ ከተገነዘቡት ፍሬ ነገር ውጭ በሰዎች ግፊት ትክክለኛ ያልሆነ ምስክርነት ይሰጣሉ" የሚል ስጋት ስላለ ነው፡፡ (May, p. 462)፡፡

በዚህም መሠረት የህፃናት የምስክርነት ቃል ሲመዘን፡-

- ዕድሜያቸው ግምት ወስጥ ሊገባ ይገባል፡፡ ዕድሜያቸው ትንሽ በሆነ መጠን የመደለል ወይም በሌላ ተፅዕኖ ሥር የመውደቅ ዕድላቸው የሰፋ ሊሆን ይችላል፡፡
- የሰጡት የምስክርነት ቃል ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት መገናዘብ ይኖርበታል፤
- ይመሠከሩበታል የተባለው ፍሬ ነገር በተከሰተበትና ቀርበው በመሠከሩበት ጊዜ መካከል ያለው ልዩነት ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡ ጊዜው ሰፊ በሆነ ቁጥር የማስታወሱ ሁኔታ እየደከመ ይሄዳል ተብሎ ይገመታል (May, p. 463)::

### *7.7.2. በዕድሜ የገፋ፣ የአካል ወይም አዕምሮ ጉድለት ያለባቸው ምስክሮች ቃል ምዘና*

በማስረጃነት የቀረቡት ምስክሮች የዕድሜ መግፋት የተነሳ የማስታወስ ችሎታቸው የጠፋ ባይሆንም የደከመ ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም በአዕምሮ ወይም በአካል ጉዳት የተነሳ

ምስክርነታቸው የተሟላ ላይሆን ይችላል፡፡ ያም ሆነ ይህ በምስክርነት እስከቀረቡና ቃላቸውን እስከሰጡ ድረስ የሰጡት የምስክርነት ቃል ሊመዘን ይገባዋል፡፡ እነዚህ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃልም በሌላ ደጋፊ ማስረጃ መታገዝ አለመታገዙን ማረጋገጥ ጠቃሚ ነው፡፡

## *7.7.3. የኤክስፐርት ማስረጃ ምዘና*

ኤክስፐርቶች ወይም ልዩ አዋቂዎች ችሎት ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን በሚሰጡበት ጊዜ ምስክርነታቸው ሳይመዘን በቀጥታ አስረጅነትን ያገኛል ማለት አይቻልም፡፡ ኤክስፐርት የሰጠው ምስክርነት ነው ስለተባለ ፍ/ቤቱ እንዳለ በጥሬው መቀበል አይገባውም፡፡ ከሌሎች ማስረጃዎች የተለየ ክብደት ይሰጠዋል ማለትም አይደለም፡፡ (አለማየሁ ኃይሌ፣ ገፅ 63)፡፡

ስለዚህም ፍርድ ቤቶች የኤክስፐርት ማስረጃን እንዳለቀ ነገር አድርገው ለመቀበል የማይገደዱ ሲሆን ይህንን ማስረጃ ፡-

- ☞ ስለተሰጠው የኤክስፐርት አስተያየት ትክክለኛነት የቀረቡ ማረጋገጫዎችን
- ☞ ኤክስፐርቱ አስተያየቱን ወይም መደምደሚያውን የሰጠው የራሱን እውቀትና ምርመራ ተጠቅሞ ወይም ሌላ ባለሞያነቱን ፍ/ቤቱ ያላረጋገጠውን ሰው ጠይቆ ያገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ መሆኑን፣
- ☞ ኤክስፐርቱ በተያዘው ጉዳይ ላይ ያለውን ገለልተኛነት (ማለትም ኤክስፐርቱ የተጠራው በማን ወገን ነው፣ ከጉዳዩ ጋር ያለው የግል ግንኙነትስ ምን ይመስላል ከሚሉት ጥያቄዎች አንፃር)፣
- ☞ ኤክስፐርቱ እንዲያረጋግጥ ወይም አስተያየት እንዲሰጥ ከተሰጠው መመሪያ ወይም ጥያቄ ጋር የሰጠው አስተያየት ያለውን ግንኙነት…ወዘተ

መሠረት በማድረግ ሊገመግመው ይገባል፡፡ (ዓለማየሁ ኃይሌ ገፅ 63)፣ (የጠ/ፍ/ቤት ፍ/ይ/መ/ቁ. 201/77፡፡)

# ምዕራፍ 8

# የሰነዶችንና ኤግዚቢት ማስረጃዎችን አስረጂነት ስለመመዘን

**ዝርዝር አላማዎች**

ሰልጣኞች ይህንን ምእራፍ ሲያጠናቅቁ ፣

- ማስረጃዉን ለመስጠት ያላቸዉን ብቃትና ቅርበት መሠረት አድርገዉ የጽሁፍ ማስረጃዎችን የመመዘን ክህሎት ያገኛሉ፤
- የፅሁፍ ሰነዶች በሚቃረኑበት ጊዜ እንዴት ማስረጃን መመዘን እንዳለባቸዉ በቂ ግንዛቤ ያገኛሉ ተግባር ላይም ያዉላሉ፣
- በኦዲት ማስረጃዎች ላይ የሚቀርቡ መቃወሚያዎችን በአግባቡ በማስተናገድ መመዘን ይችላሉ፤
- የህትመት ዉጤቶችን፣ የቴፐና የቪዲዮ ካሴቶችን፣ የፎቶግራፍ ማስረጃዎችንና የኤግዚቢት ማስረጃዎችን የመመዘን ክህሎት ይረዳሉ ተግባር ላይም ያዉላሉ፤

## *8.1. ጠቅላላ*

ዉድ ሠልጣኞች በፍትሐብሔርም ሆነ በወንጀል ጉዳይ ፍሬ ነገርን ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል ሰነዶችና ኤግዚቢቶች በማስረጃነት ሊቀርቡ እንደሚችሉ፤ በማስረጃነት ሲቀርቡ ግን አግባብነት እንዳላቸውና መቅረባቸውን የሚከላከል ህግ አለመኖሩ ሊረጋገጥ እንደሚገባ በምዕራፍ 3 ላይ ተጠቅሶአል፡፡ የአንዳንድ ፍሬ ነገሮችን መኖር ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል የሰነድ ማስረጃዎች ብቻ ሊቀርቡ እንደሚገባ ህግ የሚደነግግበት ሁኔታ መኖሩን ተመልክቶአል፡፡

ዉድ ሠልጣኞች እነዚህን ጥያቄዎች በግላችሁ ሞክሯቸዉ፡-

ሀ. የጽሁፍ ማስረጃዎች እንዴት ሊመዘኑ ይችላሉ?

ለ. ቴፐ፣ ቪዲዮ ካሴት፣ እና ፎቶግራፍ ማስረጃዎችን ስንመዝን ማድረግ ያለብን ጥንቃቄ ምን ይመስላችኋል?

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው የሰነድ ማስረጃዎች ወይም ኤግዚቢቶች ማስረጃ ሆነው ከቀረቡ በኂላ የሚመዘኑበት ሁኔታ ነው፡፡ ማለትም የሰነድ ማስረጃ ወይም ኢግዚቢት የተፈለገውን ፍሬ ነገር መኖር ማስረጃነቱን ወይም ማስተባበሉን ለመወሰን የማስረጃ ምዘና ተግባር ሲከናወን ግምት ውስጥ ሊገቡ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ትኩረት ይሰጣል፡፡

ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ከመገባቱ አስቀድሞ ግን የሚከተለው ሐሳብ በማስታወሻነት ሊያዝ ይገባዋል፡፡ ይኸውም ሰነዶችና ኤግዚቢቶች አግባብነት አላቸው የተባሉትን ፍሬ ነገሮች ከማስረዳት አንፃር አስተማማኝ ቢመስሉም ነገር ግን በጥልቀት ሲመረመሩ እና ሲመዘኑ አስተማማኝነታቸው ከምስክሮች ቃል የተሻለ ላይሆን ይችላል፡፡ የጽሁፍ ሰነድ፣ ወይም ካሴት፣ ወይም ፎቶ ግራፍ... ወዘተ ቀረበ ስለተባለ ከምስክር ቃል የበለጠ በአስተማማኝነት የሚያስረዳ መስሎ ቢታይም ነገር ግን አስተማማኝነቱን ሊሸረሽሩ ለሚችሉ በርካታ ጥያቄዎች የተጋለጠ ነው፡፡

ምስክሮች የፈለገ ተዘጋጅተው ቢቀርቡ ችሎት ላይ ከሚከናወን መስቀልኛ ጥያቄ ጋር ፊት ለፊት ስለሚጋፈጡ የሰጡት መልስ እውነተኛነት፣ ወይም ሐሰተኛነት፣ ተአማኒነት ወይም አጠራጣሪነት በቀላሉ ሊታወቅ ይችላል፡፡ ችሎት የምስክሮች እውነተኛነትና ሐሰተኛነት ማረጋገጫ መድረክ ነው፡፡ በሰነድ ላይ የተገለፀ ፍሬ ነገር ግን ከችሎት ውጭ የተፈጠረ እንደመሆኑ ማን እንደፈጠረው፣ መቼ እንደፈጠረው እና ለምን ዓላማ እንደፈጠረው ሰነዱ ራሱ አይናገርም፤ ወይም ቢናገርም አስተማማኝነቱ ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል ነው፡፡ እነዚህን ለመሠሉ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ በሌላ ደጋፊ ማስረጃ ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ስለዚህ የሰነድ ማስረጃ ቀረበ ማለት በሰነዱ ላይ የተገለፀው ፍሬ ነገርን ባለቀለት ሁኔታ አስረዳ ማለት አይደለም፣ በሚገባ ሊመዘን ይገባዋል፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪም የሰነድ ወይም ኤግዚቢት ማስረጃዎች ምዘና በማስረጃው አይነት የተነሳ የተለየ ምዘና ሂደት የሚከተል ቢሆንም ከምስክሮች ምዘና ጋር በተያያዙ የተገለፁት፡-

- ☞ ማስረጃው ያስረዳቸዋል የተባሉትን ፍሬ ነገሮች በሚገባ የመለየት፣
- ☞ በምክንያትና በውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት በሚገባ የመለየት፣
- ☞ እንዲሁም ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ ምዘና፤

ዘዴዎች በሰነድና ኤግዚቢት ማስረጃ ምዘና ላይም እንደ አግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

አስቀድሞ እንደተገለፀው የዚህ ምዕራፍ ትኩረት የሰነድ እና ኢግዚቢት ማስረጃዎች ምዘና ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የሰነድ ማስረጃ ምዘና የሚመለከታቸው በጽሁፍ የቀረቡ ሰነዶች፣ የቴፐና የቪዲዮ ካሴቶች፣ የፎቶ ግራፍ ማስረጃዎች … ወዘተ ሲሆኑ ኤግዚቢቶች ተብለው የሚገለፁት ደግሞ ፍሬ ነገርን ያስረዳሉ ተብለው የቀረቡ ነገሮች (ዕቃዎች፣ መሳሪያዎች …) ናቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ትኩረት የሚሰጥባቸውም በሥራ አጋጣሚ አዘውትረው በማስረጃነት ሲቀርቡ የሚስተዋሉት በጽሁፍ የተደረጉ ሰነዶች እና የቴፐና የቪዲዮ ካሴት እንዲሁም የፎቶግራፍ ማስረጃዎች ሲሆኑ በምዕራፉ የተገለፁት ሀሳቦች ከፍርድ ውሳኔዎችና ከሌሎች አገሮች ህጐች (ወይም ጽሁፎች) እንዲስማሙ ተደርገው የተወሰዱ ናቸው፡፡ ገለፃውም በአጠቃላይ ነጥቦች ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው፡፡

## 8.2. የጽሁፍ ሰነድ ማስረጃዎች ምዘና

### 8.2.1. ብቃትንና ቅርበትን መሠረት ያደረገ ምዘና

የሰነድ ማስረጃ ሲመዘን ትኩረት ሊደረግባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች አንዱ ማስረጃውን ያዘጋጀው ወይም የሰጠው አካል ይህንን ለመፈፀም ያለው ብቃት ወይም ቅርበት ነው፡፡ የጽሑፍ ሰነዱ ያዘለው ፍሬ ነገር ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ የሆነውን ፍሬ ነገር ያስረዳ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ፍሬ ነገሩ ተፈላጊውን ፍሬ ነገር ወይም ጭብጥ ያስረዳል ስለተባለ ብቻ ክብደት ይሰጠዋል ማለት አይቻልም፡፡ ሟች የሞተበትን ምክንያት ለማወቅ የህክምና ማስረጃ አስፈላጊ የመሆኑን ያህል፤ በማስረጃነት የቀረበው ሰነድም ሟች

የሞተበትን ምክንያት የመግለፁን ያህል ይህንን ያረጋገጠው ሰው ወይም ድርጅት ማስረጃውን ለመስጠት የሙያ ብቃት ከሌለው በሰነዱ ላይ ለተጠቀሰውና ስለሟች ሞት ምክንያት ለሚናገረው ክብደት ሊሰጠው አይችልም ስለዚህም የሰነድ ማስረጃ ሲመዘን፡

- ☞ ማስረጃ ሰጭው ተፈላጊውን ማስረጃ ለመስጠት ሥልጣን አለው ወይ?
- ☞ ማስረጃ ሰጭው ተፈላጊውን ማስረጃ ለመስጠት የሙያ ብቃት አለው ወይ?
- ☞ ማስረጃ ሰጭው በሰነዱ ላይ የተገለፀውን ፍሬ ነገር የማወቅ ቅርበት አለው ወይ?

የሚሉትን ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ከላይ የተገለፀውን የበለጠ ለማብራራት ያህል፡-

- ☞ የባህል ሐኪም ነኝ የሚል ሰው ሟች የሞተው በዚህ ምክንያት ነው የሚል ማረጋገጫ ቢሰጥ ክብደት ሊሰጠው ይገባል ወይ?
- ☞ የፍቺ ማስረጃ መስጠት የሚችለው ፍ/ቤት ነው የሚል ህግ እያለ የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች የሰጡት የፍቺ ወረቀት ፍቺን ለማረጋገጥ ብቃት አለው ወይ?
- ☞ የሬሳ ምርመራ ውጤት ከአንድ አነስተኛ የጤና ኬላ ቢቀርብልንና ማስረጃውን የሰጠው ሰው "ጤና ረዳት" በሚል የገለፀ ቢሆን ክብደት ሊሰጠው ይገባል ወይ? …

ወዘተ በማለት መጠየቅ ይኖርብናል፡፡

## መወያያ ጥያቄዎች

ከሳሽ ባቀረበው ክስ ንብረቱ የሆነችው ሚኒ ባስ መኪና ለደረሰባት አደጋ ኢንሹራንስ እንዲከፍለው ተከሳሹን (የኢንሹራንስ ድርጅት ነው) ሲጠይቀው "አሥርቼ እሰጥሀለሁ" በሚል ተከሳሹ መኪናዋን መረከቡን፤ ነገር ግን መኪናዋን ከተረከበ 3 ዓመት ያለፈው መሆኑን ጠቅሶ የመኪናዋን ዋጋ ብር 60,000፤ ለሦስት ዓመት ያለሥራ በመቆሟ የቀን ገቢ በብር 300 ታስቦ ብር 329,500 በጠቅላላው ብር 389,000 እንዲከፍለው የጠየቀ

ሲሆን፣ ስለ ቀን ገቢ ያስረዳል በማለት አባል የሆነው የትራንስፖርት ባለንብረቶች ማህበር የሰጠውንና የተጣራ የቀን ገቢዋ ብር 300 መሆኑን የሚገልፀውን ደብዳቤ አያይዟል፡፡ ተከሳሹ ስለቀን ገቢዋ የተሰጠው ደብዳቤ ሊታመን እንደማይገባ ገልፆ ይከራከራል፡፡ (ከ.ደ.ክ.ጠ.ፍ.ቤት.ይ.መ.ቁ. 119/92) የተወሰደ፡፡

- ☞ ፍ/ቤቱ የቀን ገቢዋን በሚመለከት የቀረበውን ማስረጃ ተቀብሎ በዚህ መሠረት ሊወሰን ይገባል?

## *8.2.2. የፅሁፍ ሰነዶች በሚቃረኑበት ጊዜ ስለሚፈፀም የማስረጃ ምዘና*

በማስረጃነት የቀረቡት የጽሁፍ ሰነዶች እርስ በርስ ሊቃረኑ ወይም ልዩነት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ወይም ደግሞ በሰነድ ማስረጃ ላይ የተገለፀው ፍሬ ነገር ምስክር ከሰጠው ምስክርነት ጋር የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ ለማስረዳት ያህል፡-

- ☞ ከላይ በጥያቄ መልክ የተጠቀሰው የቀን ገቢን አስመልክቶ ከትራንስፖርት ባለንብረቶች ማህበር የተፃፈለት ደብዳቤ እና ተከሳሹ በበኩሉ ከአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ስለከሳሽ የቀን ገቢ ያቀረበው ደብዳቤ፣
- ☞ ስለአንድ የገንዘብ ጉድለት ጉዳይ የተሰሩ የተለያዩ የኦዲት ሪፖርቶች የተለያየ የገንዘብ ጉድለትን የሚያመለክቱ ቢሆኑ፣
- ☞ ስለ አንድ ንብረት ሽያጭ የተደረጉ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ውሎች (አንዱ ውል ላይ ቤቱን ለከሳሽ የተሸጠ መሆኑ ሲገለፅ በሌላው ላይ ደግሞ ቤቱ ለተከሳሽ የተሸጠ መሆኑን የተገለፀበት)
- ☞ ስለ ሟች አሟሟት ምክንያት በምስክሮችና በህክምና ምርመራ ሪፖርት መካከል የሚታይ ልዩነት ሊጠቀስ ይችላሉ፡፡

እንደነዚህ አይነት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙም ፍ/ቤቱ የሚከተሉትን መሠረት በማድረግ መመዘን ይቻላል፡፡

- ☞ ልዩነት ወይም ቅራኔ መኖሩን በመጀመሪያ ደረጃ መረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

- ☞ ልዩነት ወይም ቅራኔ ያለ ቢመስልም መሠረታዊ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡
- ☞ ልዩነት ወይም ግጭት በማስረጃዎች መካከል ሲፈጠር ጉዳዩን ወንጀል ወይም ፍትሐብሔር ከሆኑ አንፃር ለይቶ መመዘን ያስፈልጋል፡፡
- ☞ ማስረጃውን ያወጣው ወይም የሰጠው ሰው ማስረጃውን ለማውጣት ያለውን ብቃት ወይም ቅርበት መመርመር ያስፈልጋል፡፡
- ☞ ማስረጀውን የሰጠው ወይም ያወጣው ሰው ከተከራካሪ ወገን ጋር ያለው ግንኙነት (ገለልተኛ ነው ወይስ አይደለም ከሚለው አንፃር) መመርመር ያስፈልጋል፡፡
- ☞ ማስረጃ የሰጠውን ወይም ያወጣውን ሰው አስቀርቦ መመርመር ይቻላል፡፡ (Ratanlal and Dhirajilal, p. 15)

## ***<u>መወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. ከላይ በጥያቄ ቁጥር 8.1. ላይ ለተገለፀው ጉዳይ የመድን ድርጅት (ተከሳሹ) ያቀረበውና ከአገር ውስጥ ገቢ የተሰጠው ደብዳቤ "ተከሳሹ ለግብር አከፋፈል ከሚያስታውቀው ገቢው ማረጋገጥ እንደተቻለው መኪናዋ የምታስገባው የተጣራ የቀን ገቢ ብር 15 መሆኑን እናስታውቃለን" የሚል ቢሆን ፍ/ቤቱ የቀን ገቢውን እንዴት መወሰን አለበት?
2. ምስክሮች ተጎጂ ነው ብለው የጠቀሱት ስም "ምህረት ኃ/ማሪያም" የሚል ሲሆን የህክምና ማስረጃው ደግሞ "ምህረት ገ/ስላሴ" የሚል ቢሆን ፍ/ቤቱ የሚደረሰው መደምደሚያ ምን መሆን አለበት?

## ***<u>8.2.3. የኦዲት ሰነዶች ምዝናን የሚመለከቱ ተጨማሪ ሐሳቦች</u>***

የገንዘብ ወይም የንብረት ጉድለትን ለማስረዳት የኦዲት ምርመራ ውጤቶች በማስረጃነት የሚቀርቡበት አጋጣሚ በርካታ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ሀሳቦች ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡

- ☞ የኦዲት ሰነዶች ላይ የተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች (መተማመኛዎች ጭምር) እንዳለቁ ማስረጃዎች (Conclusive evidence) ተደርገው መወሰድ የለባቸውም፡፡ አስረጅታቸው ይመዘናል፡፡ ማስተባበያም ሊቀርብባቸው ይችላል፡፡
- ☞ የኦዲት ሰነዶቹ ከፍርድ ቤት ውጪ የተሰሩ እንደመሆናቸው በደጋፊ ማስረጃዎች መጠናከራቸው (ኦዲተሮች፣ ታዛቢዎች) ለአስተማማኝነታቸው ክብደት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

የኦዲት ሰነዶች በማስረጃነት ሲቀርቡ ተከሳሾች ከሚያነሷቸው መከራከሪያዎች መካከል

- ☞ ሂሳቡ የተሰራው ትክክለኛ የሂሳብ አሠራር ደንብን ተከትሎ አይደለም፣
- ☞ ሂሳቡ የተሠራው በሌለሁበት በመሆኑ ፍ/ቤቱ ማስረጃ አድርጐ ሊወስደው አይገባም
- ☞ የገቢና የወጪ ማመዛዘኛዎችን የፈረምኩ ቢሆንም የጉድለት መተማመኛው ባለመፈረሙ ማስረጃነቱ የተሟላ አይደለም፣
- ☞ መተማመኛ ልፈርም የቻልኩት በግዴታ ነው፣
- ☞ በቀረቡ መተማመኛዎች ላይ የፈረምኩ ቢሆንም ቅሬታ (Reservation) እንዳለኝ በዚያው ላይ አስቀምጫለሁ… የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በዚህም መሠረት ፍ/ቤቱ ማስረጃውን ሲመረምርና ሲመዝን የጉዳዩን አይነት ግምት ውስጥ ማስገባት (ወንጀል ወይም ፍሐብሔር) የሚጠበቅበት ከመሆኑ በተጨማሪ የመቃወሚያ ነጥቦቹ የኦዲት ሪፖርቱ ላይ የሚያስከትሉትን ውጤት ማጤን ያስፈልገዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ተከሳሹ ለመቃወሚያነት የሚያቀርባቸውን ነጥቦች ለማስረዳት ያቀረበውን ማስረጃ፤ እንዲሁም ሂሳቡን የመረመሩት ሰዎች የሰጡትን የምስክርነት ቃል መሠረት በማድረግ ማስረጃውን መመርመር አለበት፡፡

### *8.2.4. የህትመት ውጤቶች አስረጅነት ምዘና*

ታትመው የወጡ ጽሁፎች (ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ መጽሐፎች...) በማስረጃነት የሚቀርቡበት አጋጣሚ በርካታ ነው፡፡ እነዚህ ጽሁፎች ውስጥ የተጠቀሱትና ማስረጃ ናቸው የተባሉት ፍሬ ነገሮች የስብሰባዎች ቃለ ጉባዔዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ ዜናዎች፣ ቃለ መጠይቆች የስብሰባ መግለጫዎች ... ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ በማስረጃነት በቀረቡ ጊዜ አስረጂነታቸው የሚመዘነው ከምን አንፃር ነው? የሚለው መመለስ የሚገባው ጥያቂ ነው፡፡

የህትመት ውጤቶች የአስረጅነት ብቃት የሚለካው ማስረጃው አግባብነት አለው ተብሎ ከቀረበበት ጭብጥና ይመለከተዋል ተብሎ ከተከሰሰው ሰው አንፃር ነው፡፡ በዚህም መሠረት የቀረበው ክስ (ወንጀልም ይሁን ፍትሐብሔር) በህትመት መሠረት የተፈፀመ ወንጀልን ወይም የካሳ ክስን መሠረት ያደረገ ከሆነ (አትሞ በማውጣት ማለት ነው) ለምሳሌ በጽሁፉ ስም ማጥፋት... እና የተከሰሰው ሰው አሳታሚው ወይም አዘጋጁ ከሆነ የህትመት ውጤቱ ክሱን በቀጥታ የማስረዳት ብቃት ይኖረዋል (የተፃፈው ነገር ስም ማጥፋት እስከሆነ ድረስ ማለት ነው)፡፡ እንዲያውም ለእንደዚህ ዓይነት አትሞ ማውጣትን ለሚመለከት ክስ ሰነዱ ብቸኛ ማስረጃ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ (Ratanlal and Dhirjilal, p. 392)::

እንዲሁም የማስረጃው አግባብነት ታትሞ መውጣትን ለማስረዳት ከሆነ (ለምሳሌ የንግድ ማህበር መመስረቻ ጽሁፍ ታትሞ መውጣቱን፣ የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ወይም የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ታትሞ መውጣቱን) የህትመት ውጤቱ ታትሞ መውጣቱ እስከተረጋገጠ ድረስ ይህንን የሚገልፀው የህትመት ውጤት ከፍተኛ አስረጅነት አለው፡፡

በሌላ በኩል ግን ክሱ አትሞ ማውጣትን፣ ወይም ታትሞ መውጣትን ሳይሆን በህትመት የተገለፀ ዜናን፣ የስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ ቃለ መጠይቅ...ወዘተ የሚመለከት ከሆነ በጋዜጣ ላይ የተነገረው ዜና "እንዲህ አለ፣ እንዲህ አደረገ" በሚል የገለፀውን ሰው፣ በጋዜጣ ወይም በሌላ የህትመት ውጤት ላይ በቃለ ጉባኤ ተወሰነ ተብሎ የተነገረውን ወሰኑ በተባሉት ሰዎች ላይ ወይም ቃለ መጠይቅ ላይ መልስ የሰጡትን ሰዎች (ተናጋሪ-Author) በሚመለከት የህትመት ውጤቱ አስረጅነት ክብደት ሊሰጠው አይችልም፡፡

ተናጋሪውን፣ ወይም ውሳኔ ሰጠ የተባለውን ሰው በተናገረው ወይም በወሰነው ውሳኔ ለመክሰስ ውሳኔውን ወይም ንግግሩን ያስረዳል በማለት የህትመት ውጤት በማስረጃነት ሲቀርብ (ተናጋሪው ራሱ አዘጋጅ ወይም አሳታሚ ካልሆነ በቀር) በእንግሎ አሜሪካ የህግ ስርዓት ተከታይ አገሮች በሰነድነት የቀረበ የሰሚ ሰሚ ማስረጃ (Documentary hearsay) በሚል በማስረጃነት አይቀበሉትም (Ratanlal and Dhirijilal, p. 392)

በኢትዮጵያ የሰሚ ሰሚ ማስረጃ እንዳይቀርብ የሚከለከል ህግ ስለሌለ ተናጋሪውን ለማስጠየቅ የሚቀርብ የህትመት ውጤትን አንቀበልም ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን ማስረጃው በሚገባ መመርመርና መመዘን አለበት፡፡ ተናጋሪው -ተናገረው፣ -ወሰነው፣ -አደረገው የተባለውን ንግግር፣ ውሳኔ፣ ድርጊት … በርግጥ የተናጋሪውን ይሁን የህትመት ውጤቱን የፃፈው ሰዉ ያዘጋጀው ወይም ያሳተመው የፈጠረው፣ ወይም አቃንቶ ያቀረበው ይሁን ሰነዱን በማየት ብቻ ማወቅ አይቻልም፡፡ ስለዚህ እንዲህ አይነቱ ማስረጀ አይቀርብም ማለት ባይገባም አስረጅነቱን ፍ/ቤቱ ክሱን በሌላ ማስረጃ ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡

## 8.3. የቴፕ እና ቪዲዮ ካሴቶች አስረጅት ምዘና

በቴፕ ወይም በቪዲዮ ካሴቶች የተቀረፁ ወይም የተቀዱ ንግግሮች ወይም በቪዲዮ ካሴት የተቀዱ ምስሎች በማስረጃነት የሚቀርቡበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች "እንዲህ አለ"፣ "እንዲህ አደረገ" ወይም "እንዲህ ተደረገ" የሚለውን ፍሬ ነገሮች ለማስረዳት አግባብነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ነገር ግን አግባብነት አላቸው ማለት አስረድተዋል ማለት ላይሆን ይችላል፡፡

የማስረጃው ተፈላጊነት በፍትሐብሔር ጉዳይ ከሆነ ምዘናው ጥብቅ ላይሆን ይችላል፡፡ አንድም የከሳሽ ማስረጃ ከተከሳሹ ማስረጀ ጋር አብሮ ሊመረመርና ሊገናዘብ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የአስረጅነት ደረጃው "በተሻለ ይመስላል"የሚል በመሆኑ ነው፡፡ ጉዳዩ የወንጀል ከሆነ ግን ማስረጃው በበርካታ ጥያቄዎች የተወጠረ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ፍ/ቤቱ ማስረጃውን፡-

- ☞ ቴፑን የቀዳው ወይም የቀረፀው ሰው፣ ወይም የተቀዳው ወይም የተቀረፀው ንግግር ወይም ድርጊት ሲፈፀም በስፍራው የነበረው ሰው ከሚሰጠው ምስክርነት ጋር በማገናዘብ፣
- ☞ ማስረጃው ተመሳስሎ ሲሠራ (Fabricated)፣ ወይም ተቆራርጦ የቀረበ (Reenacted) ወይም የተቀነባበረ (Reconstructed) የመሆን ዕድሉ የሰፋ በመሆኑ አስረጅነቱ ሲመዘን ከተቀዳው ወይም ከተቀረፀው ድምፅ ወይም ምስል ሙሉ ይዘት፣ የንግግሩ ወይም ድርጊቱ ዓላማ፣ አንፃር በማገናዘብ መመዘን ያስፈልጋል፡፡ (May, p. 26-27)

## 8.4. የፎቶ ግራፍ ማስረጃዎች አስረጅነት ምዘና

ፎቶ ግራፍ የአንድን ሰው ማንነት (Identity)፣ ወይም የተጐጂውን የአካል ጉዳት ወይም የተሰረቀውን ንብረት ወይም ወንጀል የተፈፀመበትን ቦታ የሚመለከት ሊሆን ይችላል፡፡ ያም ሆኖ ግን የፎቶግራፍ ማስረጃ ሲመዘን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

በመሠረቱ ስለቴፕና ቪዲዮ ካሴቶች ከላይ የተገለፁት ለፎቶ ግራፍ ማስረጃዎች ምዘናም አግባብነት አላቸው፡፡ በተጨማሪም በማስረጃነት የቀረበው ፎቶግራፍ የታተመው ከመጀመሪያው ምንጭ (Negative) መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል (May, p. 16)፡፡ በአጠቃላይም የህትመት ውጤቶችን፣ የቴፕና የቪዲዮ ካሴቶችን፣ እና ፎቶግራፎችን አስረጅነት ለማረጋገጥ የሚደረግን ጥብቅ የማስረጃ ምዘናን (በተለይ በወንጀል ጉዳይ) ፍ/ቤቱ የሚከተለው "ፍርድ ቤት እውነትን ይገልፃል ብሎ በማያምንበት ማስረጃ ላይ በመመስረት ውሳኔ መስጠት የለበትም፤ የቀረበው ማስረጃ በተቻለ መጠን እውነቱን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት" በሚለው ምክንያት መነሻ ነው፡፡ (May, p. 27)፡፡

## 8.5. የኤግዚቢት ማስረጃ አስረጅነት ምዘና

የኤግዚቢት ማስረጃ ዋነኛ አስተወጽኦው አካባቢያዊ ማስረጃ በመሆን ስለተፈለገው ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ግንዛቤ እንዲወስድ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ የኤግዚቢት

ማስረጃ በሌላ ማስረጃ የተነገረውን በመደገፍ (corroboration) ማገልገል እንጂ ሌላ ማስረጃ በሌለበት በራሱ ተፈላጊው ፍሬ ነገር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ያረጋግጣል ማለት አዳጋች ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን ሌሎች ማስረጃዎችን የማጠናከር አስተዋጽኦው ከተፍተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ በወንጀል ጉዳይ ተሰረቀ የተባለውን ዕቃ በማየት በምስክሮች "ቤት ገብቶ ዕቃውን ካወጣ በኋላ ተሸክሞ ሲሮጥ አይቻለሁ" በሚል ከተነገረው ቃል ጋር በማገናዘብ ዕቃውን ሰው ተሸክሞት ሊሮጥ የሚችል መሆን አለመሆኑን ፍ/ቤቱ ሊረዳው ይችላል፡፡ ግድያ ለመፈፀም አገልግሎት ላይ የዋለ ነው በሚል የቀረበን ዱላ በማየት ዱላው ሰው መግደል የሚያስችል መሆን አለመሆኑን ለመገንዘብና ተከሳሹ ደበደበ በሚል በተናገሩት ቃሎችና ሞተ በተባለው ሰው ሞት መካከል የምክንያትና የውጤት ግንኙነት እንዳለና እንደሌለ ለመገመት ያስችላል፡፡ በአጠቃላይ የኤግዚቢት ማስረጃ ምዘና በሌላ ማስረጃ የተናገረውን ፍሬ ነገር ትክክለኛነትን ወይም ተዓማኒነት በመገንባት ወይም በማፍረስ ላይ ያተኮረ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

## ምዕራፍ 9

## የእምነት ቃል አስረጂነትን ስለመመዘን

**ዝርዝር አላማዎች**

ሰልጣኞች ይህንን ምእራፍ ሲያጠናቅቁ ፣

- በፍርድ ቤት እና ከፍርድ ቤት ውጪ የሚሰጡ የእምነት ቃሎችን ይለያሉ፡፡
- የእምነት ቃል አስረጅነት በፍትሀብሄርና በወንጀል ጉዳይ መመዘን ክህሎት ያዳብራሉ፡፡

### 9.1. ጠቅላላ

በምዕራፍ 2 ላይ "ማስረጃ ማቅረብ ስለማያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች" በሚል ርዕስ ስር ከተጠቀሱት ጉዳዮች መካከል "የታመኑ ፍሬ ነገሮች" እንደሚገኙበት፣ የታመኑ ፍሬ ነገሮችን "ከፍ/ቤት ውጪ" እና "ከፍ/ቤት ውስጥ" በሚል ከፋፍሎ ማየት እንደሚቻል፣ ከነዚህ ውስጥም "ከፍ/ቤት ውጪ" የታመኑ ፍሬነገሮች ተፈላጊውን ፍሬ ነገር በተመለከተ በራሳቸው ማስረጃዎች ሲሆኑ፣ ነገር ግን ማስተባበያ ማስረጃ ሊቀርብባቸው

እንደሚችል፣ "በፍ/ቤት ውስጥ የታመኑ ፍሬ ነገሮች" የሚባሉት ደግሞ በፍትሐብሔር ጉዳይ ማስተባበያ ማስረጃ ሳይቀርብባቸው ለታመነው ፍሬ ነገር መኖር ማረጋገጫ ተደርገው ሊወሰዱ፤የወንጀል ጉዳይ ከሆነ ግን እንደሁኔታው በከሳሽ ማስረጃነት ከመቆጠር እና በሌላ ማስረጃ ከመደገፍ አልፈው ማስተባበያ ማስረጃ ሊቀርብባቸው እንደሚችል፤ ወይም እንዳለቁ ፍሬ ነገሮች ተቆጥረው ማስተባበያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ የጥፋተኛነት ውሳኔ ሊያሰጡ እንደሚችሉ ተገልፆአል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ "የታመኑ ፍሬ ነገሮች ላይ ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልግም" ቢባልም እንዲህ ዓይነት መደምደሚያ ላይ ለመድረስ" "ፍሬ ነገሮቹ በርግጥ ታምነዋል ወይ?" በሚል መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ ፍሬ ነገሮቹ የታመኑ ናቸው፤ ስለዚህ ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልጋቸውም ለማለት አስቀድሞ መታመናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ ተከሳሹ (በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር) የሰጠውን ቃል ከክሱ ጭብጥ ጋር ማገናዘብን የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ማስረጃ በቀረበ ጊዜ ማስረጃው አስረድቷል ወይስ አላስረዳም የሚለውን ለመወሰን መመዘን እንደሚያስፈልግ ሁሉ በጭብጥ የተያው ፍሬ ነገር ታምኗል ወይስ አልታመነም ለማለት የተሰጠውን ቃል መመዘን አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለዚህም 'ታመነ' የተባለው ፍሬ ነገር የታመነ መሆኑን ለማረጋገጥ "በርግጥ የዕምነት ቃል ነው ወይ?" በሚል መጠየቅና መመዘን ተገቢ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር በተከሳሽ የተሰጡ ቃሎች ላይ ላዩን ሲታዩ የታመኑ ፍሬ ነገሮችን የሚመስከቱ ቢመስሉም ነገር ግን ከተፈላጊው ጭብጥ ወይም ፍሬ ነገር አንፃር ሲገናዘቡ ታምኗል የማያስብሉ ይሆናሉ፡፡ "ተከሳሹ ሾፌር ሆኖ ሳለ ከሙያው አንፃር ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ሲገባው በቸልተኛነት ሰው ገጭቶ ገድሏል" በሚል ለቀረበበት ክስ በሰጠው ቃል "መስመሬን ጠብቄ እየነዳሁ እያለ ሟች መኪና ተከልሎ በድንገት ገብቶብኝ ሊገጭ ችሏል" ቢል ይህ በግርድፉ ሲታይ የአመነ ቢመስልም ነገር ግን ጠበቅ ተብሎ ሲመረመር ድርጊቱ የተፈፀመው በቸልተኛነት ይሁን በአጋጣሚ ለመለየት አያስችልም፡፡ ስለዚህም ይህንን ቃል በእምነት ቃልነት ከመውሰድ ይልቅ ድርጊቱ ስለተፈፀመበት አካባቢያዊ ሁኔታ (ማለትም የተከሳሹን ፍጥነት መጠንና፣ የተፈቀደውን የፍጥነት መጠን፣ ሟች ተከልሎበታል የተባለው መኪና

እይታን የሚከላከል መሆን አለመሆኑ ሚች ወደ መኪና መንገድ የገባበት ሁኔታ) በማስረጃ ሊረጋገጥ ይገባዋል፡፡ የዚህ ምዕራፍ ትኩረትም የተቀባይነትን መመዘኛ የአሟላ የዕምነት ቃል ነው የተባለ ቃል በርግጥም የዕምነት ቃል መሆኑ ወይም አለመሆኑን የሚመዘንበትን መሠረታዊ ነጥቦች መግለፅ ነው፡፡

በመጨረሻም ወደ ዝርዝር ነጥቦች ከመግባት አስቀድሞ የታመነ ፍሬ ነገር ነው የተባለ ቃል አመዛዘን ከወንጀልና ከፍትሐብሔር ጉዳዮች አንፃር ያለው ልዩነት ሊታወቅ ይገባል፡፡ በምዕራፍ 2 ስር እንደተጠቀሰው አንድ ፍሬ ነገር ታምኗል የሚባልበት መመዘኛና የሚያስከትለውም ውጤት እንደጉዳዩ ፍትሐብሔር ወይም ወንጀል መሆን የሚለያይ በመሆኑ በዚህ ምዕራፍ ስለታመኑ ፍሬ ነገሮች አስረጅነት የሚገለፀውም ይህንን መሠረት በአደረገ ሁኔታ ይሆናል፡፡

## *9.2. በወንጀል ጉዳይ የታመኑ ፍሬ ነገሮች አስረጅነት ምዘና*

በወንጀል ጉዳይ የታመኑ ፍሬ ነገሮች ብለን የምንመድባቸው በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 27/2/ እና ወይም በቁጥር 35 መሠረት ለመርማሪ ፖሊስ ወይም በምርመራ ጊዜ ቃል ለተቀበለ ፍ/ቤት የተሰጡ ቃሎች እና ከቁጥር 132-134 ላይ በተደነገገው መሠረት ክስ ችሎት ቀርቦ ተነብቦ ተከሳሹ እምነት ክህደት ሲጠየቅ የሰጠው ቃል ናቸው፡፡ የመጀመሪያው (በቁጥር 27 እና ወይም 35 መሠረት የተሰጠው) ቃል የዕምነት ቃል ነው በሚል ከመደምደምና ክሱን አስረድቷል ከማለት በፊት፣

- ☞ ወንጀሉን የሚያቋቁሙትን ፍሬ ነገሮች (ድርጊቱና የሀሳብ ክፍሉን) እንዲሁም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳ ምክንያት (Motive) ተሟልቶ የታመነ መሆኑን፣
- ☞ ተፈላጊው የምክንያትና ውጤት ግንኙነት የተሟላ መሆኑን፣
- ☞ የተሰጠው ቃል የመከላከያ ጭብጥ የሌለበት መሆኑን፣ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም በተሞክሮ እንደሚታየው ሰዎች ወንጀል መፈፀማቸውን አምነው ቃላቸውን እንዲሰጡም ባልተገደዱበት ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች- ለምሳሌ

የምርመራውን ትክክለኛ አቅጣጫ ለማሳትና ሌሎች ሰዎችን በወንጀል ከመጠየቅ ለማዳን፣ ወይም የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት፣ ማህበራዊ ተቀባይነትን ለማግኘት ወይም ከማይፈልጉት ግዴታ ለመዳን ያልፈፀሙትን ወንጀል ፈፅመናል በማለት ቃላቸውን ሊሰጡ ይችላሉ (መዝገቡ ምትኬ ገፅ 50-52)፡፡ በዚህም መሠረት ምንም እንኳን የሰጡት ቃል የዕምነት ቃል የሚያስብል ቢሆንም፤ ቃል ለመስጠት የተገደዱ ባይሆኑ እንኳን የሰጡትን ቃል ከሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ የተሰጠው ቃል በትክክልም የዕምነት ቃል መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ እንዲሁም ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃ የአቀረበ ከሆነ የዕምነት ቃሉ እና የመከላከያ ማስረጃዎቹ የገለፁዋቸው ፍሬ ነገሮች ተገናዝበው ሊመረመሩ ይገባል፡፡

የዕምነት ቃሉ የተሰጠው በፍ/ቤት ክሱ ተነብቦ ካበቃና ተከሳሹ እንዲረዳው ከተደረገ በኂላ ለተጠየቀው የዕምነት ክህደት በመልስነት ተከሳሹ ያስመዘገበው ከሆነም ከላይ በመግቢያዉ የተጠቀሱት የመመዘኛ ነጥቦች ተፈፃሚነት አላቸው፡፡ የ/ወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 134/1/ ላይ እንደተገለፀው ተከሳሹ አመነ ለመባል "በክሱ ማመልከቻው ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ ያመነ" መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ ስለዚህ፡-

- ☞ በከፊል የሚሰጥ የዕምነት ቃል የሚባል ነገር የለም፡፡ በክሱ ማመልከቻው ላይ የተገለፀውን በሙሉ ሊያምን ይገባልና፡፡
- ☞ ተሰጠ በተባለው የዕምነት ቃል ውስጥ ከፊሉን ማለትም ተከሳሹን የሚያስጠይቀውን ብቻ ነጥሎ ወስዶ ጥፋተኛ ነህ ማለት አይገባም፡፡ የሚጐዳውም የሚጠቅመውም ቃል አንድ ላይ ተወስዶ ከቀረበው ክስ አንፃር የዕምነት ቃል ነው ለማለት ያስችላል? ወይም አያስችልም? የሚለው መወሰን አለበት፡፡

እነዚህ የመመዘኛ ነጥቦች ከችሎት ውጭ ለተሰጠ የዕምነት ቃልም በመመዘኛነት ያገለግላሉ፡፡

***መወያያ ጥያቄዎች***

1. ለፖሊስ ወይም በምርመራ ጊዜ ለፍ/ቤት የተሰጠ የዕምነት ቃል ብቻውን ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለመፈፀሙ ሊያስረዳ ይችላል? ወይስ በሌላ ማስረጃ መደገፍ ይኖርበታል?
2. መርማሪ ፖሊስ ከተከሳሹ የዕምነት ቃል ሲቀበል በቦታው ሆነን ሰምተናል የሚሉ ምስክሮች (በተለምዶ የደረጃ ምስክሮች የሚባሉ) የሚሰጡት የምስክርነት ቃል የዕምነት ቃሉን አስረጂነት ከመመዘን አኳያ አስረጅነቱ ምን ያህል ነው?
3. በአንድ ጉዳይ ተከሳሽዋ በ1949 ዓ.ም በወጣው የወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ጨካኝና ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ባልዋን በመጥረቢያ ቆራርጣ ገድላለች በሚል ለቀረበባት ክስ የዕምነት ክህደት ስትጠየቅ በሰጠችው ቃል "ሟች ባለቤቴ የገበሬው ማህበር ልብስ ሰፊ በመሆኑ ገቢ ስለነበረው ዘወትር እየጠጣ ሲገባ ይረብሸኛል፡፡ ቤት አቃጥላለሁ እያለ እሳቱን በውሐ ሳጠፋበት በጨለማ ይደበድበኛል፡፡ በየካቲት ወር 1978 የአምስት ወር እርጉዝ ሳለሁ እንደተለመደው ሰክሮ በመግባት ሲደበድበኝ በሆዴ ያለው ጽንስ አስወረደኝ በዚህ ምክንያት ወደ 3 ወራት ያህል ታምሜ ተኝቻለሁ፡፡ የአሁኑ ድርጊት በተፈፀመ ዕለት እንደተለመደው ሰክሮ መጥቶ ቀደም ብዬ ለገበሬው ማህበር ስለስካሩ ከስሸው ስለነበረ እየተንገዳገደ መጥቶ ሊመታኝ ሲጠጋ እኔ እንደተለመደው እሳቱን በውሃ አጠፋሁት፤ ምክንያቱም ጨለማ ከሆነ አያየኝም ብዬ ነበር፡፡ ከዚያ የት ትገቢያለሽ ብሎ ከበሩ አጠገብ የእንጨት መፈለጫ መጥረቢያ በእጁ ይዞ ስለነበር ጨለማ ቢሆንም መፎከርና መሳደቡን ስላልተወ ጓዳ ገብቼ ተደብቄ ከነበርኩበት ወጣሁና ይዞት የነበረውን መጥረቢያ ነጥቄ ከግንባሩ ላይ በስለቱ መታሁት፤ ወደቀ፡፡ በንዴት ላይ ስለነበርኩ ስንት ጊዜ እንደመታሁት አላውቅም፡፡ ግን መትቼዋለሁ፡፡ ስለሞተም ሟች ለቀንበር መቅበሪያ በጓዳ ውስጥ ቆፍሮት ከነበረው ጉድጓድ ውስጥ ከትቼው አፈር አለበስኩት፡፡ ለብሶት የነበረውን ልብስም አውልቄ በነጠላ ሸፍኜ ነው የቀበርኩት፡፡ … ድርጊቱን በንዴት የፈፀምኩት ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ይቅርታ ያድርግልኝ" ብላለች (ከጠ/ፍ/ቤት ወ/ይ/መ/ቁ. 927/79 የተወሰደ)፡፡

ተከሳሽዋ የሰጠችው ቃል ወንጀሉን መፈፀምዋን አምናለች ለማለት ያስችላል?

4. በወንጀል ጉዳይ ተከሳሹ ክሱ ተነቦለት የዕምነት ክህደቱን ሲጠየቅ አምኖ ያስመዘገበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግን ዐቃቤ ህጉና ተከሳሹ ማስረጃዎቻቸውን

እንዲያቀርቡ ሊያዝዝ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 134/2/)፡፡ በዚህ ትዕዛዝ መሠረት የቀረበው የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ተከሳሹ ከሰጠው የዕምነት ቃል በተለየ ያስረዳ ቢሆን (ለምሳሌ ተከሳሹ ሆን ብሎ መፈፀሙን አምኖ ቃሉን ሲሰጥ የዐቃቤ ህግ የምስክሮች ግን በመከላከል ነው የተፈፀመው በሚል ቢያስረዱ) ፍ/ቤቱ ውሳኔ ለመስጠት ምን የመመዘኛ ስልቶችን መጠቀም አለበት?

## *9.3. በፍትሐብሔር ጉዳይ የታመኑ ፍሬ ነገሮች አስረጅት ምዘና*

በፍትሐብሔር ጉዳይ የዕምነት ቃል ሊሰጥባቸው የሚችሉባቸው ሁኔታዎች በምዕራፍ 2 ላይ ተመልክተዋል፡፡ ከዚህ አንፃር የመጀመሪያው እርምጃ ፍሬ ነገሮቹ የታመኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ ሲሆን ይህም በአቤቱታ ላይ የተገለፀውን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ ተከሳሹ ከሚሰጠው መልስ ጋር በማገናዘብ መመርመርን ይጠይቃል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

- ☞ በአቤቱታ ጽሁፎች እና በችሎት ክርክሮች ተከሳሹ (ወይም የተከሳሽ ከሳሽ ክስ ካለ ከሳሹ) የገለፃቸው ፍሬ ነገሮች ተለይተው መታወቅ አለባቸው፣
- ☞ በዚህም መሠረት በግልፅ አምኖአል ለማለት ተከሳሹ (ወይም የተከሳሽ ከሳሽ ክስ ካለ የከሳሹ) በከሳሹ (ወይም በተከሳሽ ከሳሹ) አቤቱታ የተገለፀውን በግልፅ መቀበሉ መረጋገጥ አለበት፡፡
- ☞ በዝምታ ታምኖአል ለማለትም በክስ ወይም በተከሳሽ ከሳሽ ክስ አቤቱታ ላይ የተገለፁት ፍሬ ነገሮችን በማመን ወይም በማስተባበል መልስ ያልተሰጠባቸው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡
- ☞ እንዲሁም ከችሎት ውጪ የታመነ ፍሬ ነገር ከሆነ የታመነው ፍሬ ነገር ከተከሳሹና መከላከያ ማስረጃዎች አንፃር መመዘን አለበት፡፡
- ☞ በመጨረሻም ታምኖአል ወይም አልታመነም በሚል ለመወሰን የታመነ ነው በሚል የተሰጠው ቃል አስረጅነት በተያዘው የፍትሐብሔር ጉዳይ የአስረጅት መመዘኛ (ደረጃ) አንፃር መታየት አለበት፡፡

## መወያያ ጥያቄዎች

1. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 235/2/ ላይ በግልፅ የተካደ ባይሆንም በአነጋገሩ ስልት እንደተካደ የሚቆጠር ከሆነ እንዳልታመነ ተቆጥሮ ማስረጃ እንደሚቀርብ ተደንግጉአል፡፡ "በአነጋገር ስልት እንደተካደ የሚቆጠር" ሲባል ምን ማለት ነው?
2. በዚሁ በቁጥር 235/2/ ላይ "ፍርድ ቤቱ አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው እንደታመኑ በተቆጠሩት ነገሮች ላይ ማስረጃ እንዲሰማባቸው ለማዘዝ ይችላል" ተብሎአል፡፡ ከዚህ አንፃር፡-

   ☞ እንደታመኑ ተቆጥረው እያለ ማስረጃ ሊሰማባቸው የሚቻለው በምን ዓይነት መንገድ የታመኑትን ነው? በግልፅና በዝርዝር በታመኑት ላይ? በዝምታ በታለፉት ላይ? በመሸሽ የተስተባበሉት ላይ? ወይስ በሁሉም ላይ?

   ☞ በፍ/ቤቱ ማስረጃ መሰማት አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ የሚያገኘው መቼ ነው?

## ማጣቀሻዎች


1. አለማየሁ ኃይሌ "የኤክስፔርት ማስረጃ በኢትዮጵያ ህግ -በማነፃፀር የቀረበ"
2. Black, H. Campbell, Black's Law Dictionary, 6th ed. West Publishing Co.St. Louis, Minn. USA(1990)
3. Clermont, Kevin M. Standard of Proof in Japan and the United States, Cornell Law School Working Paper series, Paper 5 (2003) http://15r.nellco.ors/cornell/clsops/papers/5
4. Demougin, D and Claude Fluet, Preponderace of evidence: Tort Rules and the Efficient Standard of proof (July, 2000)
5. Fisher,S.Z. Ethiopian Criminal procedure; A Source Book, Faculty of Law, HSIU(1969)

6. Hermann. J Models for Reform of the Criminal Trail in Eastern Europe: A Comparative Perspective, st.Louis, 127 Warsaw Transatlantic L.J. (2003)
7. መዝገቡ ምትኬ ስለተከሳሽ እምነት ቃልና ህጋዊ ዉጤት ፣ ህጋዊነት መፅሔት ቅጽ 1 ቁጥር 2 (ነሐሴ 1981 ዓ.ም)
8. May, R. Criminal Evidence (3rd ed), Sweet and Maxwell, London (1995)
9. Ratanlal and Dhirajlal, The Law of Evidence 21st ed, N.D., India (2004)

**<u>የፍርድ ቤት ዉሳኔዎች</u>**

1. የፍትሀብሄር መዝገብ ቁጥር 201/77
2. የፍትሀብሄር መዝገብ ቁጥር 1730/80
3. የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1118/76
4. የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 4/80
5. የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 67/80
6. የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 112/80